መናቃነቅ አቅቶት ያቃስታል። ሽማግሌውን የተጫናቸው እቃ ከበድ ያለ ስለነበር እርሳቸውም እንዲሁ ያቃስታሉ። ከእዚያ የነበሩ ሰዎች ተሰባስበው ሽማግሌውንና ፈረሱን የተጫነውን እቃ ለማንሳትና ብድግ ለማድረግ ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም። የአንዳንዱ አያያዝ ያሳዋቂ ሲሆን የሌላውም የማስመሰል እንጂ ከልብ ስላልነበረ ሙከራው ሁሉ ዋጋቢስ ይሆናል። በመካከሉ ሽማግሌው ትንፋሽ አጥሯቸው ሊሞቱ ሆነ። አንድ ሰው ከስር ገብቶ ጋሪውን ብድግ ቢያደርገው ጥሩ መፍትሄ እንደሆነ ሁሉም አወቀ። ነገር ግን ሁሉም ለነፍሱ ስለፈራ የሚደፍር ጠፋ። ከጋሪው ላይ ወጥቶ ሞኑቱን ለማራገፍ መሞከር ማለት ክብደት ጨምሮ ሽማግሌውን በይበልጥ መጉዳት ሆነ። ስለዚህ ሰው ሁሉ እርስ በእርስ ተፋጠጠ እንጂ ወደ መፍትሔ የሚሄድ አልተገኘም።

ገቨር ጩኸቱን ሰምቶ ስለመጣ በአስቸኳይ የእቃ ማንሻ መሣሪያ እንዲመጣ ሰው ይልካል። ይህን ጊዜ ነበር መሴይ ማንደላይን ከሥፍራው የደረሰው። የተሰበሰበው ሕዝብ መንገዱን ለቀቀለት። ሽማግሌው 'እባካችሁ ርዱኝ' ሲሉ ጮኹ። «የማነው ሳምራዊ እኚህን ሽማግሌ የሚያድን!» ሲል መሴይ ማንደላይን ጠይቆ ዞር ዞር ብሎ ዓይኑን አማተረ። አሁንም መፋጠጥ ብቻ ሆነ። መሴይ ማንደላይን «የእቃ ማንሻ መሣሪያ ያለው የለም?» ብሎ ሲጠይቅ «ሰዎች ሊያመጡ ሄደዋል» አለ አንድ ሰው።

«ቶሎ ይደርሳሉ?. ብሎ ሲጠይቅም «ፍሎቮ ከተባለ ሥፍራ ወደሚገኝ አንጥረኛ ነው የሄዱት። ያ ደግሞ ቢያንስ አንድ ሩብ ሰዓት ያህል ይወስዳል» ተብሎ ሲመልስለት «ሩብ ሰዓት!» ሲል ጮኸ። ሌሊቱን በሙሉ ሲዘንብ ስላደረ አካባቢው ሁሉ ጨቅይቷል። ፈረሱ ተንሸራትቶ የወደቀበትም ሥፍራ ማጥ ስለነበር የጋሪው እግሮች በአንድ በኩል ከጭቃው ውስጥ ወደ ውስጥ ሰምጠዋል። ሁኔታው ይህ ስለነበር በአምስት ደቂቃ ውስጥ የሽማግሌው ወገብ የሚቀነጠስ መሰለ።

«ሩብ ሰዓት መቆየት አንችልም» አላቸው መሴይ ማንደላይን ከዚያ የተሰበሰበውን ሰው እያየ። ይህን ጊዜ «ሌላ ምርጫ የለንም» የሚል ድምፅ ከሕዝቡ መካከል ካንዱ ሲሰማ «ከሩብ ሰዓት በኋላማ ዋጋ የለውም። ጋሪው እየሰመጠ መሆኑን አይታያችሁም እንዴ» ሲል በቁጣ ተናገረ ደጉ ሰው።

«ምንም ማድረግ አይቻልም» ሲባል «ለሙ» አለ መሴይ ማንደላይን፣ «ከስር በቶሎ ለመግባት ከወሰን ከእቃው መጫኛ ስር ሰው ሊያስገባ የሚችል በቂ ቦታ አለ። ከዘገየን ግን ይህን ለማድረግ አይቻልም። አሁኑኑ የተወሰኑ ሰዎች ከጋሪው ስር ተንሏቅቀው ከገቡ ጋሪውን በጀርባቸው ተሸክመው ብድግ ሊያደርጉት ይችላሉ። ይህን ካደረግን ሽማግሌው በግማሽ ደቂቃ

ውስጥ ወደ ውጭ ይወጣሉ። አለበለዚያ መሞታቸው ነው። ስለዚህ ግነው አሁን ሰውዬውን የሚያድን? ይህን ሳደረገ መቶ ፍራንክ ይከፈለዋል።»

ሁሉም ዝም!

«ሁለት መቶ ፍራንክ» ብሎ መሴይ ማንደላይን ሲናገር የተሰበሰበው ሰው ሁሉ መሬት መሬቱን ያይ ጀመር። ሆኖም «በድፍረት ከጋሪው ስር የሚገባ ሰው እጅግ በጣም ጡንቸኛ መሆን አለበት። ለመሆኑ ደፍር ሰው ቢገኝ እንኳን እንዴት ብሎ ነው ራሱን የሚያወጣው፣ ከዚያው ተጨፍልቆ ይቀራል እንጂ!» ሲል የሆነ ሰው ተናገረ።

«በሉ እባካችሁ፣ አራት መቶ ፍራንክ» ብሎ መሴይ ማንደላይን ሲናገር አሁንም ዝምታ ሰፈነ። ቆይቶ ግን «ፈቃደኛነቱ እኮ አይደለም የጠፋው» አለ አንዱ። ደጉ ሰው ግን ፈቃደኛ ሰው ካለ በሚል በዓይኑ ሲያማትር ገቨርን አየው። ከዚያ ለመኖሩ አላወቀም ነበር። ገቨር ተናገረ።

«ጉልበትና ኃይል ነው የሚያስፈልገው። ከዚህ ውስጥ የሚገባ ሰው ደፋርና እጅግ ጉልበተኛ መሆን አለበት። ይህን የሚያህል የእቃ መጫኛ ጋሪ ከነእቃው በጀርባው ተሸክሞ ለማንሳት የሚችል ብርቱ ጉልበት ያለው ሰው መሆን ይኖርበታል።» ቀጥሎም ገቨር እንደ ልማዱ መሴይ ማንደላይንን አፍጥጦ እያየ እያንዳንዱን ቃል ረገጥ አድርጎ ተናገረ።

«መሴይ ማንደላይን፣ አሁን እርስዎ የሚጠይቁትን ለማከናወን የሚችል አንድ ሰው ብቻ ነበር የማውቀው» ሲል መሴይ ማንደላይን ደነገጠ። ገቨር ዓይኑን ከመሴይ ማንደላይን ሳያነሳ የአነጋገር ዘይቤውን ለወጥ አድርጎ ንግግሩን በመቀጠል «ይህ ሰው ወንጀለኛ ነበር» አለ።

«እሱን እንኳን አሁን ብንተወው ይሻላል» ብሎ መሴይ ማንደላይን ሊመልስለት «ይህ ሰው ቱሉን ከሚባል ሥፍራ እስረኛ ነበር» አለው። ይኸኔ የመሴይ ማንደላይን ፊት አመድ መሰለ። ማንም ደፍሮ ስላልተናገረ አሁንም ፀጥታ ሰፈነ። ሆኖም ብዙም ሳይቆይ «ወይኔ ተጨፈለኩ» ብለው ሽማግሌው ሲጮሁ መሴይ ማንደላይን ቀና ብሎ አካባቢውን ቃኘ።

ገቨር አሁንም እንዳፈጠጠበት ነው። መልሶ የተሰበሰበውን ሰው ሁሉ ተመለከተ። ቀጥሎ የሀዘኔታ ገጽታ ለሕዝቡ አሳይቶ ቃል ሳይተነፍስ ተንበረከከ። ወዲያው ከመቅጽበት ከእቃ መጫኛው ጋሪ ስር ሲገባ ሰው ሁሉ ተጨነቀ። ሰዉ ሁሉ ወሬ ለማየት ከወዲያ ወዲህ እያለ ተተራመሰ። መሴይ ማንደላይን ለመቀመጥ ይችል እንደሆነ ከአንዱም ሁለቴ ሞከረ።

«መሴይ ማንደላይን፣ ከዚያ በቶሎ ተመልሰህ ብትወጣ ይሻላል» ሲል የተሰበሰበው ሕዝብ በሙሉ በአንድነት ጮኸ። ሽማግሌውም «መሴይ ማንደላይን ካለህበት ቶሎ ብለህ ውጣ። እኔ ልሙት እንጂ እንተ ምን በወጣህ በእኔ ምክንያት ትሞታለህ? በቶሎ ካልወጣህ አንተም ትጨፈለቃለህ» ብለው ሲናገሩ መሴይ ማንደላይን መልስ አልሰጣቸውም። አሁን ሕዝቡም ፀጥ አለ። ጋሪውና ፈረሱ በመሴይ ማንደላይን በተነካኩ ጊዜ ይበልጡኑ ወደ ውስጥ መስረግ ጀመሩ። እንዲያውም ከነአላቁቴው መሴይ ማንደላይን ራሱን ማላቀቅ ተሳነው። ሰዉ ሁሉ እጅግ በጣም ተጨነቀ። ነገር ግን ከጭቃው ውስጥ ሰምጦ የነበረው እግር ተነቃንቆ ወደ ላይ መውጣት ጀመረ። «ከግራ ተቀኝ ያዙ እንጂ» ሲል መሴይ ማንደላይን በተራው ጮኸ። እርሱም ባለው ኃይል ጋሪውን ወደ ላይ ለማንሳት ሞከረ። የተሰበሰበው ሕዝብም ለመያዝ የሚችለውን ሁሉ ይዞ ድጋፉን አበረከተ። የአንድ ሰው ድፍረት ሰዉን ሁሉ አነቃቅቶ የሌላቸው ጉልበት ሰጣቸው። ወደ ሃያ ገደማ የሚሆን ሰው በሽክሙና ጋሪውን በማንሳት ስለተባበረ ጋሪው ከእነአቃው ብድግ ብሎ ቆመ። ሽማግሌውም ከሞት ዳኑ።

መሴይ ማንደላይን ሲነሳ ፊቱ የገረጣ መሰለ። ከመጠን በላይ አልቦታል። ልብሱ በጭቃ ተለውሶ ካንዳንድ ቦታ ላይ ተቀዳዷል። የደስታ ይሁን የሀዘን አልታወቅም፣ ሰው ሁሉ አለቀሰ። ሽማግሌው የመሴይ ማንደላይን እግር ሳሙ። 'ደጉ አምላክ' ሲሉ አመሰገኑት። መሴይ ማንደላይንም በጣም ደስ ስላለው ዣቪርን በእርካታ ዓይን አየው። ዣቪር ግን አሁንም በዓይነ-ቁራኛ ጠበቀው። ሽማግሌው መላላጥ እንጂ ስብራት ባይኖርባቸውም ጉልበታቸው አልነቃነቅ ብሎ አስቸገራቸው። መሴይ ማንደላይን ከሴሮች ጋር ተነጋግሮ ከሆነ ገዳም ውስጥ በአትክልተኛነት እንዲሠሩ አስቀጠራቸው።

2

ፋንቲን ወደ ትውልድ አገርዋ ስትመለስ ከተማው ተለውጦ ነው የቆያት። ግን እንደሆነች ግን ማንም አላስታወሰም። ደግነቱ የመሴይ ማንደላይን ብሩክ ከሚሠራበት ክፍል ኮፍት ቦታ ስለነበረ ከዚያ ተቀጠረች። ነገር ግን ሥራው እርስዋ ያልተነሰችበት ዓይነት ስለነበር በመጀመሪያ እጅግ ጭንቅ ተጋላች። በዚህም ምክንያት ለእርስዋ የሚከፈለው ደመወዝ ዝቅተኛ ሆነ። ለእርስዋ ቦሩ ደረጃ ግን በቂ ገንዘብ ስለነበረና ሠርታም ለማደር ባመቻልዋ ችግርዋ ተቃለላት ለማለት ይቻላል።

ፋንቲን ራስዋን ችላ በመኖርዋ በጣም ደስ አላት። ሊላውን ላያስችሩ ራስን ችሎና በሁለት እግር ቆሞ ለማደር መቻል የውስጥ እንደሚሰጥ ማንም የሚከደው አይደለም። በመጀመሪያ ወር ደመወዝዋ መስታውት ገዛች። ውብ የሆነው ፀጉርዋን፣ ከወተት የነጡ ጥርሶችዋን፣ እድሜ ያላረገፈው የልጅነት መልክዋን ጠዋት ማታ ለማየት በመቻልዋ ደስታዋ እጥፍ ሆነ። ማንኛውም ሰው ቢሆን ራሱን እያደነቀና እርሱኑኑን በመስታወት እያየ ከመኖር የበለጠ የሚያስደስተው ነገር የለም።

ፋንቲን ከልጅዋ ከኮዜት በስተቀር ሁሉም ነገር ረሳች። አንዲት ትንሽ ክፍል ተከራይታ ስለነበር የወር ደመወዝዋን በቅድሚያ በብድር መልክ ወስዳ ክፍልዋን በሚገባ አጋጌጠችት። የጠዋት ማታ ሕልምዋ ግን ልጅዋን የማየት ምኞት ስለነበር ወደፊት ምን ሊሆን እንደሚችል በአላብ በታያት ጊዜ በደስታ ፈነደቀች። ሆኖም 'ባል አግብቼ ነበር' ብላ ለመናገር ስለማትችል ስለልጅዋ ሰው ፊት ላለማንሳት ተጠነቀቀች። ሰዎች ይህን ካወቁ 'ጋለሞታ' እያሉ ስምዋን ሊያጠፉ እንደሚችሉ ታውቃለች።

ቀደም ሲል እንደ ተጻፈው ልጅዋን ላስጠጉላት ሰዎች ቃል የገባችበትን ገንዘብ በየወሩ ሳታጓድል ትልካለች። ለልጅዋም አዘውትራ ደብዳቤ ትጽፍላታለች። ስምዋን ከመፈረም በስተቀር መጻፍ ስለማትችል ግን ለልጅዋ ደብዳቤ በሌላ ሰው ነበር የምታጽፈው። በመሥሪያ ቤትዋ አካባቢ 'ፋንቲን ብዙ ደብዳቤ ትጽፋለች። የምትጽፍለትና የሚጽፍላት ወዴጅ አላት ግለት ነው' እየተባለ ብዙ ተወራ። ስለዚህ ተከታታይዋ በዛ። መልክዋ በተለይም ፀጉርዋና ጥርሶችዋ እጅግ ማራኪ ስለነበሩ የሚቀናባትም አልታጣም። በአማካይ በየወሩ ሁለት ጊዜ ደብዳቤ እንደምትጽፍና የምትጸፈው ደብዳቤም ለተመሰሳይ ሰው እንደምትልክ የሥራ ባልደረቦችዋ ደረሱበት። ከጊዜ በኋላም የምትልክበት አድራሻንም ጭምር አወቁ። ከእለታት በአንዱ ቀን ደብዳቤዎችዋን የሚጽፍላት ሽማግሌ ከመጠጥ ቤት አግኝተውት በሞቅታ ሁሉንም ነገራቸው። በዚህም ፋንቲን ልጅ እንዳላት ቡተሰማ ጊዜ 'አንዳንድ ሴቶች የትም የትም እያሉ ሲዘሉና ሲቀብጡ ልጅ ይቀፈቅፋሉ፣ ፋንቲንም የዚህ ዓይነት ሴት ናት' እያሉ አሟት።

ፋንቲን ከፋብሪካው ውስጥ ሥራ ከጀመረች አንድ ዓመት ገደማ ሲሆናት አንድ ቀን ጠዋት እርስዋ ትሠራበት የነበረው ክፍል ተቆጣጣሪ ሃምላ ፍራንክ ትሰጣታለች። ገንዘቡን ለምን ብላ እንደሰጠቻት ስትጠይቅት ከዚያን እለት ጀምሮ ከሥራ የተሰናበተችና ገንዘቡም ለመላፈሪያ እንዲረዳት ታስቦ የተሰጣት መሆኑን ትገልጽላታለች። ፋንቲን ከንፍዋ እንደተመታች ዶሮ ደርቃ ቀረች። መልስ ለመስጠት ኃይል አልነበራትም።

ያልተከፈለ የቤት ኪራይ እዳ ስለነበረባትና እንዳንድ እቃም በዱቤ ገዝታ ስለነበር ከተማውን ለቅቃ ለመሄድ አትችልም። አገሩን ለቅቃ ከመሄድዋ በፊት የነበረባትን እዳ መክፈል አለባት። እዳዋ ከሃምሳ ፍራንክ ይበልጣል። ግራ ሲገባት ምን እንዳለች ሳታውቅ ብዙ ተናገረች። ተቆጭጣሪዋ ሴት ቢቃል ሳትመልስላት ወደ ቤትዋ እንድትሄድ በምልክት ነገረቻት። ፋንቲን እፍራና ተከዛ ከፋብሪካው ግቢ ወጥታ ሄደች። ጥፋትዋ ምን እንደ ነበር ግን ሁሉም ሰው አውቋል። ወንጀልዋ ለሌሎች ሴቶች አርአያ የምትሆን ጋለሞታ ሴት መሆንዋ ነበር። ዋናው ምክንያት ግን ኑናት እንደ ነበር ብዙ ሰው ጠርጥሯል። በነገሩ የተጠራጠሩ ሰዎች ከንቲባውን እንድታነጋገር መከርዋት። ነገር ግን ከንቲባው ሃምሳ ፍራንክ ተሰጥቷት ከሥራ እንድትባረር መፍቀዱንና ገንዘቡን የሰጥዋትም ከንቲባው ደግ ሰው ስለሆኑ እንጂ ያለ ዳረጎት ሊያባርራት ይችሉ እንደ ነበር ሙታለች። 'በገዛ ፋብሪካውስ ማን ሊያዝዘው ይችላል' ብሎ በማሰላሰልና 'ከጂያ በኋላስ ማነጋገር ምን ያስፈልጋል' በሚል ወደ ከንቲባው ሳትሄድ ቀረች። ሆኖም ከንቲባው ስለፋንቲን ከሥራ መባረር የሚያውቀው ነገር አልነበረም። ብዙ ጊዜ አስተዋይ አስተዳዳሪዎች ሥልጣንን በውክልና ለማመልከታቸው ግስተላለፍ እንደ ግዴታ ይቆጥሩታል። ውክልናውን መቼታ በማድረግ ነበር ተቆጣጣሪዋ ራሰዋን ከላሽ፣ ዳኛና ፍርድ አስፈጻሚ በማድረግ በፋንቲን ላይ የፈረደችውና ከሥራም ያባረረቻት።

ፋንቲን በአሰሪችብት እነዛቢ በግርድና ተቆጥራ ለመሥራት ፈልጋ ከዚት ቢት እየኮረች ሥራ ፈለገች። ማንም ሊቀጥራት አልፈለገም። የቤት እቃዎችዋን የገዛችው ውራጅ ከሚሸጥ ባለሱቅ ስለነበር 'እዳሽን ሳትከፍዪ ከአገር ብትጠፊ ለፖሊስ ነግሬ ካለሽበት አሊዝንለሁ' ሲል ዛተባት። ቤት እስራይዋ ግን 'ውሳት ነሽ። ከዚህም በላይ ቆንጆ ስለሆንሽ ያለብሽን የቤት ኪራይ እዳ መክፈል እያትትሽም' ስትል አበረታታቻት።

ከተቀበለችው የምሳ ፍራንክ ግማሹን ለውራጅ እቃ ሻጭ፣ ከፈሉን ቤት ኳሪተዎች ሴት ከፈለች። የእቃው እዳ ብዙ ስለነበር ለጊዜው በጣም የሚያስፈልጓትን ብቻ አሰቀርታ ሦስት አራተኛ ገደማ የሚሆነውን እቃ ለሰጪው መለሰች። እቃው ሲመለስ የሚቀርባት እዳ ወደ አንድ መቶ ፍራንክ ሆነ። ጉረቤትዋ የሰሩ ወታደሮች ልብስ ያሳጥቧት ስለነበር ከዚያ የምታገኘው ገቢ ቀሞ ለመሄድ የሚያስችል ሰንቅ መግዛ አደረገችው። ሠሙሩ ስለቆዋ ትልቁው የሰረውን ገንዘብ ለመላክ ግን አልቻለችም።

ወደ ትውልደ አገርዋ በተመለሰችበት አለት ማደሪያ የሰጠቻት እሮጊት ተቀጥሮ መኖር እንዴት እንደሚቻል ትምህርትና ምክር ስለሰጠቻት ለአሁኑ ሄ

ኑሮዋ የጨለማ መብራት ሆነላት። በመጠኑ ዋለቱና ትንሽ ክ አላቅቆት ሙናር መቻል የችገር ሁለት ገጽታዎች እንደሆኑ አሰረድታት ነበር። «የመጀመሪያው ገጽታ ስሙር ሲሆን ሁለተኛውም እንደ ዉስጥ ብላ ነበር የነገረቻት። ስለዚህ ፋንቲን በዉጨለማ ያለ መብራት መኖር በቀላሉ ለመደችው። የምትቀመስውን እራት ከጉረቤት መሰከት በማጣ የብርሃን ውጋገን እየተጠቀመች ነበር የምትጉርሰው። የምትቀምሰው እራት ከሌላትም ለጓይን ያዘ ሲያደርግ ጥቅል ብላ ትተኛለች።

ምክር የለገሰቻት አሮጊት ሩሀሩህ ሴት ስትሆን ስምዋ ግርጋሬት ይባላል። ይህቺ ሴት ድሃ ብትሆንም ለተቸገረ አዛኝ፣ ቤተ ክርስቲያን የምታዘወትር ጽኑ አማኝ፣ ምፅዋት መስጠት የሚያስደስታትና ስምዋን ከመፈራም በስተቀር ማንበብና መጻፍ የማትችል ሴት ናት። እንዲህ ያለው ደግነትና ጽኑ እምነት የኑሮ ደረጃቸው ዝቅ ካለ ሰዎች መካከል በገፍ ስለሚገኝ ነገሩ እጅግ ያስገርማል። እነዚህ ሰዎች እንዲ ሲከፋቸው፣ እንዴም ሲደሰቱ ነው የሚኖሩት። ሰዎቹ በነገ በጣም ያምናሉ።

ፋንቲን በመጀመሪያ እጅግ በጣም አፍራ ለተወሰኑ ቀናት ከክፍልዋ ሳትወጣ ከቤትዋ ውስጥ ቁጭ አለች። ከቤትዋ ከወጣች ሰዎች ከኋላ ኋላዋ እያተከተሉ ጣት በመቀሰር የሚሳለቁባት መሰላት። እውነትም ከቤትዋ በወጣች ቁጥር ሰዉ ሁሉ በማፍጠጥ ያያታል እንጂ የእሜር ሰላምታ አያሰጣትም። ስለዚህ መንገደኛው ሁሉ በክፉ ዓይን ሲያያት መጥፎ ሰሜት እደረባት። ይህም ሶሜትዋ እንደ ጥቅምት ብርድ አካልዋን በስቶና አጥንትዋን ሰርስሮ ከፉኛ አስጨነቃት።

ፋንቲን ባዶ እጅዋን የቀረች ድሃ በመሆንዋ ሌሎች እንዲያከብሯ ትና እንዲወድዋት መጠበቅ አልነበረባትም። ድሃን ማነው የሚወድደው፣ ፋንቲን ይህን የመሰለ የሕይወት እውነታ አልተከነዘችም። ከቀን በኋላ ግን ያው ሕይወት ስላስተማራት በነገሩ ደረስችበት። ከሦስት ወር በኋላ ምንተ-እፍረትዋን ከገሊናዋ ሰላስወጣች ያለ ማፈር ወደ እደባይ ትወጣ ጀመር። 'ለእኔ እንደሆነ ሁሉም ያው ነው' ትላለች እርስ በራስዋ ስትነጋገር። ፋንቲን እንዳልተሟላለት ገበሬ ብዙ ትለፈልፋለች። የምታገኘው መልስ ግን እጅግ አነስተኛ ነው። ብዙ ሳትበላ ብዙ በመልፋትዋና እካልዋ ዝሎ ሰበሽታ በመዳረጉ ሳል ይዛ እጣደፋት። እንዳንዴ ጉረቤትዋ ማርጋሬትን እየጠራች 'ሰውነቴ እንዴት ብሎ እንደ ጋለ እዳው እስኮ' እያለች ታሰለቻታለች። ቢሆንም ጠዋት ጠዋት ዞማ ፀጉርዋን በእባራ ማዘጠ ሪያ ሲታባዋረውና ደረጃ እያበጀ ስታየው ስለሚያረካት ትደሰትበታለች። ባልምትደሰትበትና ስለሚያረካትም እሳጥራ አትቁርጠውም።

ክረምት ሊገባደድ ሲል ነበር ፋንቲን ከሥራ የተባረረችው። አሁን ግን የበጋ ወራት ተገባድዶ ዳግም ክረምት ሊገባ ተቃርቧል። ክረምት ሲገባ ደግሞ ሁሉም ነገር ሞልምልም ይላል። ብርዱም አጥንት ይሰርስራል። የሰው ልብም እንደ ብርዱ ይቀዘቅዛል። ይህ ሁሉ ታዲያ ለፋንቲን ቀላል አልነበረም። ከዚህም ሌላ 'በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ' እንዲሉ ባለሀብቶችም «ያለብሽን እዳ ከፈዪ እንጂ!» እያሉ ጨቀጨቁዋት። ፋንቲን ብዙ ብትለፋም የምታገኘው ገንዘብ መጠነኛ ስለነበር እዳዋ እየጨመረ ሄደ እንጂ አልተቀነሰም። ልጅዋን ያስጠጉላት ሰዎች ለረጅም ጊዜ ስላልተከፈላቸው ደብዳቤ እየደጋገሙ ይጽፉላታል። ደብዳቤያቸው ውስጥ የሚጠቀሙባቸው ቃላት ልብን የሚያቄስሉና አጥንት የሚሰብሩ ነበሩ። በአንድ በተወሰነ ቀን የደረሳት ደብዳቤ እጅግ አስከፊ ሆኖ አገኘችው።

«ኮዜት ልብሶችዋ አልቀው ራቁትዋን ነው የምትሄደው ለማለት ይቻላል። መጪው ክረምት ስለሆነ ቢያንስ አሥር ፍራንክ በአስቸኳይ ላኪና የሚሞቅ ልብስ ይገዛላት።» ደብዳቤውን አንብባ እንደ ጨረሰች ወረቀቱን ጨምድዳና በመዳፍዋ ጨብጣ ቀኑን በሙሉ ያዘችው። ወደ ማታ ፀጉር ቤት ሄዳ በምናምን ተጠቅልሉ የነበረውን ፀጉርዋ ወደ ታች ስትለቀቀው ተንዠርገግ ከኋላዋ ተንጠለጠለ።

«እንዴ! እንዴት ያለ የሚያምር ፀጉር ነው ያለሽ?» ብሎ ፀጉር ሠሪ ሲጠይቃት «ቆርጠህ ብትወስደው ምን ያህል ትከፍለኛለህ?» አለችው።

«አሥር ፍራንክ» ሲላት «ቁረጠው» ስትል ተናገረች አንጀት በሚበላ ድምፅ። በገንዘቡ ወፈር ያለ ቀሚስ ገዝታ ለልጅዋ ላከችላት። ባልና ሚስት ግን በጣም ተናደዱ። እነርሱ ጥሬ ገንዘቡን ነበር የፈለጉት። ቀሚሱን ለራሳቸው ልጅ ለኢፖኒን ሰጥዋት። ምስኪንዋ ኮዜት፣ የከረምቱን ብርድ የተቦጫጨቀ ጨርቅ ለብሳ አሳለፈች። እናት ግን 'አሁን ልጄ ትንሽ ይሞቃታል! የሚያምረው ፀጉሬን ሽጬ አለበሰኪት' ስትል አሰላሰለች።

የተቆረጠው ፀጉርዋ እንዳይታይ በጨርቅ ሸፈነችው። ደግነቱ ያም ሆኖ አላስጠላባትም። ልብዋ ውስጥ ግን የሆነ መጥፎ ስሜት ማሳደሩ አልቀረም። አሳፋ አገዳሚው ሁሉ ስላስጠላት ሰዉን ሁሉ እንደ ጠላት ታይ ጀመር። ለመሬይ ማንደላይን ግን የተለየ ስሜት ነበራት። ሆኖም እርሱም ቢሆን ከሥራ ያባረራትና ኑሮዋን ያበላሸባት ሰው ስለሆነ ለእርሱም የነበራት አክብሮትና የተለየ ስሜት ከጊዜ በኋላ ሟሸሸ።

ሠራተኛ ከሥራ ሲወጣ ባጋጣሚ በፋብሪካው አካባቢ ካለፈች ያበደች ለማስመሰል ትስቃለች፣ ጮክ እያለች ትዘፍናለች። በዚህ ጊዜ ፋብሪካው

ውስጥ ትሠራ የነበረች አንዲት ሴት 'የዚህች ልጅ መጨረሻ አያምርም' ስትል ተነበየች።

ፋንቲን በልጅነት አፍላ ዘመንዋ የሆነ ወሮበላ 'ወደደኩሽ' ብሎ ሲቀርባት፣ ልብዋ ውስጥ ፍቅር ባይኖርም 'ለጊዜ ማሳለፊያ' በሚል ለተወሰነ ጊዜ አብራው ዘለለች። ይህ ሰው የማይረባ ዱርዬ ስለነበር በየቀኑ ግታ ግታ ይደበድባታል፣ ይረግጣታል፣ የማያደርጋት ነገር የለም። በመጨረሻ ልጅ አስታቅፏት ከአገር ጠፋ። ጥሎአት በመጥፋቱ በጣም ጠላችው። ልጅዋን ግን እንደ አምላክ አመለከቻት፣ ከልብም ወደደቻት። ችግር እየጠናባትና ብቸኝነት እየተቈራኛት በሄደ ቁጥር የልጅዋ ፍቅር ግለት ይበረታል። ሰው ሁሉ ሲሸሻት በዓለም ላይ የቀረቻትና የእኔ ናት የምትላት ኮዜት ብቻ መሆንዋ ሲታወሳት «ሀብታም ስሆንና ሲያልፍልኝ ኮዜትዬ ከጉኔ ትሆናለች፣ አብረንም እንኖራለን» በማለት ራስዋን ታዝናናለች። አሳብዋ በአሳብ ሲታያት የተኰሳተረው ፊትዋ ይፈካል። ሆኖም በሽታዋ እየጠናባት ስለሄደ ማታ ማታ ከመጠን በላይ ትሰላለች። አንድ ቀን በጠዋቱ እንግሪርና ሚስስ ቴናድዬ የጻፉላት ደብዳቤ ደረሳት። ደብዳቤው መርዶ ይዞ ነበር የመጣው።

«ስፈራችን ተስቦ ገብቷል፣ ኮዜትም በጠና ታምማለች። የመድኃኒት ዋጋ ደግሞ ንሯል፣ እየገደለን ነው። ከአሁን በኋላ ለመድኃኒት መግዣ የሚሆን ገንዘብ የለንም። በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ አርባ ፍራንክ ካላከሽልን ኮዜት መሞትዋ ነው።»

ፋንቲን ደብዳቤውን ካነበበች በኋላ ከት ብላ ሳቀች። ወደ ጐረቤትዋ ሄዳም የምፀትና የቁጭት ንግግር ተናገረች። «ይገርማል! በጣም ጥሩ ሰዎች ናቸው። አይደሉም? እ...አርባ ፍራንክ! ያሰቡት እስቲ! የቁሻር አጠያየቅ አይደል! ገንዘብ ከየት የሚመጣ ይመስላቸዋል? ደደብ፣ የቀን ጅቦች አይደሉም?»

ወደ መስኮት ተጠግታ ደብዳቤውን እንደገና አነበበችው። ከአጭር ጊዜ ቈይታ በኋላ ወደ ምድር ቤት ወረደች። ከጐረቤትዋ ቤት ወጥታ መንገዱን ተያያዘችው። ሮጠች፣ ዘለለች፣ ከት ከት ብላም ሳቀች። እንደ ግበድም አደረጋት። አካል ሲቃወስ ወይም ችግር ሲበዛ አይደል እብደት የሚከተለው! ከአደባባይ ስትደርስ ብዙ ሰው ተሰብስቦ አየች። ሰዉ የተሰበሰበው ከአንድ ጋሪ ዙሪያ ሲሆን ቀይ ልብስ የለበሰ ሰው ከጋሪው ላይ ወጥቶ ይለፈልፋል። የጥርስ ሐኪም ነበር። የሐኪሙ የአለት ተአለት ተግባር ከአገር አገር እየዞረ ጥርስን ማከም ሲሆን አሁንም ጥርሱን ያመመው ካለ እያጠያየቀ ነበር።

ፋንቲን ከሕዝቡ ጋር ተቀላቀለች:: ወዲያው ብዙም ሳትቆይ ሳቅዋን ለቀቀችው:: ሐኪሙ ጥርስ እያወለቀ ነበርና ሥራውን ቆም አድርጎ ቀና ሲል ፋንቲንን አያት:: «አንቺ እንዴት ያሉ የሚያማምሩ ጥርሶች ናቸው ያሉሽ» ሲል ሐኪሙ ጮክ ብሎ ተናገረ:: «ከወተት የነጡ ናቸው እኮ! እነዚያን የሚያማምሩ ሁለቱ የፊት ጥርሶችሽን ብትሰጪኝ አርባ ፍራንክ እከፍልሻለሁ» ባላት ጊዜ «ምንድነው የሚለው? የፊት ጥርሶችሽን ነው ያለው?» ስትል ፋንቲን ጠየቀች::

«ሁለቱ የፊት ጥርሶችሽ» አለ ሐኪሙ:: «የላይኛዎቹ ማለቴ ነው፣ እነርሱን ብትሸጪልኝ?» ብሎ ሲጠይቃት «የሚገርም እኮ ነው» ስትል ፋንቲን ተናገረች:: ጥርሳቸው የወለቀ አሮጊት «አይገርምም፤ ለጥርስ ነው አርባ ፍራንክ እከፍላለሁ ያለው?» ሲሉ ጠየቁ በመገረም:: «ልጅትዋ እድለኛ ናት::»

የሐኪሙን ቀጣይ ንግግር ላለመስማት ፋንቲን እየሮጠች ሄደች:: ሐኪሙ ግን ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ:: «ብዙ ገንዘብ ነው የሰጠሁሽ:: ገንዘቡ ይጠቅምሻል:: አሳብሽን ከለወጥሽ ወደ ማታ ቲሳክ ሆቴል ብቅ በይ፣ ከዚያ ታገኚኛለሽ::»

ፋንቲን ወደ ቤትዋ ተመለሰች:: እየሮጠች ነበርና የሄደችው ትንፋሽ አጥሯታል:: የሆነውን ለወዳጅዋ ለማርጋሬት ስትነግራት «ምን ልስጥሽ ነው ያለው» ብላ ስጠይቃት «አርባ ፍራንክ» አለቻት::

«አርባ ፍራንክ ነው ያልሽው?» በማለት ዳግም ስትጠይቃት «አዎን አርባ» ስትል መለሰች:: ፋንቲን ይህንኑ እያሰላሰለች ወደ ሥራዋ ሄደች:: ከሩብ ሰዓት በኋላ ሥራዋን አቁማ ደብዳቤውን ለማንበብ መስኮት ወዳለበት ተጠጋች:: ደብዳቤውን አንብባ እንደ ጨረሰች ወደ ወዳጅዋ ዞር ብላ «ስለተሰበ በሽታ የምታውቂው ነገር አለ?» ስትል ጠየቀቻት::

«ያው በሽታ ነዋ!» በማለት መለሰችላት::

«ልጆችን ይተናኩሳል?» ብላ ስትጠይቅም «በተለይ ልጆችን በጣም ይጉዳል» አለቻት:: ከዚያም አያይዛ «ሊገድላቸው ይችላል?» ብላ ስትጠይቅ «ብዙ ጊዜ» አለች ጓደኛዋ:: ፋንቲን ደብዳቤውን እንደገና ለማንበብ ወደ መስኮት ጠጋ አለች:: ወደ ማታ በጊዜ ከቤትዋ ወጥታ ሐኪሙ ወደ ነገራት ሆቴል ቤት አመራች::

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ገና ጎሕ ሳይቀድ ወ/ሮ ማርጋሬት ወደ ፋንቲን ክፍል ሄደች:: ብዙ ጊዜ አብረው ነበር የሚያመሹት:: በዋዜማው

ግን አብረው ስላላመሹና ዘወትር ወደ ሥራም የሚጓዙት አብረው ስለሆነ ነበር ከፋንቲን ክፍል የሄደችው:: ፋንቲን ከደረቅ የእንጨት ወንበር ላይ ተቀምጣለች:: ፊትዋ ገርጥቷል፣ ዓይኖችዋም እምባ አቅርረዋል:: ሌሊቱን በሙሉ እንቅልፍ አልወሰዳትም:: ሻሽዋ ከጉልበትዋ ላይ ወድቋል:: ወ/ሮ ማርጋሬት ገና ስታያት ከፋኖ ደነገጠች::

«ምነው? ምን ሆንሽ? ሌሊቱን በሙሉ ሳትተኚ ነው እንዴ ያደርሽው?» ብላ ጠይቃ ፋንቲንን ከእግር እስከ ራስ ፀጉር አጤነቻት:: ፋንቲን ፊትዋን ቀና አደረገች:: በአንድ ቀን ከአድሜዋ አስር ዓመት የጨመረች መሰለች::

«ምንም አልሆንኩም» አለች ፋንቲን:: «እንዲያውም ደስ ነው ያለኝ:: አሁን ልጄ ላትሞት ነው:: መንፈሴ ሁሉ የረካ ነው የመሰለኝ::» ይህን እንዳለች ከጥርስዋ ሽያጭ እጅዋ የገባውን ገንዘብ ለአሮጊትዋ አሳየቻት::

«የሥላሴ ያለህ!» ስትል ጮኸች ወ/ሮ ማርጋሬት:: «ይህ ሁሉ ገንዘብ ከየት መጣ? ከሰማይ ነው የወረደው? ወይስ ከምድር ፈለቀ?»

«ከየትም ይሁን የት፣ ገንዘቡን አግኝቼዋለሁ» አለች ፋንቲን ፈገግ ብላና የኩራት ስሜት እየተሰማት:: ሆኖም ፈገግታዋ ዓይንን የሚያሸሽ እንጂ የሚስብ አልነበረም:: ከንፈሮችዋ በደረቀ ደም ተበክለዋል:: ወላቃዋም ጉልህ ሆኖ ይታያል:: ሁለቱ የፊት ጥርሶችዋ ተነቅለዋል፤ ጥርሶችዋ የወጡበት ቀዳዳም በቅጡ አልተደፈነም::

አርባውን ፍራንክ ለልጅዋ አሳዳጊዎች ላከችው:: ሚ/ርና ሚስስ ቴናርዬ ገንዘብ ለማግኘት የፈጠሩት ዘዴ ነበር እንጂ በአገሩ ተስቦም አልገባ፣ ከዚህም በመስኮት ወደ ውጭ ወረወረችው::

ባለእዳዎችዋ እጅግ እየጨከኑባት ሄዱ:: ያገለገሉ እቃዎችን የሚሸጡ ሰውዬ ባገኘዋት ቁጥር «አንቺ እድለቢስ፣ ገንዘቤን አትከፍይም?» እያሉ ይሰድቧታል፣ ይጨቀጭቋታል:: ምን አድርጊ ነው የሚልዋት! ፋንቲን እንደሆነ እንኳን እዳዋን ልትከፍል ለሆድዋም ስላልሞላላት ብዙውን ጊዜ ጦምዋን ስለምታድር ከሰውነት ወጥታለች:: ልጅዋን የሚያሳድጉላት ባልና ሚስት ሌላ ደብዳቤ ጻፉላት::

«ከዜት ከበሽታዋ ድና በማገገም ላይ ነች:: ነገር ግን እስክ ዛሬ የተጠራቀመውን አንድ መቶ ፍራንክ አሁኑኑ ካልላክሽልን ከቤት አስወጥተን መንገድ ላይ እንጥላታለን::»

«መቶ ፍራንክ! አሁን ደግሞ ይህን ያህል ገንዘብ ከየት ይሆን የማመጣው? ይሁና! የተቀሩት ጥርሶቼን እሸጣለሁ!» አለች ኑሮዋ እያንገሸገሻት። እድለቢስዋ ፋንቲን የሰው ሁሉ መዘባበቻና መሳለቂያ ሆነች።

3

የፋንቲን ታሪክ ምን ዓይነት ታሪክ ነው! ያሸከር ታሪክ! ወይስ አሸከርን የሚገዛው ጎብረተሰብ ታሪክ? አሸከሩን ከማን የሚገዛው? ምናልባትም ከችግር? ከመከራ? ከስቃይ? ከረሃብ? ከብቸኝነት? ከተስፋ መቁረጥ? የሚቀፍና የሚሰቀጥጥ ግገር! ኑፍስ በዳቦ ሲለወጥ! ሰዎች ያልፈቀዱትንና ያልፈለጉትን እንዲሠሩ ችግር ሲያስገድዳቸው! በግዳጅ የሚያደርጉትን ጎብረተሰቡ በደስታ ሲቀበለው! አይገርምም! ባርነት ቀርቷል ይላሉ። ጨርሶ ውሸት ነው። ባርነት አልቀረም፣ ዛሬም አለ። በአሁኑ ጊዜ ጉልቶ የሚታየው ሴቶች ላይ ነው። ስሙን ቀይረው 'ዝሙት አዳሪ' ይሉታል።

እስካሁን ባየነው ድራማ ፋንቲን ቀደም ሲል የነበራትን ሁሉ አሟጥጣ ስለጨረሰች የቀራት ነገር አልነበረም። ከብርም፣ ስምም፣ እናትነትም፣ ውበትም፣ ምኑ ቅጡ ሁሉም ነገር ሄዷል። ቢነኳት አካልዋ እንደ በረዶ ይቀዘቅዛል። ስሜትዋም ስለደነዘዘ ሞቶ ተቀብሯል። ያለ ይሉኝታ የፈለገቸውን ታደርጋለች። እያወቀች አታውቅም፣ እየሰማች አትሰማም። የተከሩን ፊት አንግባ፣ ሆድ የባሰውን ልብ ተሸከማ፣ እያየ የማያይ ዓይን ሰክታ፣ እየሰማ የማይሰማ ጆሮ አንጠልጥላ፣ ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርጋ ትታ እየቀረፋት ትኖራለች። ተስፋ ሲቆርጡ ይኸው ነው የሚሆነው።

ጎብረሰቡም ሆነ ሕይወት ከፋንቲን ጋር የነበረውን ግኑኝነት አቋረጠ። እሷም ለምንም ነገር ደንታ አጣች። ሊደርስባት የሚችል መጥፎ ነገር ሁሉ ተግታዋለች። ቢሆንም ለመሸከም የምትችለውን ሁሉ ተሸከመች። ሁሉንም ነገር አየችው። ለደረሰባት ነገር ሁሉ እምባ በገፍ አውጥታ አነባችለት። አለችው፣ አለችውና 'ታዲያ አሁን ምን ይሁን? ምን ይጠበስ?' ከሚል ድምዳሜ ላይ ደረሰች። ለዚህ ነው ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርጋ የተወችው። ምኞትና ድሎት ችግርን ስለማያውቁት እንደማይጨነቁለትና እንዲሁም ሕሳን ልጅ ሞት እንቅልፍ መሰሉት ዝም እንደማል እርስዋም ምንም ነገር እንዳልሆነ ቁጥራ ችግር አልተው ቢላት እርስዋ ተወችው። ስለዚህ የምትፈራውና የምትሸሸው ነገር ከፊትዋ አልተጋረጠም። ደመና ቢያጠልልባት፣ ውቅያኖስ ቢደፋባት ምን ደንታ አላት! የኑሮዋ ሰፍነግ እንደሆነ ከሚመጥጠው በላይ ሞልቶ ፈሷል። ፋንቲን የደረሰችበት እምነትና

ድምዳሜ ይኸው ሆነ። ሆኖም ግን እርስዋ ተሳሳታለች። ግኑው መጪረሻውን የሚያውቅ? ዛሬ እንዴት ብሎ እንደሚያልፍ፣ ነገ ደግሞ እንዴት ሆኖ እንደሚመጣ ማን ያውቃል? ሁሉንም የሚያውቅ ፈጣሪ ብቻ ነው።

በትንሽ ገቢ እንደ ሀብታም የሚንቀባረሩ፣ ሳይኖራቸው ሀብታም፣ ሳይማሩ ተመራማሪ፣ ያልሆኑትን ለመሆን ሞካሪ፣ ቡና ቤት ሲገቡ የሚጀነኑ፣ ሲጃራ ሲያጭሱ የሚወጠሩ፣ ሸሚዝ መጠቅለል የሚቀናቸው፣ የጫማ ተረከዝ የሚያስረዝሙ፣ አላፊ አግዳሚውን የሚለክፉ፣ 'እሺ ቅጂ እባክሽ' እያሉ የሚፎልሉ፣ ሳይነኩ የሚነጫነጩና መቼስ ጉራቸው አያድርስ የሚያሰኙ አንዳንድ ልባቸው ያበጠባቸው ጉረምሶች ትናንሽ ከተሞች ውስጥ በብዛት ይታያሉ። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የትም አሉ። በተለይ ግን በእድሜ ሲገፉ እየደደቡ የሚሄዱና በአንጎላቸው ሳይሆን በቂጣቸው የሚያስቡ ሞልተዋል።

በ1823 ዓ.ም. ይህን መሳይ ጠባይ የነበረው አውደልዳይ፣ ጉፈሬ ብርቁና ዘመናዊ መስሎ በሰው ስቃይ የሚደሰት ጉረምሳ ነበር። ይህ ጉረምሳ ሰው ከተሰበሰበት ቡና ቤት ውስጥ ላይ ታች የምትለዋንና ኑሮ ያጉሳቀላትን፣ እንዲሁም የማይሆን ልብስ የለበሰችውንና ክቡር ገላዋን ለጉረምሳ አሳልፋ የምትሸጠዋን ሴት ደጋግሞ ይለከፋል። እንደ ልማዱ አንድ ቀን ፋንቲን ከመንገድ ላይ ወጥታ ስትንሸራሸር ከፉኛ በመልከፍ ያበሳጫታል። ሆኖም እርሷ ግን እንዳልሰማ ሁና ዝም አለችው። ሲጃራ ማጨስ ለጉረምሳው ፋሽን ነውና በአጠገቡ ስታልፍ ሲጃራውን በኃይል ምጎ የሲጃራውን ጭስ አቦነባት። ከዚያም ከወዲያ ወዲህ እያለች በአጠገቡ ባለፈች ቁጥር «የማን ናት ፋንታ! ኡኡቴ! የምን መኩሳተር ነው!። ለመሆኑ ጥርስ አልጠፋብሽም?» እያለ ሌላም ሌላም ስድብ በማከል ያንቋሸሻታል።

ሊያነጋራት ሲሞክር ፋንቲን ቀና ብላ እንኳን አታየውም። እንዲያውም ከናካቴው በአጠገቡ ባለፈች ቁጥር ቅጣት እንደ ተወሰነባት ወታደር ከወዲያ ወዲህ ሳትገላመጥ ቀጥ ብላ ነበር የምትጓዘው። ከወዲያ ወዲህ እያለች በመራመድ ወደፊት ትሄድና ተመልሳ ትመጣለች። በዚህ ጊዜ ጉረምሳው ደጋግሞ ቢለከፋትም ዝም ስላለችው በጣም ይናደዳል። ስለዚህ በመጪረሻ ከመንገድ ላይ ተቆልሎ ከነበረው በረዶ አፍሶ ያነሳና ጀርባዋን ይመታታል። ይህን ጊዜ ልክ እንደ ነብር ዘልላ አንገቱ ላይ በጠምጠም እነቀችው። ቀጥላም በጥፍሮችዋ ፊቱን በኃይል በመቧጠጥ ከፋኛ አደማችው። ድምፅ የገ ከፍ አድርጋ ሰምቶት የማያውቅ የስድብ ናዳም አወረደችበት። ጩኸትዋ ብርቱ ስለነበረ በአካባቢው ከነበረው ሻይ ቤት የነበሩ ሰዎች ሁሉ ስለሰምዋት 'ምን ተፈጠረ' በሚል ወደ ውጭ ወጡ። ቀስ እያለም ከሻይ ቤቱ ከወጡ ሰዎች ሌላ 'ለወሬ ሞትኩ' በሚል መንገደኛው ሁሉ ጉዞውን

ገትቶ ስለቆመ ብዙ ሕዝብ ተሰበሰበ። ጐረምሳው 'አልሞት ባይ ተገዳይ' በሚል ስሜት ከሚቢጥጠው ጥፍር ለመከላከል የሚቻለውን ሁሉ አደረገ። የተሰበሰበው ሕዝብም 'ብራቮ፣ ብራቮ' እያለ ጮኸ፣ ሳቀ፣ አጨበጨበ። ፋንቲን በጥፍር መኪጠጥ ብቻ ሳይሆን ጐረምሳውን በጥፊ ታጮለዋለች፣ በእርግጫም እየረገጠች ታጣድፈዋለች። ተሰፋ የቆረጠ ሰው ጉልበት ከየት እንደሚያገኝ አይታወቅም።

ድንገት አንድ ረጅም ሰውዬ ከየት እንደ መጣ ሳይታወቅ ብቅ ብሉ በቁጣ የቦካውን ወገብዋ በመያዝ «በይ ተከተዪኝ» ሲላት ፋንቲን አንገትዋን ቀና አደረገች። የጋለው ስውነትዋ በድንገት እንደ በረዶ ቀዘቀዘ። በንዴት የነደደው ድምፅዋም ዝቅ አለ። መላ ሰውነትዋ በፍርሃት ተውጠ መላ አካልዋ ተንቀጠቀጠ። የፖሊስ አዛዥ ጉቬር እንደሆነ አወቀች። በግርግሩ መኻል አወደልዳዩ ጐረምላ ሾልኮ ከዚያ ጠፋ። የተሰበሰበውን ሕዝብ ጉቬር በተነው። የጉቬር ቢሮ ከዚያ ሥፍራ ሩቅ ስላልነበረ ፋንቲንን እየጐተተ ወደ ቢሮው ወሰዳት። እርስዋም ብዙም ሳትከላከልና ቃል ሳትተነፍስ ተከተለችው። ሕዝብ ግን ሴትዮዋን ለእብደት በሚዳርግ ሰቆቃ በግሽግሽጥ አፈዘባት።

ከፖሊስ ጣቢያ እንደ ደረሱ ጉቬር በር ከፍቶ ፋንቲንን ወደ ውስጥ አስገባት። ቀጥሎም በሩን መልሶ ዘጋው። ፋንቲን እንደ ደነገጠና እንደ ፈራ ውሻ አሁንም ቃል ሳታሰማ ጥግ ይዛ ከወለሉ ላይ ቁጭ አለች። ሠበኛው መብራት አበራ። ጉቬር ከኪሱ ወረቀት አውጥቶ መጻፍ ጀመረ። የፖሊሱ አዛዥ ከሰተርተር ያለ ሰው በመሆኑ ፊቱ ላይ የመቅበጥበጥ ወይም ፈካ የማለት ምልክት አይታይበትም። ሕግን የማስከበር ጥማቱ የሚያረካበት ቅጽበት በመሆኑ ሥልጣኑን ለማሳየት ቋምጧል። ይህም በመሆኑ ስሜቱ በከፍተኛ መጠን ተነሳስቷል። የተቀመጠበት ወንበርና ቢሮው ትነሰለኛ ፍርድ የሚሰጥበት አካባቢ ለመሆኑ በጽኑ ያምናል።

ይህ ሰው ከላሼም፣ ጠበቃና ፍርድ ሰጪም ራሱ ስለሆነ የሴትዮዋን እድራጎት ባጤነ ቁጥር ወንጀለኛነትዋን አልተጠራጠረም። ከጤነኛ ሰው የማይጠበቅ ወንጀል ስትፈጽም በዓይኑ አይቷል። አንዲት ሴት አጸያ እንድን የተከፈረ የከተማ ነዋሪ ከሰው ፊት በአደባባይ ስትደበድብ ተመልክቷል። ለዚህ ወንጀል ጉቬር ራሱ የዓይን ምስክር ስለሆነ ከዚያ ሌላ ተጨማሪ ምስክር አላስፈለገውም። ስለዚህ ከወንበሩ ላይ ቁጭ ብሎ ሁኔታውን በዝርዝር መመዝገቡን ቀጠለ። ራፓሩን መዝግቦ ሲጨርስ ፊርማውን አኖረበት። ከዚያም የጻፈውን የአለት ሪፖርት ለዘበኛው ሰጠውና ተግረዱህ ሦስት ሰዎች ጨምርና ይህቺን ሴት ወደ ወህኒ ቤት

ውሰድዋት» አለው። ወደ ፋንቲን ዞር ብሉም «የስድስት ወር እስራት ተፈርዶብሻል» ሲላት እድለቢስዋ ሴት መላ ሰውነትዋ ተንቀጠቀጠ።

«ስድስት ወር! ወህኔ ቤት ውስጥ ስድስት ወር ልቆይ!» ካለች በኋላ በኃይል ተነፈሰች። «ልጄስ! ስድስት ወር በሙሉ ምን ልትሆን ነው? ወይኔ ልጄ! እስከ ዛሬ ለእንቴናድዬ ያልከፈልኩት ከመቶ ፍራንክ በላይ እዳ አለብኝ። ለመሆኑ ጌታዬ ይህን ያውቃሉ?» ስትል ጉቬርን ጠየቀችው። ከዚያም ከመሬት ላይ ወድቃ ተንፈራፈረች፣ ተንከባለለች። እነዚያ ሦስት ሰዎች ከአፈሩ ላይ እንደ ወደቀች ጉትተው ወደ ውጭ አወጥዋት።

«መሴይ ጉቬር ይማሩኝ፣ ይቅር ይበሉኝ» ስትል ጮኸች። «ምንም ዓይነት በደል አልፈጸምኩም፣ በእግዚአብሔር ሰም እምልሎታለሁ። ከመጀመሪያው ጀምሮ ከሥፍራው ቢኖሩ ኖሮ የሆነውን ሁሉ ያዩ ነበር። በፈጣሪ ስም እነግሮታለሁ፣ ሰውዬውን አልበደልኩትም። ይህን ሰው እኔ አላውቀውም። እርሱ ግን ከመሬት ተነስቶ በረዶ አፍሶ ነው የመታኝ። የሌላውን ሰው መብት ሳትነካ ከመንገድ ላይ የምትጓዘዋን ሴት የመምታት መብት ለዚህ ሰው ማን ሰጠው? ዝም ብሉ እኮ ነው በበረዶ የመታኝ። እስቲ ይፍረዱኝ! ያ እኮ ነው እኔን እብድ ያደረገኝ። እንደሚያዩኝ እኔም ጤነኛ አይደለሁም፤ ያመኛል። ሰውዬው በዚህ አላበቃም። 'እንቺ ወላቃ፣ እንቺ ዱርዬ' እያለም ሰድቦኛል። ጥርስ እንደሌለኝ አውቃለሁ፤ ቢሆንም ያስከፋኛል። ነገሩ ይህ ሆኖብኝ ነው እንጂ ሆን ብዬ ሌላውን ሰው ለመበደል ብዬ ያደረግኩት ነገር አይደለም። ሰውዬው ከመሬት ተነስቶ ነካካኝ እንጂ እኔ ላልደረስኩበትም። እርሱ ሲለፈልፍ ዝም ስላልኩት ነው በረዶ አንስቶ የመታኝ።

«ጌታዬ፣ ያልከፈልኩት የመቶ ፍራንክ እዳ አለብኝ። ያለብኝን እዳ ካልከፈልኩ ልጄን ከቤታቸው አስወጥተው ሜዳ ላይ ነው የሚጥሉብኝ። እባክዎ ስለልጄ ብለው ይራሩልኝ። አዩ ጌታዬ፣ ልጄን ከቤታቸው አስወጥተው መንገድ ከጣልዋት ራስዋን ለመጠበቅ የማትችል ሕፃን ልጅ ናት። ልጄን እኔ ካለሁበት እንዳላመጣት አቅሙም የለኝ፣ የሰው እዳም ከጭንቅላቴ ላይ ያንጥብባል! እንደሚያዩት ደግሞ ጊዜው ክረምት ነው። ታዲያ እኔ ምን ልሁን! ለጨቅላዋ ልጄ ይራሩላት፣ ይዘኑላት ጌታዬ። በእድሜ እሁን ከደረሰችበት ትንሽ ከፍ ያለች ብትሆን እንኳን እንደ ምንም ብላ ከወዲያ ወዲህ እያለች ራስዋን ለመርዳት ትችል ነበር። አሁን ባለችበት እድሜ ግን ይህን ለማድረግ አትችልም። ይራሩሉኝ፣ ይዘኑልኝ ጌታዬ» ስትል ቃልዋን በመደጋገም ለፈለፈች። ደግማና ደጋግማ መሬት ላመች። እጆችዋንም ወደ ሰማይ ዘረጋች። ጉንጮችዋ በአምባ እስኪርሱ አምርራ አለቀሰች።

ስውዬው ግን እንክች አላለም። ሆኖም መሪር ሀዘንዋና ጭንቀትዋ ከፊትዋ ላይ ጎልቶ ቢታይም ተፈጥሮ የቸራት የልጅነት ውበትዋን ሊያከስመው ስላልቻለ ከዚያ የነበሩ ሰዎች አተኩረው ሲመለከትዋት ቆንጆ ሴት ለመሆንዋ አላጡትም። ፋንቲን ተነስታ የአዛዡን ኮት ጫፍ ሳመች። ሁናቴዋ እንደ ድንጋይ የጠጠረና እንደ በረዶ የቀዘቀዘ ቢሆንም የፖሊሱን ልብ በቀላሉ ሊያሟሟና እንደ እንጨት የደረቀ ስሜቱን ሊያለዝበው አልቻለም። ዣቬር አልተበገረም።

«በይ ከዚህ ዞር በይ፣ አትለፍልፊብኝ» አለ ዣቬር። «ይበቃል፣ ምን ትነፈርቅብኛለች፣ መንገድሽን ቀጥይ። የስድስት ወር እስራት ተፈርዶብሻል። ክርስቶስ ቢመጣ እንኳን ይህን ውሳኔ ሊሽር አይችልም» ሲል በመጨረሻ የተናገራቸው ቃላት እጅግ አስደነገጣት— 'ክርስቶስ እንኳን ይህን ውሳኔ ሊሽር አይችልም'። አሁንም በድጋሚ መሬት ላይ ወድቃ እንደ ሕፃን ልጅ ተንፈራፈረች። አሁንም በድጋሚ 'ማሩኝ' ስትል ጮኸች። ዣቬር ግን ፊቱን አዞረ። ፖሊሶቹ ሁለት እጆችዋን ያዙ።

ሴትየዋ እንደዚያ ስትጮህና ስትለፈልፍ ጥቂት ሰዎች ተሰባሰቡ። ከተሰባሰቡት ሰዎች መካከል አንድ ለየት ያለ ሰው ከሕዝቡ መካከል ደብለት ብሎ ቆሟል። ይህ ሰው በዚያ ግርግር ማንም ሳያየው የውጪውን በር ከፍቶ ገብቶ ከገባ በኋላ ፊቱን ወደ ግድግዳ አዙሮ ስለቆመ ፋኒቲን ያለችውንና የተግጠነችውን ሁሉ ሰምቷል። ፖሊሶች የፋንቲንን እጅግ አጥብቀው በመያዝ ወደ ውጭ እየጐተቱ ሲያወጥዋት ባየ ጊዜ ይህ ሰው «አንድ ጊዜ ቆዩ እስቲ» ሲል አዘዘ። ፖሊሶቹ የፋንቲንን እጅ ለቀቁ። ዣቬር ከረሮው ወጣ ብሎ ሲመለከት ትእዛዙን የሰጡት ከንቲባው መሴይ ማንደላይን እንደሆኑ ይገነዘባል። የፖሊሱ አዛዥ ጐንበስ ብሎ እጅ ዐመንሳት ሰላምታ ሰጣቸው። ሆኖም ፊቱ ላይ የመቀየምና የመቆጣት ሪኬት ዐሌህ ታየ።

«ይቅርታ፣ ክቡር ከንቲባ!» ፋንቲን 'ክቡር ከንቲባ' የሚለውን ቃል ሰትሰማ የፋንቲን ፊት ተለዋወጠ። ከመቅጽበት ብድግ ብላ ቆመች። ከዚያም ላይታሰብ በድንገት ማንም ሊያቆማት በማይችል ፍጥነት ተወርውራ ከበርንቲባው እግር ሥር ወደቀች። አንገትዋን ቀና አድርጋና ዓይንዋን ጉሊጎላ አውጥታ ከንቲባውን በማፍጠጥ እያየች «የከተማው ከንቲባ እርሰዎ ኖት?» ስትል ጠየቀች። ቀጥሎም የፈዝ ሳቅ ሰቃ ከከንቲባው ፊት ላይ ዎራቱን ተፋች። ከንቲባው መሃረባቸውን አውጥተው ፊታቸውን ኳጠራረጉ በኋላ የሚከተለውን ተናገሩ።

«መሴይ ዣቬር፣ ይህችን ሴት ልቀቃትና ትሂድ።»

የፖሊሱ አዛዥ የሚለውን ሰላጣ ድርቅ አለ። የሰማው ነገር ስላሰገረመው አፉን እንደ ከፈተ ቀረ። ከንቲባው የተናገሩት ነገርና የሰጡት ትእዛዝ ፋንቲንንም አፈዘዛት። ራሱን ያዞረው ሰው እንዳይወድቅ አንድ ነገር ለመያዝ እንደሚጣደፍ ሁሉ እርሰዎም እጅዋን በቶሎ ዘርግታ የደረሰችበትን ቋሚ እንጨት ያዘች። ከዚያም አካባቢዋን ከቃኘች በኋላ እርስ በራሰዋ ስትነጋገር ድምፅዋን እጅግ ዝቅ አድርጋ ለፈለፈች።

«ልቀቅዋት! በነፃ ሊለቋኝ! ወደ ወህኔ ቤት አልወርድማ! ስድስት ወር አልታሰርም ማለት ነዋ! ለመሆኑ ይህን ያለው ማነው? ማንም ይህን ሊል አይችልም። የለም እኔ ተሳስቼአለሁ። ይህ ሰው ያ አቡይ ከንቲባ ሊሆን አይችልም። ወይ መሴይ ዣቬር! እርስዎ ኖት አይደል ይህን ያሉት? ቢሆንም ብቻ ሲያፈዙ መሆን አለበት። 'ልቀቋትና ትሂድ' ነው ያሉት? ቢፈልጉ ከቤቴ ይሂዱና ቤታቸውን ያከራየኝን ሰው ይጠይቁ። የቤት ኪራይ በጊዜው እንደምከፍልና ታማኝ ሰው መሆኔን ይነግሮታል። ይህን ራስዎ ሊያረጋግጡ ይችላሉ። እባክዎን ይቅርታ ያድርጉልኝ። እስቲ ለፈጣሪ ብለው ይራሩልኝ።»

ፋንቲን ወደ ፖሊሶቹ ፊትዋን አዙራ «ይህን ሰው ተመልከቱት። እንዴት ብዬ ምራቄን እንደ ተፋሁበት አይታቹህ የለ? የኛ ከንቲባ! ሊያስፈራሩኝ አይደለም ከዚህ የመጡት? እኔ ግን እርስዎን አልፈራም። እኔ የምፈራው መሴይ ዣቬርን ብቻ ነው። ደጉንና አዛኙን መሴይ ዣቬርን ብቻ ነው የምፈራው። ቀጥላም ወደ ፖሊሱ አዛዥ ወደ ዣቬር ፊትዋን አዞረች።

«አይ ጌታዬ፣ እውነተኛ ዳኛ መሆን አለብዎት። ትክክለኛ ዳኛ እንደሆኑ እኔም አውቃለሁ። ሴት ልጅን በጠጣር በረዶ መምታት ልክ አይደለም፣ ያውም ምንም ሳይደርሱበት! ድብደባውን የተመለከቱ መኰንኖች በትርኢቱ ተደስተው ሳቁ። እኛ ምስኪኖች የእነርሱ መደሰቻና መሳለቂያ ነን? እርስዎ የደረሱት ከዚያ በኋላ ነው። እርግጥ ነው፣ እርስዎ ሕግ የማስከበርና ሥርዓት የማስያዝ ኃላፊነት አለብዎት። ለዚህም ነው እኔን የያዙኝ። ነገር ግን ጉዳዩ ትክክል አለመሆኑን ሲረዱ 'ልቀቅዋትና ትሂድ' አሉ። ትክክለኛ ዳኛ እንደ መሆንዎ አሁንም በድጋሚ 'ሂጂ' ይበሉኝና ልሂድ። ይህንንም የሚያደርጉት ለሕፃንዎ ልጂ ብለው እንደሆነ ይገባኛል። ስድስት ወር ሙሉ ከታሰርኩ ልጂን ለመርዳትና ለማሳደግ አልችልም። መሴይ ዣቬር፣ ዳግም ሌላ ጥፋት እንደማላጠፋ ቃሌን እሰጥዎታለሁ። ማንም ቢሆን እንደ ፈለገውና እንዳሻው ይላለቅብኝ፣ ይዝለፈኝ። ከዛሬ ጀምሮ ለማንም መልስ አልሰጥም። ሁለተኛ ጥፋት አጥፍቼ ከፊትዎ ብቅም እንደ ፈለጉ ቢያደርጉኝ እኔ ዝም እላለሁ። ዛሬ ያደረግኩትን

የፈጸምኩትና እንገቱን ዘልዬ ያነቅሁት ሰውዬው በጣም ስላናደደኝ ነው። በዚያ ላይ ደግሞ፣ እኔ ነግሬዎታለሁ፣ አሞኛል። ሳል ይዞ ያጣድፈኛል። በበሽታ እንደዚህ ተይዤ ሳለ ሰውዬው በበረዶ ሲመታኝ ሰውነቴ ጋለ፣ ሰሜቴም ገነፈለ። መላ ሰውነቴ ተንቀጠቀጠ። ራሴንም መቆጣጠር ተሳነኝ። ሐኪም ደግሞ እንድጠነቀቅ መክሮኛል። ጌታዬ ሳይፈሩ ሰውነቴን ቢነኩ መላ አካሌ ምን ያህል እንደጋለ ይገነዘባሉ። መላ ሰውነቴን ቢዳስሱት ምን ያህል እንደ ጋልኩ ይረዳሉ።

አካልዋን በድንገት ስትመለከት የለበሰችው ቀሚስ መዛነፉን ሰላየች ሳብ ሳብ አድርጋ አስተካከለችው። ለካስ ፖሊሶቹ ሲጐትቷት ቀሚስዋ ተዛንፎ መሸፈን የነበረበት የሰውነትዋ ክፍል ገሃድ ወጥቶ ይታያል። ብድግ ብላ ተነስታ ፖሊሶቹን እጅ በመንሳት ወደ በሩ አምርታ «ወንድሞቼ፣ የፖሊሱ አዛዥ ትሂድ ብለዋልና መሄዴ ነው» አለቻቸው።

መሲይ ዣቬር እስከዚያች ደቂቃ ድረስ ቃል ሳይተነፍስ ስላቀረቀረ አጢኖ ለተመለከተው ሊተከል ተራ የሚጠብቅ ሐውልት እንጂ ሰው አይመስልም ነበር። ሴትዮዋ ያን ሁሉ ስትለፈልፍ ነቅነቅ እንኳን አላለም። ፋንቴን ከአረችብት ተነስታ ለመውጣት ስትራመድ የሆነ ነገር ረግጣ ኖሮ ከእንትልፍ ሊቀሰቅስ የሚችል ድምፅ ተሰማ። ዣቬር ይህን ጊዜ ከተዋጠበት የሰሚት ባህር ነቅቶ አንገቱን ቀና አደረገ። የተሰጠው ሥልጣንም እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ታሰበው።

መቼስ የበታች ሹማምንት ትንሽ ሥልጣን ሲሰጣቸው እንደ አውሬ እንደሚባሉ እሙን ነው። ትምህርት ወይም የኑሮ ልምድ እንዳልሞረደውና በአእምሮ እንዳልበሰለ ሰው ከፋኖ ይጨከናሉ። ሁሉንም ሰው እንደ ውሻ በመንከስ ይጠጯጭቁታል።

«ቸነምሳ አለቃ» ሲል ዣቬር ጮኸ። «ይህች አገር በጥባጭና ዱርዬ ሴት መውጣትዋ እንደሆነ አይታይህም? ማነው 'ትሂድ' ብሎ ያዘዘህ?» ብሎ ሲጠይቅ «እኔ» አለ ጮማ ይዞ ቆሞ የነበረው ከንቲባ። ፋንቲን ዣቬር የተናገረውን ስትሰማ ሊሰርቅ የተደረሰበት ሌባ የሰረቀውን እቃ ቀስ ብሎ እንደሚጥል ሁሉ እርስዋም በእጅዋ ይዛው የነበረውን እቃ ቀስ ብላ ለቀቀችው። የመሲይ ማንደላይንን ድምፅ ስትሰማ እጅግ በጣም ደንግጣ ዝም አለች። ሆኖም ግን ፊትዋን አንድ ጊዜ ወደ ከንቲባው፣ ቀጥላም ወደ ዣቬር በማዞር ሁለቱን ሰዎች ግንባጹርና ግስተያየት ጀመረች። «የትኛው ነው አሁን በመጨረሻ የሰማሁትን የተናገረው» ስትል በለሆሳስ ራስዋን ጠየቀች ። እንኳን መናገር ለመተንፈስም አልደፈረች።

«እኔ» ብሎ ሲናገር ዣቬር ፊቱን ወደ ከንቲባው አዞረ። ይህን ጊዜ ፊቱ በንዴት ጠቁሮ፣ ደሙ በብስጭት ፈላ። ሰውነቱ መዋዥ መጨበጫ አጥቶና በቀቢጸ-ተስፋ ተወጥሮ ተቅበጠበጠ። ድምፁን አከራሮ «ከቡር ከንቲባ ይህ ሊሆን አይችልም» ሲል ተናገረ ዣቬር በመጨረሻ።

«ለምን አይሆንም?» በማለት መሲይ ማንደላይን ዣቬርን ሊጠይቁት «ይህቺ ባለጌ ሴት፣ አንድን የተከበረ የከተማችን ነዋሪን ተሳድባለች፣ አስቀይማለች» ሲላቸው «ዣቬር ስማኝ። እንተ እውነትኛ ሰው ስለሆንክ ጉዳዩን ባስረዳህ ቅር እንደማትሰኝ ተስፋ አደርጋለሁ» ሲሉ ከንቲባው ረጋ ባለ መንፈስ ተናገሩ። ቀጥሎም «እውነቱን ልንገርህ። እንዳጋጣሚ ሆኖ እኔ በዚያ ሳልፍ አንተ ይህችን ሴት ይዘህ ስትወጣ አይቻለሁ። ብዙ ሰው ተሰብስቦ ስለነበር አንተ እኔን አላየኸኝም። አንተ ሴትዮዋን ይዘህ ከሃድክ በኋላ ግን ስለሆነው ነገር ከዚያ የነበሩ ሰዎችን ጠይቄአለሁ። ሰዎቹ ስለሁሉንም ነገር አሰረድተውኛል። ጥፋተኛው አንተ የምትለው የከተማው ነዋሪ እንጂ ይህቺ ሴት አይደለችም። እርሱን ነበር ፖሊሶች መያዝ የነበረባቸው» ሲሉት ዣቬር መልስ ሰጠ።

«ይህቺ ባለጌ ሴት ከንቲባችንን ተሳድባለች፣ አስቀይማለች» ሲላቸው «ይህ እኔን እንጂ አንተን አይመለከትም» አሉ መሲይ ማንደላይን አሁንም ረጋ ባለ መንፈስ። «የሰደበችው እኔን ስለሆነ ስለስድቡ እኔው ራሌ የፈለግሁትን እርምጃ እወስዳለሁ» አሉት።

«ይቅርታ ያድርጉልኝ ጌታዬ፣ ስድቡ የተሰነዘረው በእርስዎ ላይ ብቻ ሳይሆን በመንበርዎ ላይም ስለሆነ ይህ መዳኘት ያለበት ጉዳይ ነው።»

«ዣቬር» አሉ ከንቲባው፣ «ትልቁ ዳኛ ጎሊና ነው። ይህቺ ሴት የተናገረችውን ሰምቻለሁ። የምሠራውን የማላውቅ አይምሰልህ» ባሉት ጊዜ «ክቡር ከንቲባ፣ አሁን የማየውንና የምሰማውን እላውቅም» ሲላቸው «እንግዲያውስ ብዙ ንግግር አያስፈልግምና ትእዛዜን ተቀበል» አሉት።

«በእኔ በኩል ግን ግዳጄን ነው የምታዘዘው። ግዳጄ ደግሞ ይህቺ ሴት ለስድስት ወር እስር ቤት መቆየት እንዳለባት ይጠይቀኛል» ብሎ ሲናገር «ስማ፣ አንድ ቀን እንኳን አትታሰርም» ሲሉ ከንቲባው እቅጩን ሲነግሩት«ክቡር ከንቲባ፣ ቢፈቅዱ...» ብሎ መናገር ሲጀምር «ሌላ ቃል አትናገር» ቢሉትም እርሱ ግን «ሆኖም..» ብሎ ሲጀምር «እቁም ብያለሁ» አሉ መሲይ ማንደላይን በቁጣ። ዣቬር የሚሰማውን ላለመቀበል ለተቸገረ ቅስሙ ተሰበረ። እንደ መስከብ ወታደር ደረቱን ገልብጦ ጥሂት ከፉመ በኋላ ለከንቲባው እጅ ነስቶ ከነበረበት ሄደ። በዚህ ጊዜ ፋንቲን ወደ በር

አጠገብ ሄዳ ከንቲባውን አየችው:: ነገሩ ሁሉ ተመሰቃቀለባት:: የሁለቱን ሰዎች ንግግር ስላዳመጠች አፈረች:: የሰማቸውን ለማመንም ተቸገረች:: ከንቲባው የተናገሩትን እያንዳንዱ ቃል ልብዋ ውስጥ ተቀብሮ ቀደም ሲል የነበራትን ጥላቻ እያሟሟ ስሜትዋን አስከዳት:: በከንቲባው ጥላቻ ምትክ በቃላት ሊገለጽ በሚያዳግት ደስታና ፍቅር ልብዋ ተሞላ:: ከንቲባው ፋንቲንን በዝግታ አናገርዋት::

«የተናገርሽውን ሁሉ ሰምቻለሁ:: ስላልሻቸው ነገሮች እኔ የማውቀው ነገር የለም:: ሆኖም እውነትነት እንዳላቸው የምጠራጠረው አይደለም:: ከፋብሪካዬ ሥራ ለቅቀሽ ስለመውጣትሽ እንኳን አልሰማሁም:: ለምንድነው በጊዜው መጥተሽ ያላነጋገርሽኝ? ለማንኛውም ያለብሽን እዳ ሁሉ እኔ እከፍልልሻለሁ፤ ልጅሽንም አስመጣልሻለሁ:: ከፈለግሽም ወደ ልጅሽ ወይም ወደ ፖሪስም ሆነ ወደ ሌላ ከተማ ሄደሽ ከልጅሽ ጋር ለመኖር ትቺያለሽ:: ለልጅሽም ሆነ ላንቺ የሚያስፈልጋችሁን ገንዘብ እኔ እሰጣችኋለሁ:: ሥራ መሥራት ካስጠላሽም ከዛሬ ጀምሮ ሥራ መሥራቱን ማቆም ትቺያለሽ:: ለመኖር የሚያስችላችሁን ገንዘብ እኔ እረዳችኋለሁ:: ለዚህም እኔ ካንቺ የምፈልገው በታማኝነት እንድትኖሪ ብቻ ነው:: ደግሞም ጆሮሽን አቅንተሽ እንድትሰሚኝ የምፈልገው ነገር ቢኖር ከአሁን ቀደም በእግዚአብሔር ፊት ንጽህናሽን ጠብቀሽ እንደ ኖርሽ ስለማልጠራጠር አሁንም ከዛሬ ጀምሮ ክፉትና ምቀኝነት የተለየው ኑሮ እንድትኖሪ ከአደራ ጭምር ነው የማሳስብሽ:: ምስኪንዋ ሴት፣ አይዞሽ:: አንቺ ብቻ በኑርሽ በርቺ::»

ፋንቲን ያላትን ሁሉ ለመሸከም ከምትችለው በላይ ሆነባት:: ከልጅዋ ከክዜት ጋር አብራ ልትኖር! ከዚያ አስነዋሪ ኑሮዋ ልትላቀቅ! የገንዘብ ችግር ሳይኖርባት በደስታና በታማኝነት ከልጅዋ ጋር ልትኖር! እንዴት ሊሆን ይችላል በሚል ግራ ተጋባች:: ይህ ሁሉ ያልታሰበ ኑሮና ጥሩ ሕይወት በአሳብ ሲታያት እንዴት ብላ ትመነው! 'ወይኔ፣ ወይኔ' ብሎ ከመጮህ ሌላ ምንም ለማለት አልቻለችም:: ያንን ሁሉ ችሮታ፣ ያንን ሁሉ ደግነት ለመሸከም ሰውነትዋ አቅም ስላጣ መላ አካልዋ ተዝለፈለፈ:: ከመሬይ ማንደላይን እግር ሥር ወደቀች:: ከንቲባው ጎንበስ ብሎ ሊያነሳት ሲል እጁን ይዛ ኃፍረት እየተሰማት ላመችው:: ከዚያም ጎሊናዋን ሳተች::

ምዕራፍ አምስት
ገቮር

መሬይ ማንደላይን ከቤቱ ውስጥ የሕክምና እርዳታ የሚሰጥበት ክፍል ስለነበረው ፋንቲንን ወደዚያ አስወሰዳት:: ከዚያም እንደ ደረሰች የሕክምና እርዳታ የሚሰጡ ሴሮች ከአልጋ ላይ አስተኙዋት:: ፋንቲን በኃይል አተኩሳለች:: ሕሊናዋን ሳታውቅ ብዙ እየቃዠች ለጥቂት ጊዜ ቆየች:: ቀጥሎ ግን ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰዳት::

በሚቀጥለው ቀን ወደ ስድስት ሰዓት ገደማ ከእንቅልፍዋ ስትነቃ ከአጠገብዋ ሰው መቆሙን ተገነዘበች:: መሬይ ማንደላይን ነበር ጣራውን እያየ ከአጠገብዋ የቆመው:: ቀና ብላ ስታየው ፊቱ በሃዘኔታ ተሞልቷል:: ከንቲባው ጣራውን ሳይሆን ከግድግዳ ላይ የተሰቀለውን መስቀል ነበር የሚያየው:: ይህ ሰው መልዓክ እንጂ ሥጋ የለበሰ ፍጡር አልመሰላትም:: መላ ሰውነቱ በብርሃን የታነፀ መሰላት:: መሬይ ማንደላይን እየጸለየ ስለነበር ጸሎቱን ላለማቋረጥ ቃል ሳትተነፍስ ለረጅም ጊዜ አፍጥጣ እያያችው ቆየች:: በመጨረሻ ግን እየፈራች ቢሆንም አፍ አውጥታ ተናገረች::

«ምን እየሠሩ ነው?»

ከንቲባው የፋንቲንን መንቃት እየተጠባበቀ ከዚያ ሥፍራ ወደ አንድ ሰዓት ያህል ነበር የቆመው:: እጅዋን ይዞ የልብዋን ምት ቆጠረ:: «ደህና ነሽ:: አሁን የሚሰማሽ ነገር አለ?» ብሎ ሲጠይቃት «ብጣም ደህና ነኝ፣ እየበረታሁ ነው:: እንቅልፍ ወስዶኝ ብዙ ተኛሁ እኮ!» አለችው::

«እንግዲያውስ ወደ ጥያቄሽ ልመለስና ምን እየሠራህ ነው ስላልሽው ስላንቺ ፈጣሪን በመማጠን ጸሎት እያደረስኩ ነበር::»

ያን እለት ማታ ስለፋንቲን የሕይወት ታሪክ ሲጠይቅ አመሸ:: በሚቀጥለው ቀንም ያንኑ ቀጠለ:: ስለዚህ ምንም ነገር ሳይቀረው ስለፋንቲን ሕይወትና ኑሮ ሁሉንም ባወቀ ጊዜ «ከመጠን በላይ ተሰቃይተሻል፤ ከአሁን በኋላ ግን ችግርሽ ስለሚቃለል አሳብ አይግባሽ:: በዚህ ዓይነት ነው የሥጋ ለባሾች ሕይወት የሚለወጠውና መስዋዕት የሆነብት ነገር ሁሉ የሚያበቃው» አላት:: ቀጥሎም «ከዚህ የተለየ መንገድ እንዳለ እኔ አላውቅም:: አንቺ ያለፍሽበት ምድራዊ ገሃነም ወደ መንግሥተ-ሰማይ የሚወስድ የመጀመሪያ እርምጃ ነው:: እኛ ደግሞ ወደዚያ እንድትሂጂ መርዳት ግዴታችን ነው» ሲል የልቡን ገለጠላት::

መሴይ ማንደላይን ይህን ካለ በኋላ በኃይል ተነፈሰ። ፋንቲን መሴይ ማንደላይን የተናገረውን ስትሰማ ፊትዋ ወገግ ብሎ ስትስቅ ወሳቷ ጥርስዋ ታየ። ከንቲባው ግን አስተያየት ከመስጠት ተቆጥቦ ወዲያው ወደ እነሚርና ሚስስ ቴናርዴ ደብዳቤ መጻፍ ጀመረ። በደብዳቤው ፋንቲን ያለባት እዳ አንድ መቶ ሃያ ፍራንክ እንደሆነ ገልጾ ቢጽፍም ሦስት መቶ ፍራንክ ነበር የላከላቸው። ገንዘብ በብልጫ የላከው እንዲሁ ሳይሆን በተጆለ ፍጥነት የፋንቲንን ልጅ ይዘው እንዲመጡ በመጠየቅ ነበር። የልጅትዋ እናት እንደ ታመመችና ልጅዋን ለማየት እጅግ እንደጓጓችም አክሎ በመጻፍ ከዜትን በቶሉ ይዘው እንዲመጡ አጥብቆ ጠየቃቸው። እሁኖርዴ ደብዳቤውና ገንዘቡ እንደ ደረሳቸው እጅግ በጣም ተደነቁ።

«ለይጣን» አለ ሚ/ር ቴናርዴ ወደ ሚስቱ ፊቱን በማዞር። «ልጅትዋን እንኑጥም። ምናልባትም የሆነ ቂል ወንድ በውበትዋ ተማርኮ ይሆናል ይህን የመሰለ ደብዳቤ የጻፈው» ካለ በኋላ ሚ/ር ቴናርዴ ኮዜትን በመላክ ፈንታ ሂሳቡን በተንቃቄ አሰልቶ ፋንቲን ያለባት እዳ አምስት መቶ ፍራንክ እንደሆነ በመግለጽ ለመሴይ ማንደላይን የመልስ ደብዳቤ ጻፈላቸው። ተጨማሪው ሁለት መቶ ፍራንክ ልጅትዋ በታመመች ጊዜ ለመድኃኒት መግዣ የወጣ መሆኑንም ገልጾ ነበር የጻፈው። መሴይ ማንደላይን ደብዳቤው እንደደረሳቸው ሦስት መቶ ፍራንክ ላኩለት። ገንዘቡንም ሲልኩ አሁንም በተጆለ ፍጥነት ኮዜትን ይዘው እንዲመጡ በድጋሚ ጠየቃቸው። አሁንም «ምንም መንገድ ልጅትዋን አንሰጥም» አለ ሚ/ር ቴናርዴ።

ፋንቲን በሽታዋ ጠናባት እንጂ ስላልተሻላት አልጋ ላይ እንደ ዋለች ነው። ደኑ ሎው በቀን ሁለት ጊዜ ከነበረችበት ሃደው ይጠይቋታል። ሊጠይቅዋት በሄዱ ቁጥር ግን «ሳልሞት ኮዜትን በዓይኔ የማያት ይመስሎታል?» ስትል ትጠይቃቸዋለች። እርሳቸውም ሲመልሱ «ምናልባትም ነገ! በማንኛውም ሰዓት ልትመጫ ልታያት ትቺያለሽ» ይልዋታል። በዚህ ጊዜ የእናትዮ ፊት ወገግ ይላል። «ቢሆንማ እንዴት ደስ ባለኝ!» በማለት በምጸት ቃል ተናገረች። ፋንቲን ሕመምዋ እያደር ጠናባት እንጂ አልተሻላትም። ከአለታት በአንዱ ቀን እየተመላለሱ የሚያክሟት ሐኪም የሳምባዋን አተነፋፈስ በማዳመጫ መሣሪያ ካዳመጡ በኋላ ራሳቸውን ተቀነቁ። ይህን ያዩ ከንቲባ «እየተሻላት ነው? ሲሉ ጠየቅዋቸው።

«ሳይንሱን ለማያት የጓንችላት ልጅ አላት አይደል?» ብለው ሐኪሙ ሲጠይቁ «አዎን» የሚል መልስ ተሰጣቸው።

«እንግዲያውስ በተቱ ብታሰመጡላት ይሻላል» የሚል ቃል ከሐኪሙ ሲሰሙ መሴይ ማንደላይን እጅግ ደንግጠው ሰውነታቸው ተንቀጠቀጠ።

«ሐኪሙ ምን አሉ?» ስትል ፋንቲን በጣየቀች ጊዜ መሴይ ማንደላይን ፊታቸውን ፈገግ ለማድረግ ሞክሩ። ቀጥለውም «ልጅሽን በተሉ እንድናስመጣልሽ መክረውናል። ይህም ቦሽታሽን ሊያቃልለው እንደሚችል ነው የነገሩን» ብለዋት ወደ ቢሮአቸው ሄዱ። መሴይ ማንደላይን ከቢሮአቸው ቁጭ ብለው ሥራቸውን እየሠሩ ሳለ ጥቪር ሊያነጋግራቸው እንደሚፈልግ ጸሐፊያቸው ነገረቻቸው።

«ይግባ» አሉ ከንቲባው። የፖሊሱ አዛዥ ጥቪርም ከቢሮአቸው ገብቶ ለከንቲባው የአክብሮት ሰላምታ ሰጠ። ከንቲባው ወረቀት እያገላበጡ ፊታቸውን ወደ መስኮት አዙረው ሰለነበር ጥቪር ከቢሮአቸው ሲገባ ያዩት ነው ያየው። መሴይ ማንደላይን ቀና ብለው ሳያዩት ወረቀት ያገባቸውን ቀጠሉ። ጥቪርም የክፍሉን ፀጥታ ብዙም ሳያደፈርስ በዝግታ ወደፊት ተራመደ። ፊቱ ላይ የቆራጥነት ብቻ ሳይሆን የድፍረትም ምልክት በጉልህ ይታያል። ከንቲባው በእጃቸው ይዘውት የነበረውን ብዕርና ወረቀት አስቀምጠው ቀና ብለው አዩት።

«ታዲያስ፣ ደህና ዋልክ? ምንድነው ጥቪር፣ ምን አጋጠመህ?» ብለው ሲጠይቁት ጥቪር አሳቡን ለማሰባሰብ ለአጭር ጊዜ ዝም አለ። በመጨረሻ ግን ድምፁን አለስልሶ ሀዘን በተሞላበት አንደበት «ክቡር ከንቲባ፣ የሆነ ወንጀል ተሠርቷል» ሲል ተናገረ።

«የምን ወንጀል?»

«አንድ ግለሰብ የመንግሥት ባለሥልጣንን በሐሰት ስለወነጀለ ራሱን ለማጋለጥ ይፈልጋል። ጉዳዩ እኔን የሚመለከት ስለሆነም ይህን ለማሳወቅ ነው አሁን እኔ ወደ እርስዎ የመጣሁት።»

«ራሱን ለማጋለጥ የሚፈልገው ሰው ማነው?» በማለት ከንቲባው ሲጠይቁት «እኔ» ሲል መለሰላቸው።

«አንተ ራስህ?» ብለው ሲጠይቁትም «አዎን፣ እኔው ራሴ» አላቸው።

«ማንን በድለህ ነው ራስህን የምታጋልጠው?» ባሉት ጊዜ «ክቡርነትዎን» ሲላቸው መሴይ ማንደላይን እንደ ተቀመጡ ወንበራቸውን አስተካከሉ። ጥቪር ሳይፈራ አሁንም በትህትና ንግግሩን ቀጠለ።

«ክቡር ከንቲባ፣ ያደረስኩት በደል ከባድ ስለሆነ እኔ አሁን ክቡርነትዎን የምጠይቀው ከሥራ እንዲያሰናብቱኝና ክስ እንዲመሠርቱብኝ ነው» ሲል ጠየቃቸው።

ከንቲባው እጅግ በጣም ተገርመው ለመናገር አፋቸውን ከፈቱ:: ነገር ግን ጎቬር ጣልቃ በመግባት ቀድሞ ተናገረ::

«ሥራህን ከለቀቅክ ይበቃል ይሉኝ ይሆናል:: በእኔ እምነት ግን ይህ ብቻ እደበቃም:: በገዛ ፈቃድ ሥራ መልቀቅ መቻልማ ታላቅ ክብር ነው:: ጥፋት ስላጠፋሁና በመሰላት ሌላውን ሰው ስለበደልኩ ለፍርድ ቀርቢ መቀጣት አለብኝ:: ከሥራም መባረር ይኖርብኛል::»

«እንዴ፣ በምን ምክንያት? ምንድነው ነገሩ?» ብለው ሲጠይቁት «ክቡር ከንቲባ፣ ጉዳዩን ሲያውቁት ይህን ጥያቄ ዳግም አይጠይቁኝም:: ያኔ ነገሩ ሁሉ ይገባዎታል» ካለ በኋላ ጎቬር በኃይል ተነፈሰ:: ሀዘን እየተሰማውና እያፈረ ንግግሩን ቀጠለ::

«ክቡር ከንቲባ ከሰድሰት ሳምታት በፊት ያቺን ሴት በነፃ አንድሲቃት ካዘዙኝና እኔም በነፃ ከለቀቅኋት በኋላ በጣም ተናድጀ ሰለነበር እኔ ከሹርነተዎን ከሰሰኩ::»

«እኔን ነው የከሰሰከው?» ብለው ከንቲባው ሲጠይቁት «አዎን እርስዎን፣ ፖሊስ ድረስ ሄጀ ለፖሊስ ጠቅላይ አዛዥ ክሴን አቀረብኩ» በማለት ሲመልሰላቸው ብዙ ጊዜ የማይሰቁት መሴይ ማንደላይን ክት ክት ብለው ሳቃቸውን ለቀቁት::

«የፖሊስን ሥልጣን ተጋፋ ብለህ ነው የከሰሰከኝ?»

«የለም፣ የጥንት ወንጀለኛ ናቸው ብዬ ነው የከሰስኩዎት» ሲሳቸው ከንቲባው ደንገጡ:: እንዳቀረቀረ የቀረው ጎቬር አሁንም ንግግሩን ቀጠላ::

«ለልተጠራጠርኩም ነበር:: ለረጅም ጊዜ ያጤንኩበት ጉዳይ ስለነበር በነገሩ በጽኑ አመንኩ:: መልክዎ፣ ቁመናዎ፣ ጉልበትዎና ሌላም ሌላም ነገሮዎ ሁሉ አንድ ስለሆነብኝ ጥን ቫልጉ ነዎት ብዬ ደመደምኩ::»

«ግንን አልክ? እንዴት ብለህ ነው ስሙን የጠራኸው?»

«ጥን ቫልጉ! ከሃያ ዓመት በፊት የወነዪ ቤት ሹም በነበርኩበት ጊዜ እንድ እስረኛ ነበር:: ይህ ወንጀለኛ ከእስር ቤት ካመለጠ በኋላ የአንድ የተከበሩ ጳጳስ ንብረት ዘርፎአል:: በዚህም አላበቃም፣ በመሣሪያ ኃይል አስፈራርቶ የሌላም ሰው ንብረት ሰርቋል:: ይህን ወንጀለኛ ለመያዝ ብዙ ፍለጋ ቢካሄድም ስምንት ዓመት ሙሉ የት እንዳለ ለማወቅ ስላልተቻለ ወንጀለኛው የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ:: ክቡር ከንቲባ ምን አለፋዎት ብቻ ያ ሰው ክብሩነትዎ እንደሆነ ሰላመንኩ ለጠቅላይ ፖሊስ አዛዥ ጠቄምክዮት::»

በዚህ ዓይነት ጎቬር ነገር ሲያበዛባቸው ወረቀት ግንላበቅ የጀመሩት መሴይ ማንደላይን ረጋ ባለ አነጋገር «እና ምን ተባልክ?» ሲሉ ጎቬርን ሰጠይቁት «አበድክ እንዴ» አሉኝ ሲል መልስ ሰጣቸው::

«ከዚያስ?» ብለው ሲጠይቁት «ከዚያማ እነርሱ ልክ መሆናቸውን አመቀሁ» አለ:: ይህን ጊዜ «ጥሩ ገምተሃል» በማለት መለሱለት::

«እነርሱ ልክ መሆን አለባቸው፣ ምክንያቱም እውነተኛው ጥን ባልጉ ተገኝቷል» ብሎ ሲናገር ከንቲባው በእጃቸው ይዘውት የነበረው ወረቀት አምልጧቸው ከመሬት ወደቀ:: መሴይ ማንደላይን አንገታቸውን ቀና በማድረግ ጎቬርን በአጽንዖት ተመለከቱት:: ዝግ ብለውም «ተገኘ!» ሲሉት ጎቬር ንግግሩን ቀጠለ::

«ክቡር ከንቲባ፣ ታሪኩ እንዲህ ነው:: ገጠር ውስጥ ሻምፕማትዬ የሚባሉ አንድ የዋህና ደግ ካህን ነበሩ:: እኚህ ካህን እጅግ በጣም ድሃ ሲሆኑ የሚረዳም ዘመድ ወዳጅ አልነበራቸውም:: እንደ እርሳቸው ያለ ምስኪን ሰው የአለት ተአለት ኑሮ ምን እንደሚመስል ብዙም አይታወቅም:: በመጨረሻ እኚህ የቤተክርስቲያን ሰው ፍራፍሬ ሰርቀው ይያዛሉ:: ፍራፍሬ መስረቃቸው ይህን ያህልም የሚያስከፋና የሚያስወነጅል አልነበረም::

«የተለያዩ ፍሬ የያዙና ብዛት ያላቸው የፍራፍሬ ዛፎች ቅርንጫፎቻቸው ተቆርጠው በየመንገዱ ተጥለው ይታያሉ:: ይህ ነው እንግዲህ እንደ ክፉድ ጥፋት የተቆጠረው:: እኚያ ካህን የተያዙት ተቀንጥሰው ከወደቁት የዛፍ ቅርንጫፎች መካከል አንደኛው ከነፍሬው እርሳቸው እጅ ስለተገኘ ሲሆን በዚህም ምክንያት ነው ሌባ ተብለው የታሰሩት:: ቢሆንም ይህኛውም ወንጀል ለአጭር ጊዜ የሚያሳስር እንጂ ለብዙ ዓመታት እስር የሚያሰፈርድ አልነበረም:: ነገር ግን እዚህ ላይ ነው የተፈጥሮ ኃይል ሥራውን የሠራው:: «አባታችን ሻምኝማትዬ የታሰሩበት እስር ቤት ስለጠበበ ወደ ሌላ እስር ቤት ይዛወራሉ:: ከአዲሱ እስር ቤት ውስጥ ለረጅም ዘመን የታሰረ ብሪቬት የሚባል ሌላ እስረኛ ጥሩ ጠባይ በማሳየቱ የእስረኞች ተቆጣጣሪ ሆኖ ይሾማል:: ይህ ሰው ካህኑን ገና ሲያያቸው 'ወንጀለኛውን አገኘሁት'፣ ወንጀለኛውን አገኘሁት' ሲል ይጮሃል:: «ጌታው ወደዚህ ይመልከቱ አስቲ፣ ጥን ቫልጉ ኖት፣ አይደል?» ብሎ ሲጠይቃቸው «ጥን ቫልጉ ደግሞ ማነው?» በማለት ሰውዬውን ለማታለል አባታችን ይሞክራሉ::

«እንዳሳወቀ ለመሆን አይሞክሩ» ይላል ብሪቬት:: «ጥን ቫልጉ ማለት እርስዎ ኖት፣ አውቄዎታለሁ:: ከዛሬ ሃያ ዓመት በፊት ቱሉን ኮሚገኝ እስር ቤት እስረኛ ነበሩ:: ከእዚያ አብረን አብር የታሠርነው» ሲላቸው

«አባታችን ሻምፕማትዬ 'ጉን ቫልጉ ማለት እኔ አይደለሁም' በማለት ሸምጥጠው ካዱ:: ስለዚህ ስለጉዳዩ የተለያዩ ምርመራዎችና ክትትሎች ተደረጉ:: በተደረገው ክትትልም የጉን ቫልጉ ቤተሰቦች ከሰላሳ ዓመት በፊት የት እንደ ነበሩ ተደረሰበት:: ሆኖም ቤተሰቦቹ ያን ጊዜ ከነበሩበት አልተገኙም:: የት እንደ ሄዱ ደግሞ ማንም ሊጠቁም አልቻለም:: ጊዜው በጣም ስለቆየ ጉን ቫልጉንም ለይቶ የሚያውቅ ሰው ጠፋ:: ፍለጋው ግን ተጠናክሮ ቀጠለ:: ሆኖም ከብሪቬት ሌላ ጉን ቫልጉን የሚያውቁ ሌሎች ሁለት አስረኞች ተገኙ:: ሁለቱም የአድሚ ልክ አሥራት የተፈረደባቸው ወንጀለኞች ናቸው:: ስማቸውም ኮሽፔልና ቬኔልድዩ ሲባሉ እስረኞቹ ከአብሩበት ተጠርተው ካህኑን እንዲያዩ ተደረገ:: ካህኑን ገና ሲያዩ ምንም አልተጠራጠሩም:: እነርሱም ሰውዬው ጉን ቫልጉ እንደሆኑ አረጋገጡ:: ካህኑ እንደ ጉን ቫልጉ አድሚያቸው 54 ዓመት ሲሆን ቁመታቸውና ተክለ-ሰውነታቸው እንዲሁም መልካቸው ከሰውዬው ጋር አንድ ሆኖ ተገኘ::

«ይህ እውነት ከተደበቀበት የወጣው ልክ እኔ እርስዎ ጉን ቫልጉ እንደሆኑ ከስ በመሠረትኩበት ጊዜ ስለነበር 'አብደሃል እንዴ፣ ጉን ቫልጉ እኮ ተይዞ አሁን አራስ ከሚባል እስር ቤት ውስጥ ስለሚገኝ ፍርዱን እየተጠባበቀ ነው' ሲሉ ከዚያ እንድጠፋ ነገሩኝ:: ይህን ስሰማ ምን ያህል እንደ ደነገጥኩና እንዳፈርኩ እርስዎም ሊገምቱ ይችላሉ:: ዜናውን እንደ ሰማሁ ሰውዬውን አምጡና አሳዩኝ ብዬ ስጠይቃቸው አምጥተው አሳዩኝ::»

«ከዚያስ!» በማለት መሴይ ማንደላይን ጣልቃ ገቡ:: ጉቬር ግን ሳያመላውል ሀዘን እየተሰማው ምላሹን ሰጠ::

«ክቡር ከንቲባ፣ አውነት ነው፣ እውነት ነው:: ሰውዬው ጉን ቫልጉ እንደሆኑ ምንም አልተጠራጠርኩም:: ስለዚህ ስለፈጸምኩት ስህተት በጣም አዝናለሁ:: 'ሻምፕማትዩ ነኝ' ያሉት ሰውዬ በእርግጥ ጉን ቫልጉ ሆነው ነው ያገኘኋቸው::»

«እርግጠኛ ነህ?» ብለው ከንቲባው ሲጠይቁት ጉቬር የፌዝ ሳቅ እየሳቀ «ሰውዬውም 'እርግጠኛ ነህ?' ሲል ጠይቆኝ 'የምትሉት ነገር አይገባኝም፣ እኔ ሻምፕማትዩ እንጂ ጉን ቫልጉ አይደለሁም' ብሎም ተናግሯል:: ሰውዬው በጣም ጮሌ ነው:: ነገር ግን አራት ሰው ስለመሰከረበት ተገቢውን ቅጣት ይቀበላል እንጂ ከቅጣት አያመልጥም:: እኔም ከሕግ ፊት ቀርቤ የምሰጠውን ቃሌን እንድሰጥ ስለተጠራሁ ወደዚያው በቶሉ እሄዳለሁ::»

መሴይ ማንደላይን ታሪኩን ከሰሙ በኋላ ወደ መሬት አቀርቅረው ከጠረጴዛው ላይ ከነበሩ ወረቀቶች ላይ አፈጠጡ እንጂ ምንም አልተናገሩም::

ሥራ እንደ በዛበት ሰው አንዴ ይጽፉሉ፣ ቀጥሎም ወረቀቶቹን ያገላብጣሉ:: መሴይ ማንደላይን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ወደ ጉቬር ዞር ብለው «ይቅርታ ጉቬር! የነገርከኝ ታሪክ ብዙም አላስደሰተኝም:: አስቸኳይ የሆኑ ጉዳዮች ስላሉብኝ ከዚህ ይበልጥ ጊዜ ባናጠፋ ይሻላል:: ለመሆኑ ወደ አራስ እስር ቤት መቼ ለመሄድ አሰበሃል?» ሲሉ ጠየቁት::

«በቶሉ ሳልሄድ አልቀርም» ብሎ ሲመልስ «ከሰንት ቀን በኋላ?» ሲሉ ሌላ ጥያቄ ጠየቁት::

«ወንጀለኛው ለፍርድ የሚቀርበው ነገ ስለሆነ ዛሬ ማታ መንገድ እጀምራለሁ ብያለሁ::»

«የፍርድ ውሳኔ በቶሉ የሚሰጥ ይመስልሃል?» ብለው ሲጠይቁትም «ሌላ ቀጠሮ የሚሰጥ አይመስለኝም:: እኔ ግን የፍርድ ውሳኔ እስኪሰጥ አልቆይም:: የምስክርነት ቃሌን ሰጥቼ እንደ ጨረስኩ እመለሳለሁ::»


«መልካም» ካሉ በኋላ መሴይ ማንደለይን ጉቬርን ሰላምታ ሰጥተው አሰናበቱት:: ጉቬር ግን ከቢሮአቸው አልወጣም:: «ክቡርነትዎን በድጋሚ ይቅርታ እጠይቃለሁ» ብሎ ሲናገር «ከዚህ በላይ ምን ያስፈልጋል? እኔ እንደሆነ ሁሉንም ነገር ትቼዋለሁ» አሉት::

«ክቡር ከንቲባ፣ ቀደም ሲል የጠየቅከዎትን እንዲያስቡበት» አላቸው:: «ምንድነው እሱ?» ሲሉት «ከሥራ እንዲያሰናብቱኝ ነዋ!» አለ::

«ጉቬር፣ መከበር ያለብህ ሰው እንደሆንህ አውቃለሁ:: ስህተትህን ከሚገባው በላይ ነው ያጌላኸው:: የተበደልኩት እኔ ስለሆንኩ አንተ ፈጸምኩት የምትለውን በደል ይህን ያህል ከቁም ነገር አላስገባሁትም:: ከሥራህ መባረርን በተመለከተ፣ እንኳን ከሥራ ልትባረር እድገት የሚገባህ ሰው ነህ:: ስለዚህ እኔ በሥራህ ላይ እንድትቆይ ነው የምፈልገው» ሲሉት ጉቬር መሴይ ማንደላይንን በጥሞና እየተመለከተ የሚከተለውን ተናገረ::

«ክቡር ከንቲባ፣ ይህ ሊሆን አይችልም:: በሌላው ሰው ላይ የማደርገው ነገር በእኔም ላይ መፈጸም አለበት:: 'ማንኛውንም የጎብረተሰብ አባል የበደለ ሰው ያለ ርኅራሄ ፈልፍዬ በማውጣት ለፍርድ አቀርባለሁ' እያልኩ ዘወትር ለራሴ ቃል ገብቻለሁ:: አሁን ደግሞ እኔው ራሴ ሌላውን ሰው በድያለሁና መታሰፍ የለብኝም:: ስለዚህ ከሥራዬ መታገድ ይኖርብኛል:: የሚሠሩ እጆች ስላሉኝ የትም ሠርቼ ማደር የምችል ይመስለኛል:: ግብርና ብባም ይሆናል:: ለሌሎች ሰዎች ደግሞ ምሳሌ መሆን አለብኝ:: ስለዚህ አሁንም ቢሆን ከሥራ እንዲያባርሩኝ እማጠኖታለሁ::»

«እናያለና!» ካሉ በኋላ ከንቲባው ሊጨብጡት እጃቸውን ዘረጉለት። ጐቬር ግን ከዚሮአቸው ለመውጣት ወደ ኋላ በማፈግፈግ ሸሸት ብሎ «ይቅርታ ክቡር ከንቲባ፣ እጅዎን ለመጨበጥ አልችልም። አንድ የተከበረ ከንቲባ እንደ ማንኛውም ተራ ሰው መታየት ስለሌለበት የተራ ሰው እጅ በቀላሉ እንደሚጨበጥ ሁሉ የከንቲባ እጅ መጨበጥ የለበትም። ተራ ሰው! ለምን ተራ ሰው! ሥልጣኔን መከታ በማድረግ የሠራሁት ሥራ ተራ ሰላይ ከሚፈጽመው ተግባር የተለየ አይደለም» ካለ በኋላ ለጥ ብሎ እጅ አክቶ ከከንቲባው ቢሮ ለመውጣት ጐቬር ወደ በሩ አቀና። በሩን ከፍቶ ሲወጣም አንገቱን እንዳቀረቀረ ነበር። ከመውጣቱ በፊት ግን ፊቱን አዙሮ «ክቡር ከንቲባ፣ የሥራ መልቀቂያ ስንብት እስከተሰጠኝ ድረስ ሥራዬን እቀጥላለሁ» አለ። የበሩን እጄታ እንደ ያዘ ይህን ተናግሮ ጐቬር ከዚሮአቸው ወጥቶ ሄደ። መሴይ ማንደላይን ግን እጅግ እንደ ተከዙ ከመንበራቸው ላይ ቁጭ አሉ። ከንቲባው የጐቬርን ውትወታና ንግግር በመገረም ነበር ያዳመጡት።



ምዕራፍ ስድስት
የሻምፕማትዩ ጉዳይ

የታሪኩ እንባቢ እስካሁን በተነገረው መሴይ ማንደላይን ማለት ጐን ቫልዣ እንደሆነ ያውቃል። ስለዚህ ጐን ቫልዣ ማለት ራሱ እንደሆነ እያወቀ አሁን ሌላ ሰው ጐን ቫልዣ ሆኖ ተገኝቷል ሲሉት ምን ተሰምቶት ይሆን? ሀሊናው ምን ይላል? ምን ዓይነትስ ፈተና ውስጥ ነው የገባው? ከክሕደ ጥልቀትና ከሰማይ ርቀት የላቀው የሰው አእምሮ የዚህ ዓይነቱ ፈተና ሲገጥመው ውስጣዊ ስሜቱ ምን ይመስል ይሆን!

እስከዚያን እለት ድረስ ከልቡ ውስጥ ቀብሮ ያኖረውን ጉዳይ ጐቬር ባደጋገት ሰላነሳበት መሴይ ማደላይን ከቢሮው ውስጥ ቁጭ እንዳለ መላ ሰውነቱ ራደ። 'መጨረሻዬ ምን ይሆን?' ሲል አሰበ፣ አወጣና አወረደ፣ ቁዘመ። ውሽንፍር እንደሚያወዛውዘው ዋርካና ከባድ ጦር እንደ ገጠመው ወታደር ልቡ ከወዲያ ወዲህ ተንከራተተ። ጐቬር ነገሩን አራዝሞ ከቢሮው አልወጣ ብሎት ሲናዝር የአገሩ ደመና ሁሉ ተሰባስቦ መብረቅና ከባድ ዝናብ ከሚጥልባቸው ላይ የሚያዘንብበት መሰለው። ጐቬር እያነጋገረው ሳለ 'ሃድ፣ ተሳሳ፣ ሩጥ፣ ሻምፕማቲዩን ነፃ አውጣ። ወደ ኋላ አትበል፣ ራስህን አጋልጥ' የሚል ስሜት ሀሊናው ውስጥ ሰፍሮ ጭንቅላቱን አዙሮበት ነበር።

'አባ ሻምፕማትዩን ከእስር ቤት አውጥተህ በእርሳቸው እግር አንተ ተተካ' የሚለው አሳብ ከኅሊናው ውስጥ አልወጣ አለው። ሆኖም ውሳኔ ሆኖ አላገኘውም። ጭንቅላቱን የወረረው አሳብ፣ ስለት ያለው ነገር አካል ውስጥ ዘልቆ ሲገባ የሚፈጥረው ዓይነት ስሜት መላ ሰውነቱ ውስጥ ፈጠረበት። ይህን ጊዜ 'መጨረሻውን ምን እንደሚሆን እንያ' ሲል ለራሱ ነገረ። በሌላ መልኩ ግን 'የምን ጀግንነት ነው፣ በማለት ራሱን በመገሰፅ ከራሱ ጋር ተሟገተ። ኅሊናውና ሥጋው ሙግት በገጠሙ ጊዜ የሚይዘውንና የሚጨብጠውን አሳጡት።

ኀና ድሮ ከእስር ቤት እንደ ወጣ እኚያ የተባረኩ ጳጳስ አቀንት የሚሰብር ንግግር ባይናገሩት ኖሮ ከዚህ ዓይነቱ ግብግብ ውስጥ ባልገባ ነበር። አንደኛው ጉኑ 'የሚበቃህን ያህል ተሰቃይተሃልና አሁን ራስህን አውጣ' ብሎ ሲመክረው ሌላው ጉኑ ግን 'እንዴት ባንተ ጠሰ ሌላ ሰው ይጐዳ!' እያለ በመገሰጽ ወተወተው። ጐቬር ከቢሮው እስከ ወጣ ድረስ ስሜቱን ለመቆጣጠርና የተዝናና ለመምሰል ብዙ ታገለ። ጐቬር ከቢሮው እንደ ወጣለት ግን ቶሎ ብሎ ፋንቲንን ለማየት ወደ ተኛችበት ክፍል ሄደ። ከዚያም አንደ ደረሰ ከሌላው ቀን ይበልጥ ጊዜ ወስዶ አጫወታት። እርስዋን የሚንከባከቡ ሴሮችም የተለየ ጥንቃቄ እንዲያደርጉላት አሳሰባቸው። ቀጥሎም ምናልባት አራስ ወደሚባል ሥፍራ ሊሄድ እንደሚችል ገለጸላቸው።

ከፋንቲን ክፍል እንደ ወጣ እራት ቀርቦለት እንክት አድርጎ በላ። ከዚያም ወደ መኝታ ክፍሉ ሄዶ አሳቡን ለማሰባሰብ ሞከረ። የአረቦትን ሁኔታ በአሳብ ሲገመግመው ከዚያ በፊት ተሰምቶት በማያውቀው ስሜት ተዋጠ ። ሳያስበው በድንገት ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ተነስቶ የመኝታ ክፍሉን በር ቁለፈ። በሩ ከተቈለፈ ማንም መጥቶ ሊያስፈራራው እንደማይችል ተገነዘበ። ጥቂት ቈይቶ የክፍሉን መብራት አጠፋ። መብራት በዝቶ ስለነበር የመብራቱ ብርሃን ብዙ አናዶታል። ከዚህም በላይ መብራቱ ከጠፋ አንድ ሰው ከውጭ ሆኖ ሊያየው እንደማይችል ገመተ። ሆኖም 'ማን? የትኛው ሰው?' እያለ ራሱን ቢጠይቅም እንዳያየው የፈለገው ሰው ሁሉ አየው። የተቆለፈው በር ወለል ብሎ የተከፈተም መሰለው። ለመሆኑ በሩን ማን ከፈተው? ማንስ አየው?—ሀሊናው።

ሀሊናውና ሁሉንም የሚያይ አምላክ አየው። በመጀመሪያ ራሱን ለማታለል ሞከረ። ከተቈለፈ ቤት ውስጥ ራሱን ከደበቀ ብቻውን ስለሆነ ማንም የሚያገኘው አልመሰለውም ነበር። በሩ ተቈልፏል፣ መብራቱም ጠፍቷል። ታዲያ ማነው እርሱን ለማየት የሚችለው? ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ ይዞ ክርኑን ጠረጴዛ ላይ በማስደገፍ ከጨለመው ክፍል ውስጥ

ያስላስል ዝ። አሳቡን ለማስባስብ ብዙ ቢጥርም እንጎሉ በቂ ኃይል አጣ። ሀሊናው ውስጥ የሰፈነው አሳብ እንደ ክባድ ማዕበል ተወራጨ። በውስጡ የተንሰራፋውን አሳብ ለማስወጣትና ከእርሱ ለማራቅ ሞንትሳቱን በበለጠ ኃይል ጠበቅ አድርጎ ያዘ። ሆኖም በከፋ መልኩ በአሳብ ነጉዶ እንጂ ከተጨበጠ ውሳኔ ላይ ለመድረስ አልቻለም። እንዲያውም ከነአካቴው ሞንቀቱ እየጐሳ ሄደበት። ይባስ ብሎም ሞንትሳቱ በእሳት ተያይዞ የሚቀጠል መሰለው። ወደ መስኩት ሄዶ መስኩቱን ወለል አድርጎ ከፈተው። ወደ ሰማይ አሻቅቦ ቢያይ ከሰማዩ ላይ አንዲት ኮከብ እንኳን የለችም። ተመልሶ ሄዶ እንደ በፊቱ ሞንትሳቱን ይዞ ተቀመጠ። ሰዓቱ መንጐዱን ቀጥሎ እንድ ሰዓት አለፈ።

የተበታተነው አሳቡ ቀስ እያለ ወደ እንድ ውሳኔ ስላመራና እኚያ ካህን ባልሠሩት ሥራ የገቡበትን አሰቃቂ ወጥመድ ስላየ ከአውሬነት ባህርይና እንደ አንዳንድ የአገራችን ነገዶችና ግለሰቦች ከይሉኝታና ሀሊናቢስነት ለመላቀቅ ቻለ። ይኸኔ ነው ከቅጥት ዓለም እንደ ወጣ ያወቀው። እኚያ ደግ ሰው የእርሱን ጠስ፣ የእርሱን እዳ ተሸክመው ሲሰቃዩ በአሳብ አያቸው። እርሱ መማከት ከነበረበት አዘቅት ውስጥ ሲጣሉ በአሳብ ሲያያቸው መላ አካሉ ተሳቀቀ፣ መላ ሰውነቱም ስቅጥጥ ሲል ተሰማው። ይኸኔ የዋሁ ካህን ከዚያ የመከራ አዘቅት ውስጥ እንዳይገቡ አንድ ነገር መደረግ እንዳለበት አመነ። ይህን ሊያደርግ የሚችለው ደግሞ እርሱ ራሱ መሆኑን አልተጠራጠረም። ከእርሱስ ሌላ ማነው ይህን ሊያደርግ የሚችለው?

አሁንም ቢሆን ነገሩ ሁሉ ተምታታበት። አሁንም ቢሆን የሚችለው ጉዳይ ሆኖ አልታይህ አለው። ሀብት የትትረፈረፈው ከንቲባ ተመልሶ ወሰዱ ቤት ሊገባ ስለዚህ አሁንም ተጨነቀ፣ ተጠበበ። አንጎሉ በሞንቀትና በአሳብ ብዛት ሊፈነዳ ተቃረበ። ማንም ሰው ቢሆን ከዚያ በፊት ከእንደዚያ ያለ ፈተና ውስጥ የገባ አልመሰለውም። ሀሊናው አሳደደው፣ አረፍት ነሳው። 'ማሽላ እያረረ ይሰቃል' እንዲሉ አርሱም አንጀቱ እያረረ የፈገ ሳቅ ሳቀ። ቶሎ ብሎ ሄዶ መብራቱን እንደገና አበራው።

«ታዲያ ምን ይጠበሰ» አለ። ምን አርበተበተኝ? ምንስ አስጨነቀኝ? እኔ እንደሆነ ምንም አልሆንኩም። ነገሩ ከፍጻሜ ደርሷል። አንድ ግለሰብ በደል ቢፈጽም ጥፋቱ የእኒ አይደለም። እኔ እንደሆንኩ ክብር ያለኝ ሰው ነኝ። ይህ የፈጣሪ እንጂ የእኒ ሥራ ሊሆን አይችልም። የእርሱ ፈቃድ ይህ ከሆነ ደግሞ እኒ ምን አገባኝ? እርሱ ራሱ አስተካክሎ የቀየሰውን እኔ ምን መለወጥ እችላለሁ? ታዲያ እኒ ምን ጥልቅ ያደርገኛል፣ አያገባኝም። በሕይወት ዘመኔ፣ በሕልሜም ሆነ በውኔ፣ የተመኘሁት ነገር ቢኖር የኑሮ

ሞስትና እንዳገኝ ነበር። የአምላክ ፈቃድ ሆኖ ያንን አግኝቻለሁ። ስለዚህ በአምላክ ፈቃድ ያገኘሁትን የኑሮ ዋስትና አሁን እኒ ማበላሸት የለብኝም። ለምንድነው አሁን የደረስኩበትን መልካም ሕይወት እንዳልቀጥል ተግባር እንዳልፈጽም፣ ለሌሎች አርአያ እንዳልሆንና ያላሳኩትን የረጅም ዘመን ስታይ ውጤት ለቀረኝ የሕይወት ዘመኔ የደስታ ምንጭ እንዳይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ የማይሆነው! ለማንኛውም ይህ ያለቀ ጉዳይ ስለሆነ ከፈጣሪ ሥራ ውስጥ እኔ ለመግባት አልችልም» ሲል ተፈላሰፈ። ሆኖም ፍልስፍናው ተጨባጭ የሆነ መፍትሔ ሊያስገኝለት ስላልቻለ ከተቀመጠበት ተነስቶ ከወዲያ ወዲህ እያለ ተንቄራጠጠ። «ና ወዳጄ፣ ከዚህ ደብልቅ ራስህን አታሰቃይ» ሲል ራሱን ቢመክርም የመንፈስ እረፍትና ሰላም አላገኘም። ከመጠን በላይ ተጨነቀ። የሞንቀቱም ውጤት ብስጭት ሆነ።

ማንም የባሕር ውሃ ወደ ዳር እንዳይወጣ ለማገድ እንደማይችል ሁሉ አሳብ ሞንትሳት ውስጥ እንዳይገባም ለመከላከል አይቻልም። በኃይል እየገፋ የሚመጣውን ውሃ ማዕበል እንለዋለን። ወንጀል ሠርቶ የሚደርሰውን ሰቆቃና ሞንቀት ደግሞ የኅሊና ወቀሳ እንለዋለን። ፈጣሪ በልዩ ጥበቡ ነፍስንና ውሃን ወደ ታችና ወደ ላይ እያሳነ ያነጥራቸዋል። ጊዜው እያለፈ ሲሄድ መሴይ ማንደላይን እርስ በራሱ መነጋገሩን ቀጥሎ ተናገሪም ሰሚም ራሱ ሆነ። እጅግ በጣም የሚያሳዝነውና የሚያስገርመው ደግሞ የሚናገረው ነገር ሁሉ ለመስማት የማይፈልገውን ሲሆን ለመናገር አፉን የከፈተውም ከምን ጊዜም ይበልጥ ዐጥታ በፈለገበት ሰዓት ነበር።

«ይህ ሰው በዚያን ጊዜ የት ነበር? ይህ ጉዳይ ያለቀለት ነገር አይደለም እንዴ?» ሲል ራሱን ጠየቀ። ጥያቄዎቹን እንደ ጠየቀ «እኔን አያገኝም» ብሎ ማለፉ ልክ እንዳልሆነ የራሱ ኅሊና ነገረው። ንጹህ ሰው ባልሠራው ሥራ ከሰቃይ ማጥ ውስጥ ሲገባ ዝም ብሎ መመልከቱ ኅሊና ያለው ፍጡር ሊቀበለው የማይችል የአውሬ ጠባይ መሆኑን ለዚያው ኅሊና ነገረ። ይህን እውነታ አለማየት 'ራሰ-ወዳድ፣ ጨካኝ፣ ፈሪ፣ ወንጀለኛ ያሰኛል' ሲልም ደመደመ። በመጨረሻዎቹ ስምንት ዓመታት የሕይወት ዘመኑ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የደካማ አሳብ መራራነትን ቀመሰ። ያንን ከፉ አሳብ ከሞንትሳቱ ውስጥ አስወጥቶ ለመጣል ይችል ይመስል እየቀፈፈው ምራቁን ተፋ።

«የሕይወቴ መጨረሻ ምንድነው? ስሜን መደበቅ? ፖሊስንና ራሴን ማታለል? እስከ ዛሬ የፈጸምኩት በጎ ተግባር ሁሉ መጨረሻ ይህ ነው? በሕይወት ዘመኔ ከዚህ የተለየ ዓላማ አይኖረኝም ማለት ነው? ነፍሴን ረስቼ ሥጋዬን ብቻ ለማዳን ነው የምኖረው? ወይስ የሕይወቴ ግብ

እውነተኛ፣ ታማኝና ቀና ሰው ሆኜ መኖር ነው? ይህ አልከብረም እንዴ የእኚያ ደጉ ቋልስ የሕይወት ዓላማ! ይህ ዓላማና የሕይወት ግብ እኮ ነው እርሳቸውን ያስደሰታቸው!» ስለዚህ ከጎሊናው ጋር ዳግም ተሟገተ። ከራሱም ጋር ባደረገው ሙግት ራስን ለማውጣት ሲባል የሌላውን ሕይወት ማበላሸት ትክክል እንዳልሆነ አጤነ፣ አወቀም።

«የዚያን የቀህ ካህን ሕይወት ካላዳንኩ ምን ሰው ነኝ?» ሲል ራሱን ጠየቀ። ይህን ካላደረገ ሰው ሳይሆን ነፍሱን የረሳና እድገቱን ያልጨረሰ የሰው አውሬ ሆኖ ሊቀር እንደሚችል ለራሱ ነገረ። የሰው ልጅ ደግሞ ለራሱ ብቻ የሚኖር ከሆነ መኖር ራሱ ትርጉም የለውም። ለራስ ብቻ የሚኖር ሰውስ 'ሰው ነው' ለማለት ያስደፍራል! ብሎ ሲናገር እኚያ ደጉ ቋልስ ከአጠገቡ ቁጭ ብለው የሚሰሙትና የሚያዩት መሰለው። በአካባቢው ያሉ ሰዎች ሁሉ የሚ.የውቁት እንደ ተወዳጅ ከንቲባ ሲሆን ቋልሱ ግን የሚያውቁት ከእስር ቤት ያመለጠው ዣን ቫልዣ እንደሆነ ነው። በአካባቢው ያሉ ሰዎች ሁሉ ያዩትና የሚያዩት የውጭ አካሉንና ኦሮውን ሲሆን እኚያ ቋልስ ግን የውስጥ አካሉንና ጎሊናውን ነው ያዩትና የሚያዩት። እውነታው ይህ ከሆነ ሳያመነታ ቶሎ ብሎ ወደ አራስ ሄዶ ምስኪኑን ካህን ማዳን አለበት። ትክክለኛውን ዣን ቫልዣ አጋልጦ የውሸት ዣን ቫልዣ የሆነውን ሰው ማዳን ግዴታው ነው። ይህን ካደረገ ታላቅ መስዋዕትነት የከፈለ ቢሆንም አለከፊ ድል ይሆንለታል። ያም ሆነ ይህ ክቡር ጎሊናው የሚነግረውን ማድረግ እንዳለበትና ወደ ቋላ ማለት እንደሌለበት መሴይ ማንደላይን አሁንም ለራሱ ነገረ።

እጅግ አሳዛኝ የሆነ መጨረሻ! በዳኞች ሳይሆን በጎሊና ዳኝነት ብቻ ያን ሁሉ ሀብት፣ ያን ሁሉ የምኞትና የተንደላቀቀ ሕይወት መሰዋዕት አድርጎ በገዛ ፈቃድ፣ ማንም ሳያስገድድ የምስኪኑን ካህን ሕይወት ማዳንና የራስን ሕይወት አሳልፎ መስጠት! ይህስ በሰዎች ዓይን የሚያስነቅፍ ውሳኔ ነው ወይስ 'እውብ፣ ድንቅ ሥራ' ያሰኛል?። አንባቢ ምን ይላል?

«ይሁና!» አለ እውነተኛው ዣን ቫልዣ። «መደረግ ይኖርበታል፣ ይህን ሰው ማዳን አለብኝ።» እነዚህን ቃላት የተናገራቸው ሳይታወቀው በኃይል እየጮኸ ነበር። በዚህም የባባበትንና ተሰንጎ የተያዘበትን ወጥመድ በይበልጥ ጐላበት። ከቅዠት ዓለም በትክክል መንቃቱን ስላወቀ አሁንም እኚያ ምስኪን የአርሱን ጠሰ፣ የአርሱን እዳ እንደ ተሸከመ በጥራት አያቸው። ከጠረጴዛው ላይ የነባሩትን መጻሕፍት, ሩቱንም እቃዎች በመልክ በመልኩ አስቀመጠ። አንዳንዶቹን እሳት ውስጥ ጨመራቸው። ወረቀት አውጥቶ ደብዳቢ ጻፈ። ደብዳቢውን ፖስታ ውስጥ ጨምሮ አሸገው።

ከፖስታው ላይ የአንድ የታወቀ ባንክ ሥራ አስኪያጅ አድራሻ ጻፈበት። ደብዳቤውንና የማስታወሻ ደብተሩን ከኩቱ ኪስ ውስጥ ካደረገ በኋላ ዳግም ከውጪያ ወዲህ መንቆራጠጥ ጀመረ።

በጎሊናው ዳኝነት የወደፊት ሕይወቱን የሚወስንበት ሰዓት ተቃረበ። ከአስር ቤት ለመጨረሻ ጊዜ ካመለጠ ወዲህ አዲስ የሕይወት ምዕራፍ የከፈተለት እኚያ የሃይማኖት ሰው ነበሩ። አሁን ደግሞ እኚህ ሻምፕማትዩ የሚባሉ የሃይማኖት ሰው ሁለተኛውን የሕይወት ምዕራፍ ሊከፍቱለት ነው። ከትልቅ ጭንቀት በኋላ የደረሰበትን አስከፊ ጽዋ ለመቅመስ ሲዘጋጅ እሁለ-ሌሊት አለፈ። አሁንም ከወዲህ ወዲያ መንቆራጠጡን ቀጠለ። ብርድ ብርድ አለው። አሳት አቀጣጠለ። መስኩት መዝጋት እንደ ነበረበት ዘነጋቷል። 'ሂድ፣ ወደ ኋላ አትበል፣ ራስህን በማጋለጥ ምስኪኑን ሰው ከልሠራው ወንጀል ነፃ አውጣው፣ ካላጠፋው ጥፋት አድነው' የሚለው ደወል ከጆሮው ውስጥ አቃጨለ። «ራሴን ለማጋለጥና ስውሬውን ለማዳን ወሰንኖለሁ» ሲል አሁንም ሳይታወቀው ተናገረ። በዚህ ጊዜ ነበር የፋንቲን ጉዳይ ከፊቱ ድቅን ያለበት።

«ቆይ እስቲ፣ ይህች ምስኪን ሴት ደግሞ ከእዚህ አለች። እርስዋስ እንዴት ትሆናለች?» ጨርሶ ያላጤነው ሌላ ችግር ተፈጠረ። «እስከ ዛሬ ለራሴ ብቻ ነበር የምኖረው። ቢደላኝ፣ ቢከፋኝ፣ ራሴን ላጋልጥ ብል፣ ለነፍሴ ሳይሆን ለሥጋዬ ባድር ውሳኔዬን ለማዛባት መንገድ የሚዘጋብኝም ሆነ ከፊቴ ላይ የሚደቀን ነገር አልነበረም። ለራስ ኖሮ ለራስ መወሰን ነበር ሕይወቴ። ለዚህም ነበር ራሴን ለማጋለጥ የወሰንኩት። አሁን ግን ይህቺ ሴት ከመንገዴ ላይ ልትቆም ነው እንዴ? ለካስ እስከ ዛሬ ስለሌሎች ብዙም ሳላስብና ሳልጨነቅ መኖሬ ጠቃሚ ነበር ማለት ነው! ወይስ ራሴን ከመጠን በላይ ነበር የምወድደው? ግን እኮ ለሌሎች መኖር ታላቅ ክብር የሚያሰገኝ ከመሆኑም አልፎ ከሥራዎች ሁሉ ይበልጥ ክብር የሚያሰጥ መንፈሳዊ ተግባር ነው።

«እስቲ አሁን ያለሁበትን ሁናቴ በንጹህ ልቦና እንየው። ባለፉት አስርተ-ዓመታት ከአስር ሚሊዮን ፍራንክ በላይ የሚሆን ሀብት በማፍራቴና የተለያዩ ፋብሪካዎችን በመክፈቴ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ቤተሰቦች በደስታ ሊኖሩ ችለዋል። በዚህም አገሪትዋ ሞምር ተጠቅማለች ለማለት ይቻላል፣ ምክንያቱም የተወሰኑ ሰዎች ሕይወት በእኔ ምክንያት በመሻሻሉ ውንብድና፣ ዝሙት-አዳሪነት፣ ሌብነት፣ ነፍስ የማጥፋት ወንጀልና የመሳሰሉት የጎብረተሰብ አሚከላዎች በተወሰኑ አካባቢዎች ተቀንሰዋል። እነዚህ ችግሮች ከማጣት ጋር ዝምድና እንዳላቸው እውን ነው። ታዲያ

ለሌሎች መኖር ማለት ይህ አይደለም እንዴ? እነሆ ራሴን የማጋልጠው ይህን ሁሉ ሕዝብ ለማን አደራ ብዬ ነው! እኔ ከሃድኩ ሥራዬ ሁሉ ዲቃውላ። ሥራዬ ከተቃወለ ደግሞ ሠራተኞቼ ሁሉ የትም ሊበተኑ ነው። የቤተሰቦች ትዳር እንዳይፈርስና ልጆቻቸው የሰው እጅ እንዳያዩ፣ እናቶች በነፃቀን ማጎፀናቸው እንዳይደርቅ፣ ሌብነት እንዳይስፋፋ ብዬ ራሴን ሳላጋልጥ ብቀር ምሥጢሬን የሚያውቁ ሰዎች ቢፈጠሩ እነርሱ ዓይነት ጥሣ ነው እባካችሁ!»

እንደኛ ብድግ ብሎ ተነስቶ መንጐራደድ ጀመረ። አሁን ግን የሚንጐራደደው እንደ በፊቱ ከጭንቀት ማጥ ውስጥ ገብቶ በመርበትበት ሳይሆን በረጋ መንፈስ ነበር። እንቁ ጨለማ ከወረረውና ጥልቀት ካለው መሬት ውስጥ ተፈልፍሎ እንደሚገኝ ሁሉ አውነትም ከማሰብና ከማሰላሰል ብዛት ይደረስቢታል። ከንቲባውም ከመጨነቅ፣ ከመጠበብና ከማሰብ ብዛት ከሕይወት እውነታ ላይ የደረሰ መሰለው። ነገር ግን አሁን ያየው የሕይወት እውነታ ትክክለኛውን ጐዳና እንዳያይ የጋረደበት መሰናክል ነበር።

«አልተሳሳትኩም፣ ይኸው ነው ትክክለኛ ጐዳና» ሲል ተናገረ። «ትክክለኛውን አቅጣጫ ነው የያዝኩት። ለጭንቀቴም መፍትሔ አገኘሁለት። ከዚሁ አሳብ ላይ ነው መጽናት ያለብኝ። ምርጫዬ ይኸው ስለሆነ ወስኛለሁ። ከእዚህ ወዲያ ስለዚህ ጉዳይ እያሰለሰሉ መጨነቅ አያስፈልግም። ይህንንም የምለው ለራሴ ብቻ በማሰብ ሳይሆን ለኅብረተሰቡም ጭምር በመጨነቅ ነው። እኔ ማንደላይን ስለሆንኩ በማንደላይንነቴ እጸናለሁ። ይብላኝ ለጐን ቫልዣ! ከአሁን ጀምሮ እኔና ዣን ቫልዣ አንድ አይደለንም። የጐን ቫልዣን ማንነት እኔ አላውቅም። 'ጐን ቫልዣ ነው' ተብሎ የተጠረጠረው ሰው ራሱን ያውጣ እንጂ እኔ ምን አገባኝ። የምን የእርጎ ዝንብ መሆን ነው! አምን፣ ከዚህ ውሳኔና መደምደሚያ ላይ በመድረሴ መንፈሴ ረክቷል። አሁን ሸ የተሰየሁ ሰው እንደሆንኩ ተረድቻለሁ።» ጥቂት እንደ መረመደ ብሎ በደንብት ቀጥ ብሎ ቆመ።

«ኧረ ወዲያ» አለ። «ከዮጉ መፍትሔ ላይ ነው የደረስኩት። ካሁን በኋላ ከዚህኛው ውሳኔ ነቅንቅ አልልም። ብቻ እኮ አሁንም ቢሆን አሳቡ ከሃሊናዬ ውስጥ ዉጪ አልተነቀለም። ስለዚህ በቶሎ ተንቅሎ መውጣት ይኖርበታል። ከእዚህ ነፍስ ውስጥ እንደ ምስክር ሆነው ሊናገሩ፣ ባየኋቸው ቁጥር የዚህችን ሶኅት ሚንቀቂቲን ሊያስታውሱ የሚችሉ ብዙ እቃዎች ሁሉ አሉ። ብቻ ሳይሆን እነርሱም መወገድ አለባቸው።» ኪሱን ዳብሶ ከርሳውን ነጨጣ በኋላ ከሙሰጡ አንዲት ትንሽ ቁልፍ አወጣ። በግድ

ከምትታይ የቁልፍ መግቢያ ቀዳዳ ውስጥ ቁልፉን አስገብቶ ካጠገቡ የነበረውን ሳጥን ከፈተው። ሳጥኑ ውስጥ ብዙ እቃ አልነበረም። ያረጀ ሱሪ፣ የተበጣጠሰ ጫማ፣ የተቀዳደደ ሸሚዝ፣ እንዲሁም እርጌ ኮሮጆ መሳይ ነገርና ያኔ አሁን ወደሚገኝበት ከተማ ሲገባ ይዞት የነበረው ጻሃ ከሳጥኑ ውስጥ ተቀምጠው አገኛቸው። እቃዎቹን ሲያይ መቼ እንዳስቀመጣቸው አስታወሰ። ወደ በሩ ተመለከተ። ምንም እንኳን በሩ በሚገባ ተቀርቅሮ ቢዘጋም የሚከፈት መስሎት ፍርሃት ፍርሃት አለው።

ከሳጥኑ ውስጥ የነበሩት ልብሶቹን፣ ጫማውንና ጹላውን በቅጡ ሳይመለከታቸው ቶሎ ብሎ ከእሳት ውስጥ ጨመራቸው። እስከዚያች ሰዓት ድረስ ግን በከብር ነበር ያስቀመጣቸው። በጥቂት ሰከንድ ውስጥ ከፍሉ በብርሃን ተሞልቶ ወገግ አለ። ከእሳት የጨመራቸው ነገሮች ሁሉ ጋዩ። ጹላው እየተሰነጣጠቀ ሲነድ የእሳት ብልጭታ ራቅ ወዳለው ጦፍራ ሁሉ ይበተን ጀመር። እቃዎቹ የነበሩበት ከረጢት ነድዶ ሲያልቅ የሆነ የሚያብረቀርቅ ነገር ካመዱ ውስጥ ታየ። መሴይ ማንደላይን ዉጋ ብሎ ሊመለከት የብር እቃ መሆኑን ተገነዘበ። ኪቃጠላቸው እቃዎች አንዱ ከእኛ ደጉ ጳጳስ ቤት የሰረቀው እቃ ለመሆኑ ታወሰው። ይህን ባስታወሰ ጊዜ ወደ እሳቱ መመልከቱን ትቶ እርምጃውን ላያዛባ ከወዲህ ወዲያ መንቄራጠጡን ቀጠለ። ሆኖም አላስችል ብሎት ወደ እሳቱ ዓይኑን ቢያዞር ተብለጭልጨው ያያቸው ነገሮች እነዚያ ሁለት ከብር የተሠሩ የሻማ መብሪያዎች መሆናቸውን አረጋገጠ።

«ቆይ እስቲ» በማለት ወደ አሳቡ ተመለሰ። «ዣን ቫልዣ ግን እንደሆነ የሻማ ማብሪያዎቹም ስለሚያስታውሱ እነርሱም ከዝምድና መቆጥት አለባቸው» ሲል ከራሱ ጋር ተሟገተ። ነገር ግን እሳቱ ኃይለኛ ስለአነር ሊያቀልጣቸው ካልሆነም ደብዛቸውን አጥፍቶ ሊያበላሻቸው እንደሚችል ስለገመተ የሻማ ማብሪያዎቹን ለመመርመር ከእሳት ማንደጃው ቀስ ብሎ አወጣቸው። የሻማ ማብሪያዎቹን ለማሠጣት ወደ እሳቱ ጢጋ ባለጊዜ የእሳቱ ወላፈን ሰውነቱን ስላሞቀለት 'እንዴት ደስ ይላል' ሲል ተናገረ። የሻማ ማብሪያዎቹን እያገላበጠ አያቸው። እነርሱን እያየ ለተጨማሪ እንድ ደቂቃ ቢቆይ መልሶ እሳቱ ውስጥ ነብር የሚወረውራቸው፣ ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ወዲያው 'ዣን ቫልዣ፣ ዣን ቫልዣ' በማለት የሆነ ሰው የተጣራ ስለመሰለው ጆሮውን አቀና። ዙጉሩ ቆመ። መርዶ የተነገረውም መሰለው። ግራ ተጋባ።

«አዎን፣ ይኸው ነው የሚሻለው፣ ነገሩ ሁሉ አልቋል» በማለት 'ዣን ቫልዣ፣ ዣን ቫልዣ' ሲል የተጣራው ድምፅ ንግግሩን ቀጠለ።

ስላስገረመው ከት ብሎ የቲል ሳቅ ሳቀ። 'ምን ንደነት ጅል ፍጡር ነሽ አባካችሁ! ከዚህ ክፍል ውስጥ ማንም ሊገባ እንደማይችል እያወቅሁ' ሲል ቀባጠረ። ቢሆንም ለሰዎች ዓይን ጉልህ ያልሆነ ኃይል ከዚያ ክፍል ውስጥ እንደነበረ ግን አልተጠራጠረም። የሻማ ማብሪያዎቹን ከፍ ካለ ሥፍራ ላይ አስቀመጣቸው። በመፈራረቅ ተራ እየገቡ የሚጫወቱበትን ሁለቱን አሳበች አገናዘበ። ሁለቱም አሳቦች አንዱ ካንዱ እንደማያሻልም ተረዳ።

ሻምፕማትዩ 'ጎርን ቫልገር ናቸው' ተብሎ በጥርጣሬ መያዛቸው ምን ዓይነት አጋጣሚ እንደሆነ አስደነቀው። ስለወደፊት ሕይወቱ በድጋሚ ማሰላሰል ጀመረ። ራሱን ያጋልጥ! ስንቱን ሰው ሚዳ ላይ ጥሎ! ስንቱን ሰው የገበያ ላይ ድንጋይ አድርጎ! ለራሱስ ቢሆን ያን ሁሉ ከሸፌታ፣ ያን ሁሉ ሀብትና የምኞት ሕይወት! ያን ሁሉ የሰው ፍቅር! ይህን ሁሉ መለዋዕት አድርጎና ትቶ ከእስር ቤት ውስጥ በመግባት በእግር ብረት ይታሰር! ከጨለማ ቤት ይግባ! ይሰቃይ! ከቀዝቃዛ ስሚንቶ ላይ ይተኛ! የእስር ቤት ኑሮ ስቃይ ምን እንደሚመስል ለአሥራ ዘጠኝ ዓመት የቀመሰውና ያየው ሲሆን ተንገሽግሾ የወጣበት ነው።

«ምን ዓይነት ርግማን ነው እባካችሁ! የሕይወት ብያኔ እንደ አዋቂ ሰው ተንኰለኛና እንደ ሰው ልብ ምቀኛ ይሆናል? ሰው ከእንዲህ ያለ ወጥመድ ውስጥ ገብቶ መውጫና መግቢያ ቀዳዳ ያጣል? መንግሥተ-ሰማይ ገብቶ ሰይጣን መሆን ወይስ ገሃነም ገብቶ መልአክ መሆን!» ካለ በኋላ «የፈጣሪ ያለህ፣ የቱ ይመረጣል? ምንስ ይደረጋል?» ሲል ራሱን ይዞ ጮኸ።

ስቃዩ እንደገና በረታበት። እንደ አዲስ ነገርም ክፉኛ አስጨነቀው። ከትልቅ ገበቴ ወይም ሳፋ ላይ እንደ ተቀመጠ ውሃ በአሳብ ዋለለ። ተስፉ ሲቆርጡ እንደሚታየው፤ በቃላት ለመግለጽ እንደሚያስቸግረውና እንዲያው ዝግ ብሎ ቅርጽ እንደሚያወጣ የተምታታ አሳብ የሆነ ነገር ከፊቱ ላይ ድቅን ስላለ ከመዳህ ቆሞ መሄድ እንደ ጀመረ ሕፃን ተንገዳገደ። በዚያች ሰዓት ሁሉም ነገር የደበዘዘ እንጂ ጉልህ ሆኖ አልታየውም። ኮጮንቅላቱ የሚፈልቁ አሳቦች እንደ ጢስ የተነኑ እንጂ ተሰባስበው ቅርጽ ያላቸው ስላልነበሩ ምንም ነገር ጉልህ አልሆነለትም። ቁኝም ነፈሰ ግራ፤ ጉልህ ሆኖ የታየው ነገር ቢኖር የቁም ስቃይ መቀበሉን ብቻ ነበር። ሁሉም ነገር 'በሕይወት እያሉ መሞት፣ እየተነፈሱ መቀበር' ሆነበት። ስለዚህ ዳግም ከጀመረበት ተመለሰ። ይህ ያልታደለ ሰው ነፍስ ከአሳብ አለንጋ ግርፊያ መላቀቅ ስላልቻለ በአሳብ መዋተቱን ቀጠለ።



...ደጅመርከሙን ብትጨርስ ይበጅሃል፣ የሻማ ማብሪያዎቹንም አቃጥላቸው። እኔስ እንተነትህን የሚያስታውሱ ስለሆኑ ደብዛቸውን አጥፋ። እኚያ ፈጣኖም እርሳቸው። እርሳቸውን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ነገር እርሳ እንጂ ለማስታወስ አትሞክር። በሻምፕማትዩ ሕይወት ላይ ፍረድ፣ አምን ብትፈርድባቸው ይሻልሃል። ብራቮ፣ መልካም ሥራ! ይኸው ነው የሚሻለው፣ ነጭ ሁሉ አልቂል። ምን አለበት፣ ምናልባት ካህኑ ንጹህ ሰው ሊሆኑ ይችላሉ። ታዲያ ምን ይጠበስ? እድላቸው ሆነና በአንተ ስም ተጠርተረው ከአሳስል አዘቅት ውስጥ ይጣሉ ይሆናል። የአንተን ኃጥያት በመሸከማቸውም መጨረሻቸው የከፋ ሆኖ የስቃይና የመከራ ዘመን ያሳልፋሉ። ምን አለ ታዲያ፣ ይሁና፣ እድላቸው ነው። እንተንማ ሰዎች በይበልጥ ሊያከብሩህና ሊመልኩህ ነው።

'እንተን ያኑርልን፣ ሺህ ዓመት ከንቲባ ሁነህ ኑርልን፣ የተጠማን አጠጣልን፣ የተራበን አብላልን፣ የታረዘን አልብስልን፣ ቤተሰባቸውን ያጡ ፈቾን ጡርልን። ተባረክ፣ የሰው ፍቅር አይለይህ' እያሉ ያሞካሹሃል። ሆኖም እንተ ከዚህ ሁነህ ስትደሰት፣ ስትዝናና አንድ ሰው ግን የአንተን የትናንትና ፊተኛ ሰብእና ባለማወቅ ስምህን ወርሶ የአንተን የኃጥያት ሰንሰለት እየጐተተ ጨማ ውስጥ ለዘላለም ይኖራል። እውብ ድንቅ ሥራ! እንዴት ያለ ድርድር ነው እባክህ አንተ ርኩስ፣ የሚለው ድምፅ ጆሮው ውስጥ ሲያቃጭል ፊቱ ሰብኖ ተጠመቀ። ልቡም በኃይል መታ። የሻማ ማብሪያዎቹን በደበዘዘ ዓይኑ እንደገና ተመለከታቸው። ከውጭ ሳይሆን ከውስጡ የሚወጣው ይህ ድምፅ አፈተፍረጠም፣ ንግግሩን ቀጠለ።

«ነገን ቫልገር፣ ቃላቸውን ከፍ አድርገው የሚናገሩ ብዙ ድምፆች ይኖራሉ። ድምጾች ለዘላለም እየጮሁ አንተን ያሞግሳሉ። ሆኖም ከእነዚህ ድምፆች መካከል አንዱ ብቻ ሊሥራ ድምፆች ሳይሰሙት አንተን ያሳድድሃል። ከፈረሰማ ውስጥ ብትሸሽ እንኳን ይከተልሃል። 'ስማ አንተ ርኩስ! አንተ የተረገምክ፣ ይኼ ሁሉ ሙጥጥ፣ ይኼ ሁሉ አክብሮትና አድናቆት ለአንተ ደንቆሮ! እያለ ይጠይቅሃል። ሆኖም ይኼ ሁሉ ሙገሳና ክብር ከሰማይ ቤት ሳይኦርኒ ምድር ላይ ተቀብሮ ይቀርና ለዘላለም ይጠፋል። ርግማኑ ግን እስከ ንጥአላህሌር ረት ድረስ ይከተልሃል።» ስውር ጎሊናው ውስጥ በቀስታና ሰውነቃ ጀምሮ የሚያቃጭለውና እፍ አውጥቶ የሚናገረው ድምፅ ቀስ እያለ እያነሳሳ ለጆሮው እየቀረበ መጣ። ያ ድምፅ ንግግሩን ሲጀምር ከራሱ ጋራ የሚጨዋ መሆኑን ቢታወቀውም ከቃላቱ ኃይለኛነት፣ ከድምፁ ጥራትና ንጹህነት የተነሳ እሥጋትም ከአጠገቡ ቆሞ የሚገስጸው ስለመሰለው ከነበረበት አቶ ሞገሙ ሲፈ ተጣራ። ቢሆንም ድምፁን ከፍ አድርጎ መጣራቱ እጅግ

2

ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ሆነ። ላለፉት አምስት ሰዓት ቂጡ መሬት ሳይነካ ከወዲህ ወዲያ እያለ ነው የቆየው። ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ግን ሰውነቱ ሁሉ ስዛለ ከወንበር ላይ አረፍ አለ። ወንበር ላይ እንደ ተቀመጠ ለካስ እንቅልፍ ወቢዶት ኖሮ የማይሆን ቅዠት ቃዠ። እንደ ማንኛውም ቅዠት በሕልሙ ያየው ቀደም ሲል ጎሊናውን ስላስጨነቀበት ጉዳይ ነበር። ሕልሙ፣ ምንም እንኳን ቅዠት ቢሆንም፣ በይበልጥ እንዲያስብና እንዲጨነቅ አደረገው እንጂ እረፍት አልሰጠውም። ወደ አራስ ጉዞ ከመጀመሩ በፊት በእጁ ጽፎ ስላስቀመጠው አሳብ ነበር በሕልሙ ያየው። በወረቀቱ ላይ ጽፎ ያስቀመጠ ውን አሳብ እንዳለ ብናስቀምጠው ምናልባት ሳይጠቅመን አይቀርም። የዚህን ሕልም ፍሬ አሳብ ሳናክል ብንቀጥል በዚያን እለት ምሽት የሆነውን ታሪክ በቁንጽል ማስቀረት ይሆናል። ያየው ሕልም እንበለው ቅዠት እንዲት የታመመች ሴት ስለገጠማት የሕይወት ውጣ ውረድ የሚያወሳ ነበር። ያ ታሪክ ቀጥሎ የተነገረው ሲሆን ከፖስታ ላይ የጻፈው ቃል 'በዚያን እለት ምሽት ያየሁት ሕልም' የሚል ነበር። ሕልሙም፦

«ከአንድ ትልቅ እርሻ ውስጥ ነበርሁ። ከዚያ እርሻ ውስጥ ሳር እንኳን በቅሎ አይታይም። ሰዓቱም ቀን ይሁን ማታ አይታወቅም። እኔና የልጅነት ወንድሜ ከእርሻው ውስጥ አብረን እንጓዛለን። ሀኖም አብሮኝ ስለሚጓዘው ወንድሜ ብዙም የማውቀው ነገር የለም። መልኩ እንኳን በቅጡ ትዝ አይለኝም። ቢሆንም ግን ብዙ እናወራለን። ድሮ ስለምናውቃትና ዘወትር መስኮት ስለምትከፍትልን ጉረቤታችን ነበር የምናወራው። እያወራን ሳለ በተከፈተው መስኮት በኩል በሚገባ ነፋስ የተነሳ ብርድ ብርድ እንዳለን አስታውሳለሁ። ከእኛ ጋር የሚጓዙ ሌሎች ሰዎችም ነበሩ። የሚገርመው ከእርሻው ውስጥ ዛፍ የሚባል ነገር የለም።

«አንድ ሰው በአጠገባችን ሲያልፍ አየን። ሰውዬው ራቆቱን ነው የሚጓዘው። ምንተ-አናረቱን የሚሸፍንበት ልብስ እንኳን አልለበሰም። መላ ሰውነቱ ሁሉ የጠቆቈረ ሲሆን አፈርማ ቀለም ካለው ፈረስ ላይ ተቀምጧል። ፀጉሩ መላጣ በመሆኑ ከራስ ቅሉ ውስጥ የነበሩ የደም ሥሮች ጉልተው ይታያሉ። ሰውዬው እንደ ብረት የከበደ ዱላ በእጁ ይዟል። በአጠገባችን ሲያልፍ ቃል ሳይተነፍስ ነው የሄደው።

«'ሙር ባለው በዚያኛው መንገድ እንሂድ' አለኝ ወንድሜ። እርሱ ያመላከተውን መንገድ ተከትለን ተጓዝን። ሊያደናቅፈን የሚችል ዛፍ ወይም ቁጥቋጦ ስለሌለ በአካባቢው የሚታየው ቀይ አፈር ብቻ ነው። አየተረመጠን ስለምንሰነገረው አስተያየት አሳብ የሚሰጠን ሰው አላገኘንም።

ሥር ብዙ ባይ ወንድሜ ከአጠገቤ ሄዷል። በሩቁ ወደሚታይ መንደር አመራሁ። ያ መንደር እኚያ ካህን የታሰሩበት ከተማ መሰለኝ። ከከተማው ወደሚያስገባ መንገድ ስጠጋ ያ ከተማ ጭር ማለቱን ተገነዘብኩ። ወደ ሌላ አቅጣጫ የሚወስደውን መንገድ ለመያዝ አቋርጬ ተሻገርኩ። ከሁለት መንገዶች መገናኛ አጠገብ አንድ ሰው ግደግዳ ተደግፎ ቆሟል። 'ይህቺ ከተማ ማን ትባላለች?' ብዬ ስጠይቀው መልስ አልሰጠኝም። ይህ ሰው ከቆመበት ሥፍራ አጠገብ የሆነ ቤት በር ሲከፈት ስላየሁ ዘው ብዬ ገባሁ። ከገባሁበት ክፍል ውስጥ ሰው ስላልነበረ ወደሚቀጥለው ክፍል አመራሁ። ከዚያ ክፍል ውስጥም አንድ ሰው ግድግዳ ይዞ ቆሞ አየሁ። 'የማን ቤት ነው? እኔስ የት ነው ያለሁት?' ስል ጠየቅሁት። ይህም ሰው መልስ አልሰጠኝም። ከእዚያ ቤት ቅጥር ግቢ የአትክልት ሥፍራ ስለነበር ወደ አትክልቱ ሥፍራ ሄድኩ። የአትክልቱም ሥፍራ ጭር ያለ ሲሆን አዙንም ዛፍ ተደግፎ የቆመ ሰው አየሁ። 'ይህ ቤት የማን ነው? እኔስ የት ነው ያለሁት?' ስል ጠየቅሁት። እርሱም መልስ አልሰጠኝም።

«ከዚያ ቤት በቶሌ ወጥቼ መንገዴን በመቀጠል ከመንደር መንደር ዞርኩ። ያለፍኩባቸው መንደሮች ሁሉ ጭር ያሉ ናቸው። ድምፅ የሚባል ነገር ጨርሶ አይሰማም። ከወዲያ ወዲህ ውር ውር የሚል ወፍ እንኳን የለም። ነገር ግን ያጋጠሙኝ ቤቶች በሮች ሁሉ ክፍት ሲሆኑ በየመንገዱ ጥግና ከየቤቱ ግድግዳ አጠገብ ሰው ቆሟል። እነዚያ የቆሙ ሰዎች ሁሉ ቃል አይተነፍሱም። የሚደንቀው ደግሞ ከቆሙት ሰዎች መካከል ሁለቱን በአንድ ጊዜ ለማየት አይቻልም፤ እነርሱም አይተያዩም። እኔ ግን ባጠገባቸው ባለፍኩ ቁጥር ሁሉም አተኩረው ያዩኛል።

«ከከተማው ወጣሁና በአካባቢው ወደሚገኝ ሜዳ ለመሄድ መንገዴን ቀጠልኩ። ጥቂት እንደ ተጓዝኩ ወደ ኋላ ዞር ብዬ ሳይ ብዙ ሠራዊት ተከትሎኛል። በየመንገዱና በየጥሻው ስር ቆመው የነበሩ ሰዎች ናቸው የተከተሉኝ። ትኩር ብዬ ስመለከታቸው የፊት ገጽታቸው የተለየና አስገራሚ ፍጡሮች እንደሆኑ ተገነዘብኩ። የተቻኮሉ አይመስሉም፤ ነገር ግን ከእኔ ይበልጥ በፍጥነት ነው የሚራመዱት። ሲራመዱ ድምፅ አያሰሙም። ወደ ግራና ቀኝ ሳይ በድንገት ሲከቡኝ አየኋቸው። ፊታቸው ቀይ አፈር ነው የሚመስለው። ወደ ከተማው ስገባ በመጀመሪያ ያነጋገርኳቸው ሰውዬ 'ወዴት ነው የምትሄደው? ከሞትክ መቆየትህን አታውቅም እንዴ?' ሲሉ ጠየቁኝ። መልስ ልሰጣቸው አፌን ስከፍት ከአጠገቤ ሰው የለም።»

መሴይ ማንደላይን በጣም በርዶት ከእንቅልፉ ነቃ። ተከፍተው የነበሩትን መስኮቶች ውርጭ ያዘለ አየር ያውዛውዛቸዋል። አሳቱ ጠፍቷል። አካባቢው

መሴይ ማንደላይን ፍርድ ቤቱ ውስጥ ችሎት ከማካሄዱበት አዳራሽ ገባ። አዳራሹ ጢም ብሎ ሞልቷል። ከጠቡቆች እነሰተኛ ደጋፊ ባለተቀር ብዙ ጫጫታ የለም። ችሎቱ ቀደም ሲል የሌሎች ሰዎችን ጉዳይ ካዳመጠ አሁን የሚነጋገረው 'ፍራፍሬ ሰርቀዋል' ስለተባሉት ስለሻምፕግኖቹ ነው። እኚህ ሰው በአርግጥ ፍራፍሬ ለመስረቃቸው ማረጋገጫ አልተገኘም። ማረጋገጫ የተገኘለት ወንጀላቸው ግን ከእስር ቤት ግምለጣቸው ነበር። ምርመራው ቀጥሎ የምስክሮች ቃል ተሰምቷል። አሁን የሚጠበቀው የአቃቤ ሕግ ክርክርና የዳኞች ውሳኔ ሲሆን አዝማሚያው በካስት ላይ ከባድ ቅጣት እንደሚጣል ነው። ጠበቃቸው ግን በጣም ጉበዝ ስለነበር ከዚያ በፊት እርሱ በያዘው ጉዳይ ተረትቶ አያውቅም። ሰውዬው ጠቢቃ ብቻ ሳይሆን ጥሩ ጸሐፊም ነው።

የሥነሥርዓት አስከባሪዎች አለቃ በሩን ከፍቶ እንደ ገባ መሴይ ማንደላይን «ጉበዝ አንዴት ነው፣ ልገባ እችላለሁ?» ብሎ ሲጠይቀው «አይቻልም» በማለት ኃላፊው መለሰለት።

«ለምን?» ብሎ መሴይ ማንደላይን ሲጠይቅ «ምክንያቱም ቤቱ ሙሉ ስለሆነ መቀመጫ የለም» አለው።

«ምን ማለትህ ነው? አሁን አንድ መቀመጫ ጠፍቶ ነው?» ብሎ ሲጠይቀው «አንድ መቀመጫ! በሩ የተዘጋው ሌላ ሰው እንዳይገባ ለማሳሳብ ስለሆነ ካሁን በኋላ ሰው አይገባም» ሲል መለሰለት። ሆኖም የጠቅላዎች ኃላፊ ጥቂት ቆይቶ «በእርግጥ ዳኞች ከተሰየሙበት አካባቢ ሁለት ወይም ሦስት ሰው የሚያስቀምጥ ቦታ አለ። ነገር ግን ከዚያ ቦታ እንዲቀመጡ የሚፈቀድላቸው የመንግሥት ባለሥልጣናት ብቻ ናቸው» ሲል ተናገረ። ኃላፊው ይህን ተናግሮ ወደ ሌላ አቅጣጫ ሄደ። ይህን ጊዜ ኃላፊው ያነጋገረው ሰው ወረቀትና ብዕር ከኪሱ አወጣ። ቀጥሎም መብራት ኖላ ብሎ ወደሚታይበት ጠጋ አለ።

«መሴይ ማንደላይን – የሞንቴስ ሱር ሞንቴስ ከንቲባ» ብሎ ከጸደ ይኋላ ሕዝቡን አልፎ የሥነሥርዓት አስከባሪዎች አለቃ ወደ ሄደበት አቅጣጫ ሄዶ የያዘውን ወረቀት ለኃላፊው ሰጠውና 'ይህን ወረቀት ለመፃል ዳኛው ስጣችው' አለው። ኃላፊውም ጽሑፉን ከተመለከተ በኋላ ለዳኛው ሰጣቸው። የሞንቴስ ሱር ሞንቴስ ከንቲባ ሰው ሁሉ ያከብረውና ያደንቀው ግለሰብ እንደሆነ ዳኛው ገመቱ። ባለፉት ሰባት ዓመታት ሰውዬው በሚኖርበት አካባቢ ብቻ ሳይሆን በመላ አገሪቱ ዝናው የገነነ ሰው መሆኑን ያውቃሉ። ዝናው እንደ ገነነ በወዙ ሰው ያውቃል።

ስላጨለመ አለመንጋቱን መሴይ ማንደላይን አወቀ። ተነስቶ ወደ መስኮቱ ሄደ። ሰማይ ላይ ከዋክብት አይታዩም። ወደ ውጭ ሲመለከት አንድ የሚያቃጨል ድምፅ ዓይኑን ሳበው። የጋሪ ኮቴ ነበር የሰማው።

«በዚህ ሰዓት ደግሞ የምን ጋሪ ነው? ገና ሳይነጋ ማነው ባሁን ሰዓት ቢጋሪ የሚሄደው?» ሲል ራሱን ጠየቀ። ወዲያው የነበረበት ክፍል ሲንኳኳ ሰማ። የሆነ ነገር ከእግር እስከ ራሱ ወረረው፣ በጣም ደነገጠ።

«ማነህ?» ብሎ ሲጠይቅ አንድ ሰው መልስ ሰጠው። «ክቡር ከንቲባ፣ እኔ ነኝ።» በድምፃቸው አሮጊትዋ የቤት ሠራተኛው እንደሆኑ አወቀ።

«ምነው፣ ምን ፈለጉ?» ብሎ ሲጠይቃቸው «ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ሆኗል ጌታዬ» አሉት።

«ታዲያ ምን አለበት?» በማለት ሲናገር «ክቡር ከንቲባ፣ ረሱት እንዴ? ጋሪ በጠዋት እንዲመጣ አዝዘው ነበር እኮ!» አሉት።

«ይቅርታ፣ አዎን አዝዘዉ ነበር።»

አሮጊትዋ ቢያዩት እጅግ ይደነግጡ ነበር። የሻማ ማብሪያዎቹን ተመለከተ። የቀለጠውን ሻማ ጠራረገ። አሮጊትዋ በር ላይ ቆመው ይጠብቃሉ። ሲዘገይባቸው «ጌታዬ፣ ባለጋሪውን ምን ልበለው?» በማለት ሲጠይቁት «ጠብቅ ይበሉት። መጣሁ፣ አንድ ደቂቃ» አሳቸው።

ጋሪው አራብ ከተማ አጠገብ ሲደርስ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ይሆናል። እስካሁን ታሪኩን የተከታተልነው ሰው ከጋሪው ወርዶ በእግሩ ወደ ከተማው ተጓዘ። ከተማውን ከዚያ በፊት አያውቀውም። ለአገሩ ባዳ ለሰዉ እንግዳ ነው። ብዙ ሰሰተጓዘ ሲመለስ መንገዱ ጠፋው። ሲፈራ ሲቸር ከዚያ አካባቢ ፍርድ ቤት እንዳለ አንዱን መንገደኛ ጠየቀ።

«ጌታዬ» አለ ሰውዬው፣ «የፍርድ ቤት ሙግት ለመስማት ፈልገው እንደሆነ ጊዜው መሸቷል። ዳኞቹ ሥራ የሚያቆሙት በአሥራ ሁለት ሰዓት ነው» ብሎት ጥቂት እንደ ተጓዙ አደባባይ ካለበት ሲደርሱ ፍርድ ቤቱ ከዚያ እንደቢ ከራረቀ ከአንድ ትልቅ ሕንፃ ውስጥ እንደሆነ አመላከተው።

«ጌታው እደለኛ ነዎት፣ የፍርድ ቤቱ መብራት አልጠፋም። ዳኞቹ አሁንም ችሎት ላይ ናቸው ማለት ሰለሆነ መግባት ከፈለጉ መግባት ይችላሉ። እስካሁን የቆዩት ምናልባት ለመወሰን የሚያስቸግር ብርቱ አርገር ነገሯቸው መሆን አለበት።»

የሻምፕማትዩን ጉዳይ የያዙት ዳኛ ጽሑፉን ሲያዩ ወረቀቱን የላከላቸው ግለሰብ የሚያውቁት ብቻ ሳይሆን የሚያደንቁትና የሚያከብሩት ሰው እንደሆነ አስተዋሉ። የሥነሥርዓት አስከባሪዎች አለቃ ወረቀቱን ለዳኛው ሲሰጣቸው ከወረቀቱ በተጨማሪ ሰውዬው የምስክርነት ቃላቸውን ለመስጠት እንደሚፈልጉ በቃሉ ገለጸላቸው። ዳኛውም «በቶሎ አስገባቸው» ሲሉ ኃላፊውን አዘዙት። የዚህ ታሪክ ባለቤት የሆነው አሳዛኙና የተከፋው ሰው ወረቀቱን ከሰጠ በኋላ ከነበረበት ሥፍራ አልተነቃነቀም። «ጌታዬ ይከተሉኝ» አለ የሥነሥርዓት አስከባሪዎች አለቃ። ቀደም ሲል ፊቴን ያዞረበት የዘበኞ ኃላፊ አሁን ግን ለጥ ብሎ እጅ ነስቶ ነው 'ይከተሉኝ' ያለው። ኃላፊው በተራው ብጣሽ ወረቀት ለመሬይ ማንደላይን ሰጠው። ወረቀቱ ላይ የተጻፈው ጽሑፍ 'የመሐል ዳኛ የአክብሮት ሰላምታውን ያቀርባል' የሚል ነበር። ወረቀቱን ኪሱ ውስጥ ከተተው። ቢሆንም ያ ወረቀት የሆነ ትዝታ ጫረበት። የሥነሥርዓት አስከባሪዎች ኃላፊን ተከትሎ ሄደ። የመቀመጫ ወንበር ካለበት ሲደርሱ «ጌታዬ ይቀመጡ» አለው።

መሬይ ማንደላይን ኃላፊው በቶሎ እንዲሄድለት ቢፈልግም እርሱ ግን ግድግዳ ተደግፎ ቆመ። ከንቲባው አላበው፣ መተንፈስም አቃተው። መላ ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ። ነገር ግን የተቀመጠበት ቦታ በመጠኑም ቢሆን ዞር ያለ ስለነበር ከዚያ የነበረ ሰው በግላጭ አላየውም። ቁጭ እንዳለ አሳቡን የመቀየር ዝንባሌ ታየበት። 'አሁን ማን አስገድዶኝ ነው የመጣሁት?' ሲል ራሱን ጠየቀ። እንዴት እንደሆነ ሳይታወቀው በቶሎ ብድግ ብሎ በመሪመድ ችሎቱ ውስጥ ዳኞቹ ወደ ነበሩበት ሥፍራ ሄደ።

3

መሬይ ማንደላይን አሳባቢውን በሚገባ ቃኘ። ከፊት ለፊት ከፍ ካለው ቦታ ላይ ዳኞች ተቀምጠዋል። ጠበቆችም ከአጠገባቸው ተቀምጠው አፍዋጠው ያያሉ። ጠባቂ ወታደሮች በየጥጉ ተበታትነው ቆመዋል። የዳኞች ጠረጴዛ በደማቅ ጨርቅ ተሸፍኖአል። የበር እጀታዎች በእድፍ ጠቁረዋል። 'ሰው ሠራሽ ሕግ እውነትን ያወጣል' በሚል እምነት ከዚያ ሾህበረ ሁሉ በጥሞና ያዳምጣል። የሰው ብዛት ከወትሮው በዛ ያለ ስለነበር መሬይ ማንደላይን ማንም ልብ አላለውም። ሰው ሁሉ ይመለከት የነበረው ከውንጀለኞች መቆሚያ ላይ በሁለት ጠባቂዎች ታጅቦው የቆሙትን ተከሳሹ ሻምፕማትዩን ነበር። ከንቲባው አተኩሮ ሲመለከታቸው በመልክ መመሳሰላቸውን ተገነዘበ። በእድሜ ግን እርሳቸው ከእርሱ ያረጁ ናቸው።

ዳኞቹ ከተተመጡበት አሳባቢ ሲደርስ የመሐል ዳኛውና አቃቢ ሕጉ በጉልህ ስላዩትና ስለለዩት የአንገት ሰላምታ ሰጡት። ከሃያ ሰባት ዓመት በፊት ያያቸው ዳኞች፣ ሕግ አስከባሪ፣ ጠበቆችና ሥነሥርዓት አስከባሪዎች መሆናቸውን እርሱም አስታወሰ። ከሰንት ዓመት በኋላ አሁንም ከእነርሱ እጅ ሊወድቅ በመሆኑና ውሳኔአቸውም ስላስፈራው ዓይኑን ጨፈነ። ከፊት ለፊቱ የቆሙት ተከሳሽ 'ጣርን ቫልጣ ናቸው ተብሎ የተከሰሱት' የሚል አሳብ ስለተቀረጸበትና ጎሊናውን የሳተ ስለመሰለው ቶሎ ብሎ ከወንበር ላይ ቁጭ አለ። ወዲያው እንደ ተቀመጠ ጣቪርን በዓይኑ ፈለገው፣ ግን አላገኘውም። ሕግ አስከባሪው በምስክሮችና በእርሱ መካከል ስለተቀመጠ እነርሱንም ለማየት አልቻለም። ከፍሉ ጨለምለም ያለ ስለነበርና ቦግ ያለ ብርሃንም ስላልነበረው ሰዎችን ከሩቅ ለመለየት አስቸጋሪ ነበር።

ከርከሩ የፈጀው ወደ ሦስት ሰዓት ገደማ ሲሆን ተከሳሹ እንደበተረቱዕ ስላልነበሩ የተከሰሱበትን ይካዱ እንጂ ጉዳያቸውን በሚገባ አላስረዱም። እንዲያውም ብዙውን ጊዜ ጣራ ጣራውን ነበር የሚያዩት። ሲያደምቸው ቂላቂልና ጅላጅል ቢጤ ይመስላሉ። ቀደም ሲል እንደ ተነገረው በእኚህ የተገኘው ፍራፍሬ ከየት እንዳገኙት ተከሳሹ ሲጠየቁ ከመሬት እንደሆነ አስረድተዋል። ምናልባትም ፍራፍሬ የያዘው የዛፍ ቅርንጫፍ ሌባ ቀጥፎ ከመንገድ ላይ ሊጥለው ይችላል። ስለዚህ ፍራፍሬዎችን የያዘ ቅርንጫፍ በመስበር የሰረቁት ሻምፓማትዩ ናቸው ለማለት ያስቸግራል። በዚህም የተነሳ በስርቆት ወንጀል አልተከሰሱም። ሆኖም ከእስር ቤት ለማምለጣቸው በበቂ ማስረጃ ስለተረጋገጠ በዚያ ወንጀል ተከስሰዋል። ጣን ቫልጣ ለመሆናቸው ምስክሮች ቢያረጋግጡም እርሳቸው ግን እስከ መጨረሻው ክደዋል።

«ከሀዲቱን ትተው የፍርድ ቤቱን መልካም አስተያየት ቢጠይቁ የሚበጅ መሆኑን ቢገለጽላቸውም አሻፈረኝ ብለዋል። በእርሳቸው አመለካከት ወንጀላቸውን ስለካዱ ከቅጣት የሚያመልጡ መስሎአቸው ይሆናል። በዚህ በኩል በጣም ተሳስተዋል። ይህ እንግዲህ ከእውቀት ማነስ እንጂ ሆን ተብሎ የተደረገ ሊሆን አይችልም። ተከሳሹ በእርግጥ

ንቃት ይጉድላቸዋል። ይህም የሆነው ምናልባት ለረጅም ጊዜ ከእስር ቤት ቆይተው በመለቀቃቸውና ከዚያም በኋላ ብዙ ስለተንከራተቱ ወይም ደግሞ በሌላም ምክንያት ሊሆን ይችላል። ሆነም ቀረም የእርሳቸው እነጋገር አለማወቅ ወይም ችሎታ ማነስ ከሚሰጠው ብያኔ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር አይገባም። ተከሳሹ ዣን ቫልዣ እንደሆኑና የቅጣት ዘመናቸውን ሳይጨርሱ ከእስር ቤት ለማምለጣቸው ጥርጥር የለውም። ስለዚህ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ—መሠረት ተገቢውን ቅጣት እንዲጣልባቸው በትህትና እጠይቃለሁ።»

ዳኞች ስለሰሙት አስተያየትና ስለፈጸሙት ጥልቅ ምርምር ሕግ አስከባሪው በቅድሚያ ምስጋናውን አቅርቦአል። ተከሳሹን ግን የዳኞችን አስተያየት መሠረት በማድረግ ክፉኛ ነቅፎአቸዋል። ተከሳሹ ዣን ቫልዣ መሆናቸውን ስለመረጋገጡ ሲያስረዳም «ዝም ማለታቸው በራሱ ክሱን መቀበላቸውን ያሳያል። ቀደም ሲል የተከሰሱበትን ጉዳይ ከደው ነበር። ለመሆኑ ዣን ቫልዣ ማነው? ዣን ቫልዣ እኮ የተተፋ፣ አገር የጠላውና ሌላም፣ ሌላም ቅጽል ሊሰጠው የሚችል አስከፊ ፍጡር ነው» ብሎ ሲናገር ከዚያ የነበረ ሰው ሁሉ ተሸማቀቀ። «ሻምፕማትዩ ማለት ዣን ቫልዣ ማለት ነው» ተብሎ ክስ ሲመሠረት 'ጉርናል ደ. ላ. ፕሪፌትየር' የተሰኘ ጋዜጣ ስለዚህ ሰው ሲያስረዳ «ዣን ቫልዣ ማለት ወሮበላ፣ ቀጣፊ፣ ለማኝ፣ መተዳደሪያ የሌለው አውደልዳይ፣ ሕይወቱን ወንጀል በመሥራት የሚመራና ሌላም፣ ሌላም ቅጽል ሊሰጠው የሚገባ ሰው ነው» ብሎ እንደ ጻፈ በመግለጽ ሕግ አስከባሪው ተናገረ።

«ይህ ሰው ፍራፍሬ ሰርቆ ቢያዝም አድራጎቱን ክዷል። እንዲሁም ከእስር ቤት ለማምለጡም ከሕግ ፊት ክዷል። የሚገርመው ደግሞ ይህ ሰው የገዛ ሰሙን እንኳን የካደ ነው። ምን ያልሳደው ነገር አለ! ሕልውናውን ጭምር ነው የካደው ለማለት ይቻላል። ነገር ግን እርሱ ሽንጡን ገትሮ ቢከድም አራት ምስክሮች መስክረውበታል። የተከበሩና ውሸት የማያውቁት የፖሊስ አዛዥ ዣቬር በእርሱ ላይ መስክረዋል። ከተከሳሹ ጋር አብረው ታስረው ከነበሩት ሰዎች መካከል ሦስት እስረኞችም መስክረውበታል። ይህ ሰው እነዚህ አራት ምስክሮች ከመሰከሩበት በኋላ እንኳን ወንጀሉን አምኖ ይቅርታ አልጠየቀም። ስለዚህ ማኅበራዊ ሕይወትን ሊያፋልስ ታጥቆ የተነሣ ወንጀለኛ በመሆኑ ቅጣቱ ሊቃለልለት አይገባም።»

ይህን እርሳቸውን ክፉኛ የሚወነጅል ማብራሪያ ሕግ አስከባሪው ሲሰጥ ዳኞቹ እሩቸውን ከፍተው በመገረም ሀዘን እየተሰማቸው አዳመጡት። ሕግ አስከባሪው እንደበተ-ርዕቱ በመሆኑ አነጋገሩን ቢያደንቁም በማያውቁት

ነገር እንደዚያ ሲመርድባቸው በልባቸው ክፉኛ ረገሙት። ተከሳሹ ግሬ ቀኙን ከቃኙ በኋላ ራሳቸውን ነቀነቁ እንጂ አልተናገሩም። ሕግ አስከባሪው ግን ትችቱን ቀጠለ።

«ማንኛውም ሰው ወንጀል ሊሠራ ወይም ሊዋሽ ይችላል፣ ከሕግ ሊያመልጥ ግን አይችልም። ይህ ሰው ወንጀል ከመሥራት አልፎ ከሕግ ለማምለጥ ሞክሯል። ይህ እንግዲህ ክብድ ወንጀል ስለሆነ በእድሜ ልክ እሥራት እንዲቀጣ አሳስባለሁ፣ ችሎቱንም አመሰግናለሁ።»

«ስለተሰጠው አስተያየት የሚሰጡት መልስ አለ?» ሲሉ የመሐል ዳኛው ተከሳሹን ጠየቋቸው። ቆባቸውን ያፍተለትሉ የነበሩት የቤተክርስቲያን ሰው ምንም ነገር እንዳልሰሙ ሆነው ዝም አሉ። ዳኛው ጥያቄውን ደገሙላቸው። አሁን ግን ጥያቄውን ስለሰሙ ዳኛው ምን ማለት እንደ ፈለጉ ገባቸው። ይህን ጊዜ ከእንቅልፉ እንደ ነቃ ሰው ከወዲያ ወዲህ ተመለከቱ። ዳኞቹን፣ ሕግ አስከባሪውን፣ ጠበቆችንና ተመልካች ሕዝብን አፍጥጠው ካዩ በኋላ ከፊት ለፊት የነበረውን መከለያ ብረት አጥብቀው ያዙ። ከዚያም በከፍተኛ ድምፅ መናገር ጀመሩ። ቃላት ተሸቀዳደሙ 'እኔ ልቅደም፣ የለም እኔ ልቅደም' ያልዋቸው ይመስል እየተቻኮሉ በኃይለኛ ፍጥነት ተናገሩ።

«የምለውን በጥሞና አድምጡኝ። ከመሲይ ባሉፕ ሱቅ ለጋሪ የሚሆን የብረት ተሸከርካሪ ሠራተኛ ነኝ። ብረት መቀጥቀጥ እጅግ በጣም ከባድ የሆነ ሥራ ነው። ሥራውን እንሠራ የነበረው ክቤት ውጭ ሲሆን አሠሪያችን ለሠራተኞች ደኅንነት ይህን ያህል ደንታ የላቸውም። ደግ አሠሪ ለሠራተኞቹ በማሰብ ለሥራ መሥሪያ የሚሆን የተለየ ቤት ያዘጋጃል። እኛ ግን ሥራችንን የምንሠራው ሜዳ ላይ ነው። በብርድ ጊዜ ቆፈን ሲይዘን ሥራችንን አቁመን በትንፋሻችን እጆቻችንን ያሞቅን እንደሆነ አሠሪያችን ግሥላ መስለው በጣም ይቆጡናል። 'ለምን የሥራ ጊዜ ታባክናላችሁ' እያሉም ይጮሁብናል። በተለይ በክረምት ክብድ በረዶ በሚጥልበት ሰዓት ብረት መቀጥቀጥ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ የደረበበት ብቻ ነው የሚያውቀው። በአሜር ጊዜ ውስጥ ስውነትን አሟምቶ በልጅነት ያስረጃል። በዚህ ሥራ ላይ የተሰማራ ሁሉ በእርባ ዓመቱ የሰማንያ ዓመት ሽማሌ ያስመስለዋል። ሰው ሲያረጅ 'አሮጌ ውሻ' ብለው ነው የሚጠሩት። አሠሪዎች ያረጀ ሽማግሌን መጦር ስለማይፈልጉ እኔም ላይ ጨክነው ከአሥራ ሦስት ዓመት ክሞላኝ በኋላ ብዙ ጊዜ ያመኝ ጀመር። በእርጅናዬ ዘመን በቀን ለሳላ ሱስ ነበር የሚከፍሉኝ። ግንዘቡ እጅግ አነስተኛ ቢሆንም ምርጫ ስላልነበረኝ በዚቹ አነስተኛ ደመወዝ መሥራቴን ቀጠልኩ።

«ዘንድሮን ጊዜ እንዲት ልብስ አጣቢ ልጅ ነበረችኝ። ልጄ ልብስ እያጠበች በየጊዜው ጥሪት ገንዘብ ታመጣልኝ ነበር። እርስዋ ለፍታ የምታመጣውን ገንዘብ በማሩር እየተንገዳገድን 'ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል' እንዲሉ፣ እንደግይኖር የለምና እኛም እንዳቅማችን ኑሮን ኖርናት። ዶፍ ቢወርድ፣ ሙሩር ቢያቅጥል ልጄ ወደ ኋላ ሳትል ቀኑን ሙሉ ልብስ ታጥባ ሳለች። ከደምበኞችዋ አብዛኛዎቹ የሚቀይሩት ልብስ የሌላቸው ስለነበሩ የሚለዋወጥ ልብስ በእለቱ ታጥቦና ተተኩሶ ማስረከብ ግዴታዋ ነበር። ተያፂዎቹው ካልተሟላ ዳግም ተመልሰው አይመጡም። የልብስ አጣቢ ሰውነት ከእግር እስከ ጭንቅላት ይርሳል። ልጄ ልብሶቹን ታጥብ የነበረው ከአሲት ውስጥ ሳይሆን ወንዝ ወርዳ ነበር። አንዳንዴ ከወንዝ የምትመለሰው ጀምበር ከጠለቀች በኋላ ስለነበር በጣም ይደክማታል። ወዲያው እንደ መጣች ለመተኛት ከመሬት ላይ ትዘረራለች። ባልዋ እኔ ፊት ጭምር ጠፋት ማታ ይቀጠቅጣታል። ልጄ አንድ ቀን እንኳን ሳይደላት ከዚህ ኮሚሪ ዓለም ርቃ ሄዳለች። ከዚያ ሁሉ ስቃይና መከራ ተገላግላ ዛሬ ቤቷደወት የለችም። መኳንንቶቼ የምናገረው ነገር ሁሉ እውነት ነው፣ እየሞገሙ አይደለም። እኔ ግን እንደሆንኩ ለማወቅ ከፈለጋችሁ አሁኑኑ ሂዳችሁ መሲይ ባሎጥን ብትጠይቋቸው እውነቱን ያወጣሉ። ከዚህ ወዲያ የምለው የለኝም። እናንተ ከእኔ ምን እንደምትፈልጉ እኔ አላውቅም።»

ሰውዬው ንግግራቸውን አቆሙ እንጂ ቁጭ አላሉም። በቁጭትና በብሽቀቀት የተሞላ ንግግራቸውን ሲያቆሙ ከዚያ የነበረው ሰው ሁሉ ሳቀባቸው። ቀና ብሉ በማየት የሚስቁትን ሁሉ በዓይን ገረመምዋቸው። ነገር ግን ምክንያቱን ሳያውቁ እርሳቸውም መሳቅ ጀመሩ።

«ማይክና የሚያስፈራ ነገር ነው፣ አይደል?» አሉ መሐል ዳኛው። ዳኛው ቀን መንፈሰና ለሰው የሚያዝኑ ዓይነት ሰው ስለነበሩ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው «ይህ መሲይ ባሎጥ የተባለውን አሠሪ ተከሳሹ ቀደም ብለው የጠቀሱት ሰው ስለነበር ሰውዬው ተፈልጎ ሊገኝ አልቻለም። ድርጅቱ ስለሠሠረ አገር ቱሉ ኩባንሳል» ካሉ በኋላ ዳኛው ተከሳሹን እየተመለከቱ «ሂደትህ ይሻላል፣ ሆኖም ግን በመጪውን አንድትመልስልኝ የምጠይቃቸው ሁለት ጥያቄዎች አሉኝ። እነዚህም አንደኛ 'ፍራፍሬ ሰርቀሃል ወይስ አልሰረቅህም' ሁለተኛ ከህጠር ቤት ያመለጠውና ወንጀለኛው ጎን ባልገር ግስት አንተ 'ከ ወደ አይደለህም'?»

የሚናገረውን አጥርቶ እንደማያውቅና የተናገረውን በትክክል የገባው ሰው እንደማያደርገው ሁሉ እርሳቸውም 'የምለውን በሚገባ አጥርቼ አውቃለሁ' በማለ ሰሚነት ጭንቅላታቸውን ነቀነቁ። እርሳቸውም በተራቸው

የመሐል ዳኛውን እያዩ «በመጀመሪያ ደረጃ» ካሉ በኋላ ቀና ብለው ሚዛ ጣራውን ተመለከቱ። ቀጥሎም ከችሎቱ ውስጥ የተቀመጠውን ሰው ሁሉ በዓይናቸው ቃኙ። ይህን ጊዜ «ምን ከወዲያ ወዲህ ትላለህ? የተጠየቅኸውን መልስ እንጂ፣ በራስህ ላይ እኮ ነው የምትፈርደው» አለ ሕገ አስከባሪው ጣልቃ በመግባት። ተከሳሹ ወዲያው ከመቅጽበት በአፋጣኝ ተናኙ።

«እውና እጅግ ጨካኝ ሰው ነዎት፣ ማለቴ እርስዎ አዜን በመጨረሻ የተናገሩት። እኔ የምሠራውንና የምናገረውን አውቃለሁ። ፍሬ የሚገባ ነገር አልሰረቅኩም። ስርቆት የሚባል ነገርም አይነካክኝም። የእለተ እንጀራ እንኳን በቅጡ የማላገኝ ሰው ነኝ። ገላዬን ለመታጠብ ከወንዝ ወርጀ ስመለስ መንገዱ ሁሉ ጭቃ ሆነብኝ። ኩጭቃው ለመሸሽ ቦግ ጥን ይኛ ስራመድ ፍራፍሬዎችን የየዘ የዛፍ ቅርንጫፍ አየሁ። 'የወደቀን አንሳ፣ የሞተን ቅበሩ' እንዲሉ እኔም ያንን ቅርንጫፍ አነሳሁት። ያነሳሁት ይህን ሁሉ መከራና ስቃይ ያስከትልብኛል ብዬ አላሰብኩም ነበር። ያነሳሁት ስለራበኝ ነው። አሁን ግን በዚያ ሰበብ ከታሠርኩ ሦስት ወሬ ነው። ከዚህ ወዲያ የማወሳው ታሪክ የለኝም። አንተ ታዲያ ክሱ ለው በመሆንህ ትሰድበኛለህ። 'አትፍረድ እንዳይፈረድብህ' የተባለውን ረስተህ ባአኔ ላይ ትፈርዳለህ። የሥነሥርዓት አስከባሪዎች አለቃ ግን ደግ ሰው ቢመስሉ ወደ ጀሮዬ ጠጋ ብሉ 'መልስ ይስጡ እንጂ' ሊያለ በትህትና ይመክረኛል።

«እኔ እንደሆነ ብዙ ገፍቼ ባለመማሬና አሳበ-ውስጠ በመሆኔ የንግግርና ሰውን የማሳመን ችሎታ የለኝም። ስለዚህ አሳቤን በቁርጥ ማቅረብ ያዳግተኛል። ከችሎቱ ውስጥ ያላችሁት ሁሉ ሌባ አለመሆኔን ለማየት ስላልቻላችሁ ትስቁብኛላችሁ። ከልቤ ልንገራችሁ፣ ተነስታችኋል። ከዘንግ ጎልገፐ ትናገራላችሁ። እኔ ይህ ሰው ማን እንደሆነ አላውቅም። እኔ እሠራ የነበረው ከመሲይ ባሎጥ ድርጅት ውስጥ ሲሆን ስሜ ሽምጥማት፣ ይባላል። ጉበቦች ብትሆኑ የት እንደ ተወለድኩ ትጠይቁኝ ነበር። ቢሆንም ግን እኔም ስለራሴ ብዙ አላውቅም። እያንዳንዱ ሰው የተወለደበት አዜ ወይም መንደር ሊኖረው ይችላል። እኔ ግን የት እንደ ተወለድኩ እንኳን አላውቅም። እናቴና አባቴ ዘላኖች ስለነበሩ የኖሩት ከሀገሪ ቦታ እየተዘዋወሩ ነው። ስወለድ 'ማሙሽ' እያሉ ነበር የሚጠሩኝ። አሁን ደግሞ 'ሽማሙ' እየተባልኩ ነው የምጠራው። በትክክል እኔ የምጠራበትው ስሞች የክርስትና ስሞች ናቸው። አንተ ግን እንደፈለግከው ልትለይማቸው ትችላለህ። ብቻ ለመነኝ፣ እኔ እናንተ እንደምትሉት ሌላ ሰው ሳልሆን አባ ሽምጥማት፣ ነኝ። የኖርኩትም ከአሠሪዬ ከመሲይ ባሎጥ ቤት ነው። እኔ አሁን የለለኝ ነገር ቢኖር እናንተ የምትሉትን ታሪክ መስማት ነው። ሰው ሁሉ እንደ አብድ ውሻ እያየኝ እኔን የሚከታተልበት ምክንያት አይገባኝም።»

ኢቃቤ ሕጉ ዳኞችን እያየ «ጌታዬ፣ ይህ ሰው አላዋቂ በመምሰል የጮሌ ተግባር እየፈጸመ ስለሆነ የተከተለው የብልጠት ተግባር መልካም ፍሬ እያፈራለትም:: የፍርድ ቤቱ መልካም ፈቃድ ከሆነ የዚህን ሰው ብልጠት ለማክሸፍ አራቱ ምስክሮች በአንድነት ተጠርተው በድጋሚ እንዲመሰክሩበት በእከብሮት እጠይቃለሁ» አለ:: የመሐል ዳኛም ሲመልሱ «አቃቤ ሕጉን ለማሳሰብ የምፈልገው የፖሊስ አዛገር ጉቬር የምስክርነት ቃሉን ከሰጠ በኋላ አጣዳፊ ሥራ ስለነበረበት ይቅርታ ጠይቆ ወደ መጣበት ሄዷል:: የሄደውም ፍርድ ቤቱ ስለፈቀደለት ነው» አሉ::

«እውነት ነው» አለ አቃቤ ሕጉ፣ «መሴይ ጉቬር አሁን ከዚህ ሊመጡ አይችሉም:: ሆኖም ግን እርሳቸው ለክቡር ፍርድ ቤቱ ያሰሙት የምስክርነት ቃል በድጋሚ መናገር ይቻላል:: መሴይ ጉቬር የተከበሩ ሰው ናቸው:: ሥራቸውን የሚያከብሩና ለእውነት የቆሙ ሰው ለመሆናቸው የሚጠራጠሩት አይደለም:: ስለዚህ እርሳቸው የሰጡት የምስክርነት ቃል ሳይጠራጠሩ በእውነትነቱ መቀበል ይቻላል:: እርሳቸውም ሲናገሩ 'የተከሳሹን ክህደት ለማስተባበል የመሐላ ቃል ወይንም የተለየ ማረጋገጫ አያስፈልገንም:: ይህን ሰው በትክክል ለመለየቴ ጥርጥር የለውም:: የዚህ ሰው ስም ሻምፕግትዩ ሳይሆን ወንጀለኛውና እጅግ የሚፈራው ጉን ቫልጉ ነው:: የቱሉን እስር ቤት ዘቦች አለቃ በነበርኩበት ጊዜ ሰውዬውን ለረጅም ዘመን አይቼዋለሁ:: ቃሌን እንደገና ብደግም ይህን ሰው ገና ሳየው ነው ያወቅሁት' በማለት መስክረዋል::»

የዚህ ሰው አገላለጽ በዳኞቹና ከዚያ በነበረ ሰው ላይ ሰርጾ የመግባትና የማሳመን ኃይል ነበረው:: የመሴይ ጉቬር የምስክርነት ቃል አስተዋጽዖ ካደግ በኋላ የፖሊስ አዛዡን ከዚያ በድጋሚ የማስጠራቱን አሳብ ትቶ ምሁሩ ምሰክሮች ብቻ ቃላቸውን በድጋሚ እንዲያሰሙና አንዳንድ ጥያቄ እንዲቀርብላቸው አቃቤ ሕጉ አሳሰበ:: በዚህ ጊዜ የሥነሥርዓት አስከባሪ ፖሊስ ምሰክሮችን በድጋሚ እንዲያስገባ ዳኛው አዘዙ:: ጉን ቫልጉ ከእስር ቤት ካመለጠ በኋላ የእስራት ዘመኑን ጨርሶ የተለቀቀው ብሪቬት የሚባል ሰው በትደጋያ ተጠርቶ ገባ:: የብሪቬት እድሜ ስልሳ ዓመት ገደማ ነበር::

«ብሪቬት፣ ለመድገም የሚከብድ የረጅም ዘመን ቅጣት ተቀብለሃል:: ስለዚህ መሐላ ለመማል አትችልም» ሲሉት ብሪቬት ወደ መሬት አቀረቀረ:: «ሆኖም ሕግ ያዋረደውና በሥራው የተቀጣ ወንጀለኛ መቼም በውስጡ ሊላውን የማክበርና የሊላውን መብት የመጠበቅ ስሜት ይኖረዋል ብዬ አምናለሁ:: ምናልባት ቀደም ሲል በሰጠኸው የምስክርነት ቃል በኅሊናህ ዳኝነት የምታሻሽለው ነገር ቢኖር እንድታሰማን እጠይቅሃለሁ:: ተከሳሹም ተነስቶ እንዲቆምና መስካሪውም ተከሳሹን እያየ እንዲናገር ሆኖ ጌዳዩ የቆየ በመሆኑ መስካሪው አስቦና አሰላስሎ አሳቡን እንዲሰጠን አሳስባለሁ:: ይህ ሰው ቀደም ብላችሁ እስር ቤት ውስጥ አብራችሁ የኖራችሁት ጉን ቫልጉ የሚባል እስረኛ ለመሆኑ አረጋግጠህ ለመመስከር ትችል እንደሆነ የምስክርነት ቃልህን በድጋሚ እንድትሰጥ አጠንክሬ እጠይቃለሁ» ሲሉት ብሪቬት ተከሳሹን አተኩሮ ተመለከታቸው:: ከዚያም ፊቱን ወደ ዳኞቹ አዞረ:: ብሪቬትና ሻምፕግትዩ ዓይን ለዓይን በመፋጠጥ ተያዩ::

«አዎን ጌታዬ፣ ይህ ሰው ጉን ቫልጉ ለመሆኑ በመጀመሪያ የሰየሁት እኔ ነኝ:: አሁንም ቃሌን አልለውጥም፣ ይህ ሰው ጉን ቫልጉ ነው:: ቱሉን ከሚገኝ ወህኒ ቤት የገባው በ1796 ዓ.ም. ሲሆን ከዚያ ያመለጠው በ1815 ዓ.ም. ነው:: እኔ ከእስር ቤት የወጣሁት እርሱ ባመለጠ በዓመቴ ነበር:: ሰውዬውን አሁን ሳየው በመጠኑም ቢሆን ተለውጧል:: ነገር ግን ለውጡ ከእድሜ ጋር የሚሄድ ስለሆነ ያሳየው ለውጥ እኔን ሊያሳስት አይችልም:: ጉን ቫልጉ ራሱ ነው» ብሎ በማረጋገጥ ሲመሰክር ዳኛው እርሱ እንዲቀመጥ፣ ተከሳሹ ግን እንደቆመ እንዲቆይ አዘዙ::

ቀጥሎ ሸኒልዲዩ የሚባል ምስክር እንዲገባ ተደረገ:: ይህ ሰው ቱሉን ከተማ ውስጥ ከሚገኝ እስር ቤት የእድሜ ልክ እስራት የተፈረደበት ወንጀለኛ ነው:: የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ነው የተጠራው:: ቁመቱ አጠር ያለ የሃምሳ ዓመት አዛውንት ሲሆን ምን እንኳን ፊቱ ቢጨማደድም በሁኔታው ነቃ ያለ ተቅበጥባጭ ሰው ነው:: ዳኛው ለብሪቬት ያሉትን ለእርሱም ደገሙለት::

«በሠራኸው ወንጀል ምክንያት በመማል ቃልህን ታከብራለህ ለማለት ስለማያስደፍር መማል እትችልም» ሲሉት ሻምፕግትዩ እንገታቸውን ቀና አድርገው ከዚያ የነበረውን ሰው በድጋሚ በዓይን ቃኙት:: ዳኛው አሳቡን እንዲያሰባስብና እስረኛውን በትክክል ያውቀው እንደሆነ እንዲያስረዳ ሸኒልዲዩን ሲጠይቁት ከት ብሎ ሳቀ::

«ታውቀው እንደሆነ አሉኝ! አምስት ዓመት ሙሉ በአንድ ሰንሰለት ታስረን እኮ ነው የኖርነው:: አንተ በአንድ ብረት ታስረን አልነበረምን» ብሎ ተከሳሹን ሲጠይቅ ዳኛው «ቁጭ በል» አሉት::

የሥነሥርዓት አስከባሪ ፖሊስ አዛዥ ኮሽፔል የሚባለውን መስካሪ አስገባ:: ይህ ሰው የእድሜ ልክ እስራት የተፈረደበት ሌላው እስረኛ ሲሆን ከመታሰሩ በፊት ከብት የሚያረባ ገበሬ ነበር:: ወደ ኋላ ግን ከብት ማርባቱን ትቶ ወደ ሽፍታነት የተለወጠ አደገኛ ሰው ሆነ:: ሰውዬውን

ሰውዬው ከቆመበት አጠገብ በርቶ የነበረው መብራት የሰውዬውን ጫታ በጉልህ አሳየ። ቆቡን በእጁ ይዟል። ሽክ ብሎ ለብሶ የካፖርቱን ቁልፍ አስተካክሎ ነው የቄሰፈው። ፀጉሩ ግን ሸብቷል። ሦስቱም መስካሪዎች ወደ እርሱ አፈጠጡ። ሦስቱም 'በእርግጥ ራሱ ነው' ሲሉ ለራሳቸው ነገሩ። የሰውዬው ድምፅ መስካሪዎቹን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ሰው አፈዘዘ። 'ምንድነው ነገሩ!' እያለ ሁሉም ሰው ግራ ተጋባ። ሰውዬው በጣም ረጋ ያለ ሰው ነው። ከእዚያ የነበረ ሰው ሁሉ ከዚህ እርጋታን የተካነ ከሚመስል ፍጡር እንደዚያ ያለ ሰንጥቆ የሚሄድ ድምፅ ወጣ ብሎ ለማመን ተቸገረ። ዳኛውና ሕግ አስከባሪው ቃል ከመተንፈሳቸውና የሥነሥርዓት አስከባሪ ፖሊሶች ኃላፊ 'መልሱት' ብሎ ትእዛዝ ከማስተላለፉ በፊት መሴይ ማንደላይን በፍጥነት በመራመድ ምስክሮቹ ወደ ነበሩበት ሄደ።

«ብሪቬት፣ ኮሽፔል፣ ሸኔልድዩ እኔን አታውቁኝም?» ብሎ ሲጠይቃቸው ሦስቱም በመፍዘዝ ተመለከቱት። ቄንቅላታቸውን በማወዛወዝ አለማወቃቸውን ገለጹለት። ኮሽፔል በጣም ስለፈራ ተነስቶ እጅ ነሳው። መሴይ ማንደላይን ፊቱን ወደ ዳኞቹ አዙሮ በለሰለሰ አንደበት ተናገረ።

«የተከበራችሁ ዳኞች፣ ተከሳሹን ልቀቁት። ክቡርነትዎ እኔን ግን 'ያዙት' ብለው ትእዛዝ ያስተላልፉ። የምትፈልጉት ዣን ቫልዣ ማለት እኔ ነኝ» ብሎ ሲናገር ቤቱ ፀጥ፣ ረጭ አለ። አንድ ሰው እንኳን ከነበረበት ተነቃንቆ ወንበር አላንቋቋም። እያንዳንዱ ሰው ከዚያ ቤት ውስጥ ፍትህ የሰፈነ መሰለው። የመሐል ዳኛው ፊት በሀዘን ተዋጠ። ከአቃቤ ሕጉ ጋር ዓይን ለዓይን ተያዩ። ሕግ አስከባሪው የግራ ቀኝ ዳኞች ጋር ዝግ ባለ ድምፅ ቃላት ተለዋወጡ። ወደ ተመልካቹ ሕዝብም ፊቱን እዞሮ «ከመካከላችሁ ሐኪም ይገኛል?» ሲል ጠየቀ። በመቀጠልም «የተከበራችሁ ዳኞች፣ አሁን የሰማነው ነገር እጅግ የሚከነክንና የሚረብሽ ነው። በግል እውቀት ባይሆን በገና የሞንቴስ ሱር ሞንቴስ ከንቲባ መሴይ ማንደላይንን እናውቃቸዋለን። በእናንተ መሐል ምናልባት ሐኪም ካለ ለክብራቸውና ለዝናቸው ብላችሁ እባካችሁ እርድዋቸው» ሲል በመጮህ ተናገረ።

ሕግ አስከባሪው ንግግሩን እንዲቀጥል መሴይ ማንደላይን እድል አልሰጠውም። በተረጋጋና ጆሮን በሚስብ ድምፅ ንግግሩን አቋረጠበት። ከችሎቱ ውስጥ የነበረ የዓይን ምስክር የጻፈውንና ማንደላይን የተናገሩትን ሙሉ ቃል ምንም ሳንለውጥ ቀጥለን እናቀርባለን። ጸሐፊው ንግግሩን በጽሑፍ ያሰፈረው ችሎቱ እንደ ተነሳ ወዲያው ነበር።

ቢድፍን ሲመለከቱትና ሲያጤኑት ከተከሳሹ ይበልጥ የቂላቂል ባህርይ ያለው ይመስላል። ሲወለድ ጀምሮም ተፈጥሮ ፊትዋን ያዞረችበት፣ የአውሬ ባህርይ ያለውና አስር ቤት እጣ ከፍሉ የሆነ ሰው ነው። ዳኛው ለሌሎች የተናገሩትን በመድገም «ከፊትህ የቆመውን ሰው ስታየው ሳትጠራጠር ሊሉት በቁጥጥት «ዣን ቫልዣ ነው» አላቸው። «ዣን ቫልዣ እያሉም ሰዎች የሚጠሩትና እጅግ በጣም ጉልበተኛ የነበረ ሰው መሆኑን አውቃለሁ።»

እያንዳንዱ መስካሪ በተናገረ ቁጥር ከችሎቱ ውስጥ የነበረ ሁሉ «ተከሳሹ ዣን ቫልዣ ነው ወይስ አይደለም» የሚለውን ጥርጣሬ አስወግዶ ወደ ማመኑ ደረጃ ተቃረበ። እያንዳንዱ ሰው 'ይኼ ሰው አለቀለት' በማለት ሁሉም በየፊናው አጉረመረመ። መስካሪዎች ተመሳሳይ የሆነ የምስክርነት ቃላቸውን ሲሰጡ ሰዉ በይበልጥ ተንጫጫ። ሁሉም በያለበት በአባ ሻምፕማትዩ ላይ ፈረደ። አንዱ መስካሪ ያለውን ሌላው እያጠ ነከረው ሲሄድ ተከሳሹ ጆሮአቸውን ማመን ተስኖአቸው በይበልጥ ፈዘዙ። የመጀመሪያው ምስክር ቃሉን እንደ ሰጠ «አይ ግድ የለም፣ ሌላ ምስክር አለ» በማለት እርስ በራሳቸው ሲነጋገሩ ከአጠገባቸው የነበረው ሁለተኛው ምስክር ሰማቸው። የሁለተኛው ምስክር ቃሉን ሲሰጥ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው «ያዙና፣ ጥሩ ነው» ሲሉ ተናገሩ ተከሳሹ። የመጨረሻውና ሦስተኛው ምስክር ቃሉን ሲሰጥ በጣም ጮክ ብለው «በጣም ጉበዝ» ባሉ ጊዜ ዳኛው ፊታቸውን ወደ ተከሳሹ አዞሩ።

«ሦስቱም መስካሪዎች ያሉትን ሰምተዋል፤ ታዲያ አሁንስ ምን ይላሉ?» ብለው ሊጠይቁ «ምን እላለሁ፤ ሁሉም ጉበዞች ናቸው!» ብለው መለሱ። በዚህ ጊዜ ከዚያ የነበረ ሰው ሁሉ በያለበት ተንጫጫ። ሁሉም በየፊናው የግሉን ብያኔ በመሰጠት እና አውጥቶ 'ይህ ሰው በቃው' ባለ ጊዜ ዳኛው «ቀጥታ እሰጣችሁ» አሉ። «እንግዲህ አሁን ጉዳዩን አጠቃልለን የውሳኔ አሳብ መሰጠት ይኖርብናል» ሲሉ 'ብር የሆነ ጉርሃን ያለ ድምፅ ያለው ሰው ዳኞች ከተቀመጡበት አነባቢ ሲናገር የተሰማው።

«ብሪቬት፣ ሼኔልዲዩና ኮሽፔል እስቲ አንድ ጊዜ ወደዚህ ተመልከቱ» የሚል ድምፅ ቢሰሙ ሦስቱም መስካሪዎች ከው አሉ። በጥፊ የተመቱም መሰላቸው። መስካሪዎች በአንድነት ፊታቸውን አዞሩ። ባለሥልጣናት ከሚቀመጡበት ወንበር ላይ ተቀምጠ የነበረ አንድ ሰው ተነስቶ ዳኞች ከተሰየሙበት አነባቢ ሲሄድ አዩ። የመሐል ዳኛው፣ ሕግ አስከባሪውና ሌሎች አንድ ሃያ የሚሆኑ ሰዎች ይህ ሰው ማን እንደሆነ አወቁ።